# ታጠቅ

የቴዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የኢትዮጵያ
## ጊ ዜ ያ ዊ ሁ ኔ ታ

● የጦር ሃይሎች ደርግና የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ጉዳይ ●

P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 1.

ጥቅምት 1967

## ማውጫ


መቅድም ________________________________ ገጽ ሀ

መግቢያ ____ "ተጎታች ኩዴታ" ______________ ገጽ 1

1. የኃይለ ሥላሴ መገለበጥና የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ሥርዓት ሁኔታ ________________ 6

2. የጦር ሃይሎች አቀናባሪ ደርግ ሥራዎችና አቋም 10

3. የኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ መደቦችና የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ________________ 24

4. የሚከተለው ዐርምጃ ምን መሆን አለበት? _____ 37

ቀኖችና ድርጊቶች ________________ 60


ዋጋው $1.50

## መቅድም

ባገራችን በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው ፖለቲካዊ ለውጥ ባንድ በኩል የተጎተተ በመስለም፣በሌላ በኩል ደግሞ የሁኔታው አስተዳደግ በጣም ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ ለመከታተል አስቸጋሪ ሆኖአል። አንዳንድ ያገር ቤት ጓዶች እኛን፣በውጭ የምንገኘውን፣ካገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታ ርቃችኋልና ብዙ ነገር አይገባችሁም ይሉናል። እርግጥም እዚህ ሆኖ ያገሪቷን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ለመከታተል ስለሚያስቸግር ብዙ ዜናዎች ይጎሉናል፣ ወዐት የማናውቃቸው ነገሮች አሉ። በሌላ በኩል ግን ባንዳንድ ጉዳዮች ላይ በቅርብ ሆነው ከሚከታተሉት እና የተሻለ [illegible] ትንተና ለማቅረብ እንችላለን የሚል እምነት አለን። ካፍንጫ ስር ያለውን ከማየት እራቅ ብሎ ያለውን ማየት እንደሚቀል ሁሉ፣እና በዚህ አንጻር ራቅ ማለታችን ሳይጠቅመን አልቀረም እንላለን። ለማንኛውም ግን ጉድለቶቻችንን ለማረምና በተሻለ መንገድ ለማገልገል ዝግጁ ነን።

እንባባት ይሆናል ብለን ሳንፈራ፣ ይኸው ከዚህ ቀጥሎ የኢትዮጵያን ልዩ ሁኔታ እንደታየን ለመተንተን ተነስተናል። ሰው የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም እንደሚባለው ነው። ባሁኑ ጊዜ ስላገሪቷ ሁኔታና ስለወደፊት አረማመዷ ሀሳብ መለዋወጥ በጣም ያስፈልጋል። እለቱ የተጣራ አስተሳሰብና አቅጣጫ እንዲገኝ የሚለፋበት እለት ነው። በጥብቅና በጥሞና መወያየት ያስፈልጋል።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ስለኃይለ ሥላሴ መገለበጥና ስለኢትዮጵያ ባላባታዊ ስርዐት ሁኔታ፣ስለጦር ኃይሎች ደርግ አስተሳሰብና አቋም፣ስላገሪቷ መደቦችና ስለ ሪቮሉሽን ጉዳይ፣ ስለ"ኢትዮጵያ ትቅደም"፣ባሁኑ ጊዜ ለንጠይቃቸው ስለሚገቡን ነገሮች ወዘተ... አንዳንድ አጣዳፊ የመሰሉንን ነጥቦች አንስተን ለመተንተን ሞክረናል። ስለኢትዮጵያ መደቦችና ስለኢትዮጵያ ሪቮሉሽን የተጻፈው ክፍል አጭር ከመሆኑ ሌላ፣ ምናልባት ቋንቋው አንባቢን ያስቸግር ይሆናል የሚል ስጋት አለን። ነገር ግን፣ ይህንን ክፍል ሆነ ሌላ ጽሁፉን አንባቢው ደጋግሞ እንዲያነብ፣ማስታወሻዎችን እንዲወስድና በቀረበው ሀሳብ ሁሉ ላይ የራሱን ግምት እንዲያበጅ፣ይህንም በጽሁፍ እንዲያስታውቀን አደራ እንላለን። እንደዚህ ዓይነቱን ጽሁፍ ሁለት ሶስት ጊዜ ሲያነቡት ነው ጥያቄዎችን ለመረዳትና ሌሎችንም ጥያቄዎች ለማቅረብ የሚቻለው።

አቅማችን የሚፈቅድ ቢሆን ኖሮ፣ስለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ በየሳምንቱ መጻፍ አስፈላጊ ነበር። በየእለቱ ባገሪቷ ፖለቲካ ውስጥ በሚታዩት ለውጦች ላይ አስተያየት መስጠት ተገቢ ነበር። ግን ሁኔታው ስላልፈቀደልን፣በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አሁን

በደርጉ ስለተወሰዱት አንዳንድ እርምጃዎች — ለምሳሌ የወታደሩ እርስ በርስ መታኮስ — ለመተቸት አይደለ አላገጠመንም::ጽሁፉ በጠቅላላው የሚመለከተው እስከመስከረም መጨረሻ ያለውን ሁኔታ ሲሆን፣በተለይ የሚያተኩረው ሰራዊቱ ስልጣን ከያዘበት ከሰኔ 26 ጀምሮ ኃይለ ሥላሴን እስከገለበጠበት እስከ መስከረም 2 ባለው ወቅት ላይ ነው::

አሁን ባለንበት ሰዓት ኢትዮጵያ ወዴት እንደምትራመድ በርግጥ ለማወቅ አልተቻለም::ወደወታደራዊ ፈላጭ ቆራጭና ምናልባትም ፋሺስታዊ አገዛዝ ይሁን ወደ ዲሞክራሲያዊ አናኗር፣ የትኛው ያገሪቱ የቅርብ የወደፊት እድል እንደሆነ ገና አልታወቀም:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ከተደራጁና ከታገሉ የፊተኛውን አስቀርተው በመጀመሪያ ደረጃ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ ከዚያም ወደ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽንና ወደ ህዝባዊት የኢትዮጵያ ሬፖብሊክ ሊያመሩ ይችላሉ::በፍጥነት ለመደራጀትና ለማደራጀት ካልተቻለ፣ለጥቂት የታሪክ ወቅትም ቢሆን፣ከኃይለ ስላሴ ፋሺስታዊ አገዛዝ ያላነሰ፣ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ይመጣ ይሆናል::አገሪቱ ወዴት እንደምትራመድ በሚመጡት ጥቂት ወራት ውስጥ ይጣራል::

ገራም ነፈሰ ቀን፣የኢትዮጵያ ተራማጆች የገዘው ግዴታ መደራጀትና ማደራጀት ነው::የተባሉት ተራማጆች የትንሽ ከበርቴውን ግለሰበኛነት፣ጉረኛነትና ወላዋይነት ካሸነፉ፣ዲሞክራሲያዊ አሰራርና ስነስርዐት ካከበሩ፣ባንድነት የማይደራጁበት ምክንያት የለም::ለማንኛውም ግን፣ ባገሪቱ ሁኔታ ትንተና ላይ መጀመሪያ መስማማት ስለሚያስፈልግ፣ የሀምሌን ታጠቅ በመከተል፣አሁን ይህኛውን ጽሁፍ አቅርበናል::

ፈለቀ እውነቱ

ጥቅምት፣1967





## የጦር ኃይሎች ደርግና የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ጉዳይ

### መግቢያ:—ተጉታች ኩዴታ

ቀዝቃዛ ረቮሉሽን፣ተጉታች ኩዴታ+፣ለስላሳ ረቮሉሽን፣የወራት ኩዴታ፣ ደግሞም ፀረ ፊውዳል ረቮሉሽን፣ ደምአልባ ረቮሉሽን.....::ባለፈው የካቲት 1966 በኢትዮጵያ የፈነዳው የሰፊው ህዝብ ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ያስከተለው የመንግስት ግልበጣ በውጭ አገር ተመልካቾች ዘንድ ብዙ ቅጽሎችን አትርፏል::በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን አትርፏል::አንዳንዶቹማ የኃይለ ስላሴን መገልበጥ እራሱ ከወራት በፊት እንደታቀደና ስለዚህም የወጣት ኢትዮጵያውያን መኮንኖችን ብልህነትና እርቆ አስተዋይነት የሚያሳይ ድርጊት አድርጎ እስከማቅረብ ደርሰዋል::ሁኔታው በርግጥም በጠቅላላው ወዳጅንም ሆነ ጠላትን ሳያስገርም አንዳልቀረ ግልጽ ነው::ምናልባትም አንዳንዶቹ እንደሚሉት ሁሉ በርግጥ የዚህ ዓይነቱ "ተጉታች" እንቅስቃሴ በማንኛውም አገር ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ሊሆን ይችላል::

ባለፈው ሀምሌ 15 ቀን በወጣው ታጠቅ —በአውሮፖ የኢት. ተማሪዎች የቲዎሪ መጽሄት — የየካቲት እንቅስቃሴ ከስድስት ወሮችም በኋላ ገና አላከተመም ሲል ነበር ትንተናውን የጀመረው::አሁንም እንደዚያው ማለት የግድ ሆኖብናል::ዛሬም እንቅስቃሴው ከተጀመረ ከስምንት ወሮች በኋላ ፈላጭ ቆራጩ ኃይለ ስላሴ ከስልጣን ከተባረረ ወዲያም፣ ሁኔታው ገና አላከተመም::ያገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ፣በተለይም የገጠሩ ሁኔታ ምንም ስላልተለወጠ እርሱን ሁሉ ለጊዜውወደጎን ትተን፣የህዝቡን ስሜትና ፍላጎት ብንመለከት አሁንም እንደዚያው ነው:: የባላባቱ ቀንደኞች መታሰርና የንጉሡ የራሱ መወገድ ምንም የሚታይና የሚጨበጥ ለውጥ ገና አላመጣም::ህዝቡ አሁንም "አንዳች ነገርን" ይጠባበቃል:: የመንግስት ስልጣን ጉዳይ እስካሁን ያለው በትልቅ ጥያቄ ምልክት ነው::ኢትዮጵያ ወዴት እንደምትራመድ በውነቱ ገና አልታወቀም::ለሁሉም ግልጽ አልሆነም:: የየካቲት እንቅስቃሴ አሁንም አላከተመም ማለት ነው::ታዲያ እዚህ ላይ የሚቀርበው ጥያቄ "ይህ ሁሉ እንዴት ሊሆን ቻለ" የሚለው ነው::ህዝባዊ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ስምንት ወራት አልፈውት ሳለ፣ እንዴት ነው እስከዛሬ የመንግስት ስልጣን ቁርጥ ባለ መንገድ ያልተያዘው::እንዴት ቢሆን ነው ሁኔታው እስተዛሬ ያልተደላደለው

የኢትዮጵያ ወታደር እርቆ አስተዋይ ሊሆን አይችልም ለማለት ሳይሆን፣የደርጉን ወይንም የመላ ሰራዊቱን "ብልህነት" መጥቀስ ለዚህ ጥያቄ መልስ አይሆንም::መልሱ የሚገኘው የኢትዮጵያን ህብረተ ሰብ መደቦች ሁኔታ በማየት ብቻ ነው:: የየካቲት እንቅስቃሴ ለገዥ መደቦች፣ማለትም ለቢሮ ከበርቴውና ለባላባት መደቦች፣በጣም

+ኩዴታ ማለት በጥቂቶች የሚደረግ ድንገተኛ የመንግስት ግልበጣ ማለት ነው

ድንገተኛ ነበር::እንደደራሽ የውሀ ሙላት ነበር::ኃይለ ስላሴና እነአከሊሉ እንዴ ቀን ህዝቡ እንደሚነሳባቸው ቢያውቁም፣ ያነሳሉ ስፋት እስከዚህ መተንፈሻ ፋታ የሚያሳጣቸው አለመሰላቸውም ነበር:: የቤር ከበርቴውን መደብ መሪዎች እነአከሊሉ ሀብተወልዱን እንተዋቸው፣ እነሬሱ ከአገለገሉት ውጭ የሆኑት ወዲያው እንቅስቃሴው እንደተጀመረ ነበርና:: በዚያ ሁኔታ፣ፀረ ረቮሉሽናዊ ምላሽን ሊያደራጁና ሊፈጽም ይችል የነበረው የባላባቱ መደብ ነበር::እነእንዳልካቸው—እስራተ ካሳ— አበይ አበበ፣የመደቡ መሪዎች ከቤር ከበርቴው ርዝራዥ ጋር ሆነው እስከሰኔ አጋማሽ ድረስ ይህንን ሞከረውት ነበር፣አልሆነላቸውም:: ሠራዊቱን ለመከፋፈልና ስልጣናቸውን ለማደላደል አልተሳካላቸውም::ሳይሆንላቸው የቀረበትም ዋናው ምክንያት የገዥ መደቦች ከሠራዊቱና ከፖሊሱ ከራሱ በስተቀር፣ ከዚህ ዘር በነሱ ላይ ከተነሳው ከጥንት የመጪና መሳሪያቸው ውጭ፣ በህብረተ ሰቡ ውስጥ የመደብ መሰርክዛቸው በጣም የመነመነ፣ደካማ ስለነበረና ስለሆነ ነው::በሌላ በኩል ደግሞ በከተማ ውስጥ ስለተዘጉ፣ይህንኑ ደካማ የገጠር መሰርክዛቸውን፣የዘቀተኛ ባላባቶች፣መደብ፣ነፍጠኛውን ለማዘጋጀት ከላይ እንደተባለው ሁሉ አዳል አልነበራቸውም::እንደእውነቱ ከሆነ፣ገና በመጋቢት 4 ባገሪቷ ያለው አድሃሪ ሀይል ሁሉ በንጉሡ ዙርያ በተሰበሰበበት ቀን፣የገዥ መደቦች ዋጋ ያለው ፀረ ረቮሉሽናዊ ምላሽ ሊያደራጁና ሊያከናውኑ የማይችሉ መሆናቸው ገለጽ ሆኖ ነበር::ሠራዊቱና ፖሊሱ ከጃቸው ካፈተለከ ወዲያ በምን አባታቸው የህዝቡን ቁጣ ይቋቋሙታል::ይህንን ሐቅ በጊዜው የተረዱ የባላባት መደብ አባሎች ገና እንደተጠየቁ በቶሎ እጃቸውን ለሠራዊቱ ሰጥተዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ፣የኃይለ ስላሴን ፊውዳላዊ ዙፋን ያነቃነቁት በመዉረሻም የፈነቀሉት ሀይሎች ራሳቸው የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ዝግጁ አልነበሩም::የየካቲት እንቅስቃሴ እነርሱንም ጭምር በድንገት ነበር የወረደባቸው ለማለት ይቻላል::ሰፊው ህዝብ፣ማለትም ገበሬው፣ወዛደሩ፣የተነሳው ሳይደራጅ ስለሆነ፣የታገለውም እንዲሁ ሳይደራጅ ስለሆነ ያም ሆነ አሁን የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ በፍጹም አይችልም ነበር::አሁንም አይችልም::እንግዲህ እነዚህን ሁለት ዋና የህብረተ ሰብ መደቦች ወደጉን ከተውናቸው፣የሚቀረው ሌላ ሀይል የንዑስ ከበርቴው፣ በተለይም በወታደሩ የተወከለው ክንፉ ነው::ከሁሉም ወደመንግስት ስልጣን ይቀርብ የነበረው፣የሚቀርበው፣የእንቅስቃሴው ዋና ተዋናይ ወታደሩም ለስልጣን የተዘጋጀ አልነበረም::እንዲያውም እራሱ በገዛ እርምጃዎቹ ዘር ገራ ሳይገባ አልቀረም::በየጊዜው በተነሳና ወደፊት በገፋ ቁጥር ፀረ ረቮሉሽንን በየደረጃው ቢጠብቅ እለመጣ ብሎታል::ስለዚህም እስከ ሰኔ ድረስ ሲያመነታ ቆይቶ ወደ መንግስት ስልጣን



ከተወጋ በኋላ አሁን ገና ኃይለ ስላሴን ገለበጠ የመንግስትን ስልጣን በርግጥም 'በህግ' መያዙን አስታወቀ::

ገን ነገሩ አሁንም ቢሆን መቸ አለቀ የገዥ መደቦች ስለተበታተኑ ፀረ ረቮሉሽን ሊያመጡ አልቻሉም፣በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስትን ሥልጣን ለመያዝ የተዘጋጀ መደብ ቁርቶ የመደብ ክፍልም አልነበረም::በኢትዮጵያ 'ተጉታች ኩዴታ' የተደረገው በዚህ ዓይነት ነው::እንግዲህ የሥልጣን ጉዳይ አሁንም ስላልተደላደለ፣የእንቅስቃሴው የፍጻሜ ድንበር ገና ስለማይታይ፣ሁሉም ነገር ይቀጥላል::ኢትዮጵያ ወዴት እንደምትጓዝ ገና ገለጽ አልሆነም::ህዝቡ አሁንም 'እንዳች ነገር'ይጠብቃል::

የየካቲትን ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ወደ'ተጉታች ኩዴታ'የለወጠው ዋናው ምክንያት የመንግስትን ስልጣን ከቁጥጥሮች የገዥ መደቦች ለመንጠቅ ዝግጁት ያደረገ መደብም ሆነ የህዝብ ክፍል አለመኖሩ ነበር::በሌላው ዓለምና በተለይም በአህጉራችን በአፍሪካ ወታደር መንግስትን ሲገለብጥ ጉዳዩ ቢበዛ ጥቂት ሳምንታት ብቻ ይፈጃ ነበር::ብጥር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ይደላደላል::የኢትዮጵያ ሁኔታ ልዩ የሆነውና 'ተጉታች ኩዴታ'አድናቆትን በውጭ ሰዎች ዘንድ ያተረፈውየኢትዮጵያ ህዝብ በፍጥረቱ ልዩ ስለሆነ አይደለም::በኢትዮጵያ የመደቦች ትግል የደረሰበት ደረጃ የተለየ ስለሆነ ብቻ ነው::

እውነት ነው፣የመንግስት ስልጣንን በማመለከተው በኩል የየካቲት እንቅስቃሴ 'ተጉታች'ሆኗል::ገን ይህ ተጉታችነት ድርጊቶች የሚከናወኑበትን ፍጥነት አይመለከትም::እንዲያውም ያገሪቷን ሁኔታ ለመከታተል አስቸጋሪ የሆነው፣ድርጊቶቹ የሚፈጸሙበት ፍጥነቱ ገራ የሚያጋባ ስለሆነ ነው::በተለይም ሠራዊቱ ስልጣኑን ከያዘበት ከሰኔ 22 ወዲህ በየእለቱ ከየለ ጉደለ አዳዲስ ነገሮች፣አዳዲስ እርምጃዎች ባገሪቷ የፖለቲካ ኑሮ ውስጥ ስለታዩና ስለተወሰዱ ሁኔታውን ለመከታተል አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል::

ሌላው ሁኔታውን በደንብ እንዳንከታተል የሚያስቸግረው ነገር የትክክለኛነት፣የቀጥተኛ አነጋገር፣የጥራት መጥፋት ነው::በዚህ ጽሁፍ በዚህ ነገር ላይ እንደገና እንመለስበታለን::ለጊዜው ገን ምን ማለታችን እንደሆነ ባጭሩ እናመለከት:: የጦር ሃይሎች ደርግ ከሰኔ 22 ወዲህ 'ማብራሪያ'፣'ገለጫ'፣ 'መግለጫ' እያለ ብዙ ጽሁፎችን በመንግስቱ ጋዜጦች እንዲወጡ አድርጓል::የመንግስቱ ጋዜጠኞችም በበኩላቸው ስለ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች መዐት ነገሮችን ጽፈዋል::እነዚህን በመንግስቱ ጋዜጦች የወጡትን ዋና ዋና ጽሁፎች ወስደን ብንመለከት፣ ብዙውን ጊዜ ምን ለማለት እንደፈለጉ ለመረዳት ያስቸግራል::ሌላው ቁርቶ የደርጉ የሀምሌ 2 አስራ ሶስት ነጥቦችና አሁን በቅርቡ

ኃይለ ሥላሴ እንደወደቀ የወጡት "ዓላማዎች"፣ማለትም በጣም ትልልቅ የፖለቲካ ውሳኔዎች ጥራት የላቸውም፡፡ብዙ ጥያቄዎችና ብዙ ትርጉሞች የሚያስከትሉ ናቸው፡፡አገሪቷ ገና ከፊውዳል ስርዐት ስላልጣጣች ሰው በጠቅላላው፣ማለትም የሚጽፈው ህዝብ፣በቀጥታና በጠራ አኳኋን መናገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ባለመገንዘቡ፣በዚያው በድሮ አማርኛ፣ እስከተቻለ ድረስ ለማለት የሚፈለገውን በገሃዱ ሳያስታውቅ ሸፋፍኖ ወደፊት መራመድ የሚቻል ይመስለዋል፡፡እንደነገሩ ዓረፍተ ነገር ግማሽ ገጽ የያዘ ሆኖ በአንዱ ጉዳይ ይጀምርና በሌላ ጉዳይ ይዘጋል፡፡

በተጨማሪም በኃይለ ሥላሴ ፊውዳል—ፋሺስት አገዛዝ ስር የንግግርና የመጻፍ ነጻነት ስላልነበረ ጠቅላላው ከተሜ ወሬዎችን የሚያገኘው አንዱ ሌላው የያዛትን ወሬም ሆነ የፈጠራትን "ዜና" በሚያካፍልበት ጊዜ ነበር፡፡ይህ ሁኔታ አሁንም፡አለ፡፡የጦር ሃይሎች ደርግም "የጠራ ሹሞችን" ለማስጠንቀቅ ደጋግሞ መግለጫ ማውጣት የግድ ሆኖበታል፡፡ብዙ ወሬ ይወራል፡፡አንዳንዴ ጊዜ በጣም ድራማ የለበሱ "ዜናዎች" ይሰራጫሉ፡፡በዚህ ሁኔታ፣እንኳንስ በውጭ አገር ያለ ሰው ቀርቶ በዚያው በቦታው ላይ ያለውም እውነቱን ከፈጠራው መለየት ስለሚያቅተው ይወናበዳል፡፡በዚህ ሁኔታ፣ሳይገባው ትንተና ለማድረግ የሚነሳ ሰው የግዱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በበኩላችን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የምንመሰረተው በርግጥ በሆኑ ነገሮችና ሁኔታዎች ላይ ነው፡፡እነሻለቃ አጥናፉ ሰኔ20 ቀን የነአክሊሉን መለቀቅ እንደጠየቁ እናውቃለን፡፡ይህ ተጨባጭ ነገር ነው፡፡በርግጥ ሰራዊቱን ሰብስበው በድምጽ ማጉያ አነጋገረውት እንደሆን ወይንም ተራ ወታደሩ ራሱ የሚወጠሩበትን ጥያቄ አቅርቦላቸው አሳፍሯቸው እንደሁ አናውቅም፡፡ብናውቅ ጥሩ ነበር፡፡ ለጊዜው ግን ለትንተናችን የመጀመሪያው ተጨባጭ ዜና ብቻ ይበቃናል፡፡

ሌላው የየካቲትን እንቅስቃሴ ዓይነተኛ የሚያደርገው ነገር የመሪ አስተሳሰብ መጥፋት ነው፡፡እስካሁን ድረስ በተካበረ አኳኋን የቀረበና የብዙሃን ተከታይነት ያገኘ ሃሳብ በግልጽ አልታየም፡፡ ይህም ነገር ላይ ከተጠቀሰው አለመዘ[illegible]ት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ይህን ያህልም ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ይሁንና ስለወደፊቱ አረማመዱ ሃሳብ ያቀረቡትን የነቁ የህዝብ ክፍሎች ብንመለከት በውነቱ በተጣራና በማያከራከር አኳኋን ከስራ ላይ ሊውል የሚችል አሳብ ያቀረበ አለ ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ በበኩሉ የአውሮፓ ማህበር ከመጋቢት ጀር ጀምሮ ያመለከተው የህዝቡን የመደራጀት አስፈላጊነት ነው፡፡አሁን ኃይለ ሥላሴ ከተገለበጠም ወዲያ ይህ ማህበር የሚጠይቀው ዋናው ነገር ይህንኑ ነው፡፡ከሁሉ አስቀድሞ ሰፊው ህዝብ መደራጀት አለበት፡፡ወታደሩ ፈቀደ አልፈቀደ፣



ህገ መንግስት ወጣ አልወጣ፣ህዝቡ የራሱን የፖለቲካና ህዝባዊ ድርጅቶች በፍጥነት ማቋቋም አለበት፡፡ያለድርጅቱ ህዝቡ ምንም አያገኝም፡፡

ያውሮፓው ማህበር አቋም ይህ ሲሆን ባገር ቤት ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን፣የሰራተኛው ማህበር ኢሰአማ፣በጠቅላላውም ባገሪቷ የሚገኘው የግራ ክንፍ "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን"፣"የጊዜያዊ የሞግዚት መንግስትን" ወዘተ...መፈጠር ደጋግሞ ጠይቋል፡፡አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፡፡ይሁንናም ይህ ውጤት አልሰጠም፡፡በነዚህ ነገሮች ላይ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንመለስባቸዋለን፡፡ እዚህ ላይ ለማመልከት የምንፈልገው ግን እስካሁን ድረስ የማያጠራጥር ሰፊ ተከታይነትን ያገኘ አቋም አለመቅረቡን ነው፡፡

"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውስ ልንባል እንችላለን፡፡አሁን ባለንበት ጊዜ ሠራዊቱ በመላ አገሪቷ በየአውራጃው "ኢትዮጵያ ትቅደም" "ለህዝብ እንዲገለጥ" በማድረግ ላይ ነው፡፡በጋዜጣው በየዕለቱ እንደሚጻፈውም ከሆነ፣የዚህ ወይንም የዚያኛው አውራጃ ህዝብ ለዚህ "ዓላማ" ተባባሪነቱን መግለጹ እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህ የተባባሪነት ገለጣ ከሰፊው ህዝብ ከራሱ የመጣ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ኃይለ ሥላሴ ስለተገለበጠ ህዝቡ መደሰቱ የማያጠራጥር ነገር ቢሆንም፣ከላይ እንዳልነው ህዝቡ ገና "እንዳች ነገርን" ይጠብቃል፡፡አሁን በየቦታው"በጭብጨባ" ተባባሪነቱን መግለጡ እውነቱን ሊሸፍንብን አይችልም፡፡"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው ዘር ዘር ባለህበት እርጋ እንዳይሆን ያሰጋል፡፡ የዚህ "ፍልስፍና"አመንጪዎች በመንግስት ስልጣን ደረጃ የታወቁትን እርምጃዎች ቢወስዱም፣ሰፊውን ጭሰኛ፣ወዛደር፣ሰፊውን ህዝብ ባለህበት እርጋ ማለት ቀጥለዋል፡፡በዚህ ሁኔታ፣እንደ ሃይለሥላሴ መንግስት ሁሉ በጉልበት አስፈራርቶ ለመያዝ ካልሆነ በስተቀር፣የተባለው "የኢትዮጵያ ትቅደም"ጥሪ ሰፊውን ህዝብ ሊያስከትል የሚችል "ፍልስፍና" እንዳልሆነ ወደፊት በበለጠ ገልጽ ይሆናል፡፡

በነዚህና በመሳሰሉት ነጥቦች ላይ እንደገና በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንመለስባቸዋለን፡፡አሁን ግን ለመጠቆም የምንፈልገው፣የኢትዮጵያ ሁኔታ አሁንም ያልተጣራ መሆኑን ነው፡፡አገሪቷ ወዴት እንደምትጓዝ ገና ግልጽ አልሆነም፡፡በዚህ ሁኔታ ካሉት አንዳንድ ጥያቄዎችን ለመመለስ መሞከር አለብን፡፡ምናልባት ሁኔታውን የበለጠ ሊያብራሩ ይችሉ ይሆናል፣ምናልባትም ትክክለኛውን አቅጣጫ ያመለክቱ ይሆናል፡፡ለማንኛውም ተስፋችን ይህ ነው፡፡

እንግዲህ፣በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በቅድሚያ ለመመለስ የምንሞክራቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡ኃይለ ሥላሴ ከተገለበጠ ወዲህ የኢትዮጵያ የፊውዳሊዝም ሁኔታ

ከምን ላይ ደርሷል? የጦር ኃይሎች ደርግ በርግጥ የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው? የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ጉዳይ ዛሬ እንዴት መታየት አለበት የሚቀጥለውስ አዝማሚያ ምንድን ነው?

ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው ሁኔታዎች ምክንያት፣ይህም ጽሁፍ እንደእውነቱ ከሆነ የተሟላ ሊሆን አይችልም:: የተሟላ ጥናት መምጣት የነበረበት በቦታው ላይ ከሚገኙ ምሁራን ነበር፣ግን እነሱ ምናልባት በየእለቱ ትግል ተወጥረው በመያዛቸው ለዚህ ዓይነቱ አስፈላጊነቱ ለማይካድ ስራ ጊዜ አላገኙ ይሆናል::ከነሀሴ ወር ወዲህ "የሰፊው ህዝብ ድምጽ" የሚባል የሳምንት ጋዜጣ፣ባዲሳባ የሚታተም፣ሁኔታውን ለመከታተልና ሀሳቦችን ለማቅረብ በመሞከር ላይ ነው::ይህ ጋዜጣ ወደፊት በነዚህ ጥያቄዎች ላይ በማተኮር ጥሩ ጥናቶችን እንደሚያወጣ ተስፋ እናደርጋለን::

በተረፈ እንግዲህ አንባቢ በትእግስትና በጥሞና ሙከራችንን እንዲከታተልልን እንጋብዛለን::ደግሞም ለማንኛውም ነገር፣አንባቢው ራሱ ትንተናችንን ከሆነው ሁሉ ጋር ለማመሳሰል ይመቸው ዘንድ በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ "ድርጊቶች ከነጊዜያቸው" የሚለውን መረጃ ሰጥተናል::

## 1. የኃይለ ስላሴ መገልበጥና የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ስርዐት ሁኔታ

እነዚህ መስመሮች የሚጻፉት ኃይለ ስላሴ ከስልጣን ከተወገደ ከወር በኋላ ነው::በዚህ ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ የንጉሡን መውደቅ በመቃወም የተነሳ ኃይል አልታየም:: እንዳለካቸው የወደቀ ለት በሀምሌ 15 የወጣው ታጠቅ፣ከዚህ በላይ የጠቀስነው፣የኢትዮጵያ ገበሬ ለንጉሡም ሆነ ለዘውዱ ደንታ የለውም ብሎ ነበር::የገጠሩ ዝቅተኛ ባላባት እንኳንስ "ለንጉስህ" ብሎ ይቅርና "ለሃይማኖትህ" እንኳ ቢል ገበሬው እንደማይከተለው ታጠቅ አመልክቶ ነበር::አሁን ንጉሡ ከወደቀ በኋላ፣መላው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ "እሰይ"አለ እንጂ፣የገጠሩም ባላባት ሆነ የከተማው ከበርቴ የንጉሡን መውደቅ በግሃድ ለመቃወም ፈጽሞ አልደፈረም::ንጉስና ዘውዱ ከጠፉ የኢትዮጵያ ህዝቦች እርስ በርስ ይፋጃሉ የሚለውን ማወናበጃ ከንቱነት መቃም ከጀመርን ብዙ ዓመታት አለፈው፣ይኸው ዛሬ እርግጠኛ ከንቱነቱ በግልጽ ታይቷል::

በኃይለ ስላሴ መውደቅ ያልተደሰቱ የገዥ መደቦችና ኢምፔሪያሊስቶች ብቻ ናቸው::ገዥ መደቦች ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ሁሉ፣በቶሎ ለመደራጀትና ፀረረቮሉሽንን ለማጠናከር፣በዚህም እንኳን ንጉሡንና መደባቸውን ከስልጣን ለማቆየት እድል አላገኙም::ኢምፔሪያሊዝም በበኩሉ እስካሁን በእንቅስቃሴው ላይ ሙሉ ቁጥጥር ያገኘ አይመስልም፣ከንግዲህ ግን በተንኮልና በሴራ ተጽዕኖውን መልሶ ለማስፈር እንደሚፍጨረጨር



ምንም ጥርጥር የለውም::ለማንኛውም ግን የኢትዮጵያ አድሃሪ ኃይሎችና የምእራብ ኢምፔሪያሊዝም በኃይለ ሥላሴ መውደቅ ፈጽሞ ደስ አላላቸውም::ይህ ግልጽ ነገር ነው::እንኳንስ እነዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ቀርተው፣ባፍሪካ ህዝብ ላይ የተጫኑት በርከት ያሉ ፀረ ህዝብ ገዥዎች በሰውየው መገልበጥ ደስ እንዳልተሰኙ በይፋ ገልጠዋል:: ይሁን እንጂ በኃይለ ስላሴ መገልበጥ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንዱ ትልቅ ድል ማግኘታቸው መታወቅ አለበት::

ከየካቲት እንቅስቃሴ "ዋጉታቸነት" የተነሳ፣የኃይለ ሥላሴ መውደቅ እንደቀላል ነገር ታለፈ::ምንም እንኳ የውጭ ጋዜጦች፣ራዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች፣የኢትዮጵያ ጋዜጦችም ጭምር፣የንጉሡን መገልበጥ በትላቅ ፊደላት ቢጽፉና በትላልቅ ስዕሎች ቢያሳዩም፣ድርጊቱ ምንም ያህል አላስተጋባም::ሰውን፣በተለይም በጥሞና የኢትዮጵያን ሁኔታ የሚከታተለውን ተመልካች ምንም ያህል አላስደነቀም:: ተመልካችን ይበልጡን ያስደነቀው የንጉሡ ተራ ሌባና አጭበርባሪ ሆኖ መገኘት ነው::

ይሁንናም፣ ኃይለ ስላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሊፋቅ የማይችል ፀረ ህዝብ ማህተሙን አስፍሮ መሄዱ ለሁሉም ሰው ግልጽ መሆን አለበት::ከክፍለ ዘመን ግማሽ በላይ የኢትዮጵያን ህዝቦች በድንቁርና፣በበሽታ፣በድህነት ሰንሰለት ተብትቦ በፀረ ህዝብ አመጽ ገዝቷል::የባላባታዊው መደብ ዋና መሪና ባፍሪካ ምድርም ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የጽዮኒዝም ዋና አገልጋይ በመሆኑ ባንድ በኩል በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ፋሺስታዊ ጭቆናን ሲያስፍን፣በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቷን በእጅ አዙር ቅኝነት ለኢምፔሪያሊስቶች አሳልፎ የሸጠ ሰው ነው::አሁን ከስልጣን በወረደበት ወቅት ቀኝ ገዥዎች ካፍሪካ ሲወጡ ከኋላቸው ከተውት የድህነት፣የድንቁርናና የበሽታ ቅርስ የባሰ፣ለህሊና የሚቀፍ ሁኔታ ከኋላው አስቀርቶ መሄዱ ነው::ኃይለ ስላሴ ለኢትዮጵያ ህዝቦች አውርሶ የሚያልፈው ነገር ያገሪቷን ከአፍሪካ ምድር መጨረሻ ቦታ መያዝ ነው::በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የማይፋቅ ጉድፍ ጥሎ አልፏል የምንለውና የርሱም መገልበጥ እንደትልቅ ድል መታየት አለበት የምንለው በዚህ ምክንያት ነው::

እንግዲህ የኢትዮጵያ ባላባታዊ ስርዐት ቁንጮ የሆነው ንጉሠ ነገሥቱ ከወደቀ በኋላ፣ስርዐቱ ራሱ ዛሬ ከምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

ኃይለ ስላሴ ቢወድቅም የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ስርዐት በፍፁም ከመሰረቱ አልተነካም::የኃይለ ስላሴ መውደቅና የትላልቅ ባላባቶች ተይዞ መታሰር የሚያመለክተው በመንግስት ስልጣን ደረጃ ገዥ መደቦች መገለላቸውን ብቻ ነው::ኢኮኖሚያዊና ህብረተ ሰባዊ መሰረታቸው ፈጽሞ አልተነካም::ባላባታዊ ስርዐትና ኢምፔሪያሊዝም

የጫኑት ያገዛዝ መኪናም መሪያቹን፣ዋናዎቹን አንቀሳቃሾቹን አጧ እንጂ አልተሰባበረም፤ በቦታው አለ፡፡ሌላው ቀርቶ፣የንጉሡና የነአክሊሉ የነበረው ዋና መሳሪያ የነበረው የፀጥታ ድርጅት አሁንም በቦታው አለ፡፡ የፖርቱጋል ወታደሮች ያህል እንኳ የኢትዮጵያ ወታደሮች ይህንን ድርጅት ፈጽሞ አልነኩትም፡፡ባጭሩ፣ኃይለ ሥላሴ ቢሄዱም ስርዐቱ ከቦታው አልተንቀሳቀሰም፡፡ይህንን ሁኔታ ቀረብ ብለን ማየት ያስፈልገናል፡፡ከዚያ በፊት ግን አንዳንድ ነገሮችን እናመልከት፡፡ የተሳለቀ ባላባቶች መደብ በመንግስት ስልጣን ደረጃ ተደምስሶአል እንላለን፡ ነገር ግን ይህም እንኳ ቢሆን እስከተከከለኛው ፍጻሜ ገና አልተገፋበትም፡፡አንደኛ ነገር የታወቁ የጥንት ባላባቶች አሁንም በብዛት ነፃ ሁነው ይታያሉ፡፡እነመንገሻ ስዩም፣እነፍቅረ ሥላሴ ሀብተማርያም/የወለጋው/ና ሌሎችም ከቦታቸው ያልተነቃነቁ የባላባታዊ አገዛዝ ተጨባጭ ምልክቶች አሁንም አሉ፡፡ ሁለተኛ ነገር፣ኃይለ ሥላሴን ያሽቀነጠረው ሠራዊት ሌላ ንጉሥ በቦታው እንዲተካ ጠይቋል፡፡በኢትዮጵያ የኃይለ ሥላሴ ዘውድ የውርደታችንና የጭቆናችን ምልክት እንጂ፣ፍጹም 'የአንድነት ምልክት' እንዳልሆነ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እያወቀው፣አልጋ ወራሹን ለማንገስ ጥሪ ማድረግ ታጥቦ ጭቃ ነው፡፡ለማንኛውም ግን የተሳለቀ ባላባቶች መደብ ሙሉ በሙሉ አለመደምሰሱ፣ወይንም የንቅስቃሴው 'ጊዜያዊ' መሪ የሆነው ወታደር መደቡ እንዲደመሰስ አለመፈለጉን፣ወይንም የነገሩ አስፈላጊነት ፈጽሞ እንዳልታየው ያመለክታል፡፡

እሺ፡፡ የተሳለቀ ባላባቶች መደብ በቀላ ጉደል ከስልጣን ተገለለ፣በቀላ ጉደል በዚህ ደረጃ ተደመሰሰ እንበል፡፡ይሁን እንጂ የባላባታዊ ስርዐት ኢኮኖሚያዊና ህብረተ ሰባዊ መሰረት አሁንም አልተነካም፡፡መጀመሪያ ነገር፣የመሬት ጉዳይ ተደጋግሞ ይነሳ እንጂ የመሬት ይዞታን ለመጀመር አንዳችም እርምጃ አልተወሰደም፡፡ እንዲያውም የጦር ኃይሎች ደርግ ጭሰኛውን 'እንደቀደመው ቀጥል!' በማለት ላይ ነው፡፡ ለባለመሬቱም ለመንግስትም የሚፈለገብህን ሁሉ ክፈል ይለዋል፡፡በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' በሚሰበክበት ጊዜ፣ጭሰኛውም 'ጌታውን' እንዲፈጽም ይነገረዋል፡፡ የባላባታዊው ስርዐት ኢኮኖሚያዊ መሰረት አልተነካም፡፡ሁለተኛ ነገር፣በዚህ ኢኮኖሚያዊ መሰረት አማካይነት ዘጠና በመቶውን ያህል የኢትዮጵያን አርሶ አደር የሚያራቀቀው የዘቀተኛ ባላባቶች መደብ፣ያ ከመጋቢት 4 ቀን ጀምሮ ወደኃይለ ሥላሴ ይጎርፍ የነበረው ዘራፊ ሁሉ አሁንም በቦታው አለ፡፡እንዲያውም ከመንግስቱ ጋዜጦች በቀላሉ ለማየት እንደሚቻለው፣ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ለሚለው ነገር ዋና ሰባኪ ባንዳንድ ቦታዎች ይኸው መደብ ሆኗል!! የባላባታዊ አገዛዝ ህብረተሰባዊ መሰረት አሁንም አልተነካም ማለት ነው፡፡



ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው ሁሉ፣የዘቀተኛ ባላባቶችን መደብ ከሶስት ክፍሉ ለማየት ይቻላል፡፡— የሰሜኑ ክፍለአገር፣የደቡቡ ተወላጅና የደቡቡ ነፍጠኛ፡፡ የጦር ኃይሎች እንቅስቃሴና የጦር ኃይሎች ደርግ በዚህ መደብ ላይ እስካሁን ምንም እርምጃ አልወሰደም፡፡ባሁኑ ጊዜ ዋና አብሮአቸው የተሰለፈው የገጠር ኃይል 'ኢትዮጵያ ትቅደም'ን የሚሰብኩላቸውም እርሱ ነው፡፡ዞሮ ዞሮም አሁን ስልጣኑን የያዘው የንዑስ ከበርቴው አንዱ ክንፍ ከዚህ መደብ ጋር በመሻረክ ጭሰኛውን ይጨቁን ይሆናል፡፡ ይህ ወደፊት ይበልጡኑ ግልጽ እየሆነ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም፡፡ወጣም ወረደ፣ለሰፊው ህዝብ ጥቅምና ደህንነት፣ለብሄራዊ ዲሞክራቲክ ረቮሉሽን የሚታገሉት ሃይሎች ሁሉ መቼውንም ቢሆን የዚህን የገጠር ባላባታዊ አገዛዝ ህብረተ ሰባዊ መሠረት በቦታው መገኘት መርሳት የለባቸውም፡፡

በመንግስት ስልጣን ደረጃ ታላላቅ ባላባቶችና ዋነኞቹ የቢሮ ከበርቴዎች ቢገለሉም፣ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በመሻረክ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ የጫኑት የመንግስት መኪና አሁንም እንዳለ ነው፡፡ የባላባታዊው ስርዐት ዋና ፀረህዝብ መሳሪያ የሆነው 'የፀጥታ ድርጅት' አሁንም እንዳለ ነው፡፡ከተማና ገጠርን ተበትበው እንደሸረሪት ድር የያዙት ዘራፊዎችና ጨቋኞች አሁንም አሉ፡፡ከቦታቸው አልተንቀሳቀሱም፡፡ የመስፍን ወ/ማርያምን የቀልድ ምክር በመከተል 'ግዛት' በማለት ፈንታ 'ክፍለ አገር' 'አስተዳደር' ወዘተ. ስለተባለ ለሰፊው ህዝብ ምንም ለውጥ አያመጣም፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገና ከዚህ በታች እንመለስበታለን፡፡ግን ካሁኑ መታወቅ ያለበት፣እንደእውነቱ ከሆነ፣ኃይለ ሥላሴ ቢገለበጥም የባላባታዊው ስርዐት መሰረት እስካሁን አለመነካቱ ነው፡፡

ከዚህ በታች የጦር ሃይሎችን ደርግ አረማመድ በሰፊው ለማየት እንሞክራለን፡፡እስከዚያ ድረስ ግን አንዳንዱ ነጥቦችን ካሁኑ ለመሰንዘር እንወዳለን — የጦር ሃይሎች ደርግ እስካሁን በተያዙት ሰዎችና በንጉሡም ላይ ያቀረባቸው ክሶች 'በስልጣን መባለግ'ና 'ያላግባብ መበልጸግ' ነው፡፡/የወሎን ረሃብ ጉዳይ ለጊዜው ወደጎን እንተወዋለን፡፡/እንግዲህ እዚህ ላይ ሁለት ጥያቄዎችን ለማቅረብ ይቻላል፡፡አንደኛ እነዚህን ሁለት የክስ ነጥቦች በሚመለከተው በኩል፣ሊከሰሱ የሚገባቸው አሁን የተያዙት ሰዎች ብቻ ናቸውን? ከወረዳ ዳኛ እስከ ጠቅላይ ገዥ፣ከፀሀፊ እስከ ሚኒስትር የመንግስቱን መኪና ከዳር እስከዳር በሚያንቀሳቅሱት ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር 'በስልጣን የባለገ'ና 'ያላግባብ የከበረ'ቀልቶ የለም ወይ? ገደቡ የት ላይ ነው?

እዚህ ላይ አንዱ ማስጠንቀቂያ፡፡እነዚያ የተያዙት ለምን

ተያዙ ማለታችን አይደለም፡፡ለማሳየት የምንፈልገው፣ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ የጫኑት የመንግስት መዋቅር እስካልተሰባበረ ድረስ ባላባታዊ አገዛዝ ተደምስሶ ለማለት እንደማይቻልና ደግሞም ሠራዊቱ አሁንም ሆነ ወደፊት ከትልቅ ቀራኔ ውስጥ እንደሚወድቅ ለማመልከት ያህል ነው፡፡

ሁለተኛ ጥያቄ፡- እንደሚታወቀው፣ የጦር ሃይሎች ደርግ ያንበሳ አውቶቡስንና የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ እንዲሁም በጎ አድራጎትን የመንግስት ሀብት አድርጎቸዋል፡፡ሌሎቸስ ያሏንቶች ከርከር የህዝብ ሀብት መሆን የሚገባቸው የንግድ ድርጅቶች የሉም ወይ? ካሉ ለምን እስካሁን አልተነኩም?

እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች ያቀረብነው፣ የጦር ሃይሎች ደርግ በባላባታዊው ስርዐት መሪዎች ላይ እንጂ በስርዐቱ ላይ አለመነሳቱን ለማመልከት ሲሆን፣በፍጥረቱም ያሁኑን ወታደራዊ እንቅስቃሴ የመሰለ እንቅስቃሴ ባላባታዊውን ስርዐት ለመደምሰስ እንደማይችል ለማመልከት ነው፡፡በስርዐቱ ላይ ተነስቶ እርሱን በመደምሰስ አዲስ ስርዐት ለመገንባት የሚችለው ሰፊው ህዝብ ብቻ ነው፡፡ይህም ደግሞ ይዋል ይደር እንጂ መምጣቱ የማይቀር ነው፡፡የታሪክ ግዴታ ነው፡፡

እንግዲህ እናጠቃልል፡፡የኃይለ ስላሴ መንግስት በመጨረሻ መሳሪያዎቹ የኢትዮጵያን ህዝቦች ከግማሽ ክፍለዘመን በላይ በአመጽ ከገዛ በኋላ አሁን ወድቋል፡፡ይህንን የመሰለ ፀረ ህዝብ አገዛዝ ሁሉ መውደቁ የማይቀር መሆኑንና አወዳደቁም የማያምር መሆኑን በበኩላችን ዓይነ ልሳናችን ከተከፈተ ጀምሮ ተናግረናል፡፡ይህ ደርሶ በማየታችን ደስታችን ከፍ ያለ ነው፡፡ይሁን እንጂ፣ ባላባታዊ አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝም ከኃይለ ስላሴ ጋር አልወደቁም፡፡አሁን የመንግስት ስልጣን የያዘው የንዑስ ከበርቴው ክፍል ለነዚህ ዋና የኢትዮጲያ ህዝብ ጠላቶች መውደቂያ ጥርጊያ ጎዳናውን ያዘጋጅ እንደሆነ፣ወይንም እርሱም የጸረ ህዝብ ሀይሎችን አድሀሪ ጎዳና እራሱ ይወስድ እንደሁ በቀርቡ ይታያል፡፡ያም ሆነ ይህ፣ ለኢትዮጲያ ሰፊ ህዝብና ለዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ሁሉ ሳንታከት የምናቀርበው ጥሪ "ተደራጁ" ነው፡፡ያለ ድርጅት ህዝብ ምንም አያገኝም ፡፡

## 2. የጦር ሃይሎች አቀናባሪ ደርግ ሥራዎችና አቋም፡፡

የየካቲቱን እንቅስቃሴ መጣይ ገዥ መደቦች አልተረዱትም ነበር፡፡በተለይም ንጉሡና እነእንዳልካቸው መኮንን ሁኔታውን በፍጹም አልተረዱትም ነበር፡፡ከዚህ በላይ እንደተባለው ሁሉ፣እንዳልካቸው መኮንን ስልጣንን ከያዘበት ወቅት ጀምሮ እስከወደቀበት ቀን ድረስ ፀረ ረቮሉሽንን ለማዘጋጀት ሞክሯል፡፡በተለይም በሚያዝያ ወር



"በከፍተኛ የፀጥታ ኮሚሽን" አማካይነት በሰርቶ አደሩ ህዝብ ላይ ፀረረቮሉሽናዊ ጥቃ ናን ካሰፈረና ሠራዊቱንም ለመከፋፈል ከሞከረ በኋላ፣በወሩ መጨረሻ ገደም የልብ ልብ ተሰምቶት እንደነበር ገልጽ ነው፡፡ለዚህ ምስክር በሚያዝያ 27 የነፃነት በዓል በሚከበርበት ቀን ንጉሡ እንዲያነበው የተሰጠውንና ያነበበውን ዲስኩር ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ቀን ኃይለ ሥላሴ ያሰማው "መሪ ቃል" የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ይዟል፡-

> "የህዝባችንን ችግር ለመወጣትና የወደፊት እድሉንም ለማሳመር በልዩ ልዩ ዘዴ በዚህ አኳኋን በምንጣጣርበት ጊዜ መሻሻሉና መሸጋገሩ በሰላም እንዳይፈጸም የደም መፋሰስና ሁከት እንዲፈጠር የሚሰሩ በሿዐዳን የተደገፉ ብዙ እጆች ገብተው በነዚህ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር በማድረግ፣የመንፈስ እረፍትና ፀጥታ በአገሩ ውስጥ እንዳይኖር በማድረግ በልዩ ልዩ ክፍሎች የተፈጸሙት ሁከቶች ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአገሪቱም በሁሉም ረገድ ያስከተለው ጉዳት እጅግ ከፍ ያለና ኢትዮጵያም በሰላምና በፀጥታ እድገቷንና መሻሻሏን የምትፈጽም አገር ነች በማለት በዓለም ላይ የነበራትን እምነትና ስም ለማሳጣት አድርጎ ለአገራችን ለኢኮኖሚ እድገትና ልማቱ የሚረዱትን የወዳጅ አገሮች እጅ ወደኋላ እንዳይል የሚያሰጋ ሆኗል፡፡... የኢትዮጵያ ህዝብ፣ከጦር ወታደሩና ከፀጥታ አስከባሪው ጋር በመተባበር ሁከት ፈጣሪዎችን *እንዲቆጣጠርና እንዲደመስስ ማድረግ ብሄራዊ ግዴታው መሆኑን መዘንጋት የለበትም*..."
> /ሥርዝ የተጨመረ/

ይህ የሚያዝያ 27 የኃይለ ስላሴ ዲስኩር ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡መጀመሪያ ነገር፣በዚህ ወቅት፣በተሳለቀ ባላባቶች መደብና የቢሮው ከበርቴው መደብ ርዝራዥ፣በእንዳልካቸው መሪነት በንጉሡ ዙሪያ ከተሰበሰበ በኋላ የህዝቡን ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ "ለመደምሰስ" ተስፋ አድርጎ ነበር፡፡በሠራዊቱ ውስጥ እንዳልካቸውና ሲ አይ ኤ ይሠሩት የነበረው ሴራ ውጤት የሰጠ መስሏቸው ነበር፡፡ግን በሰኔ ወር የተከተለው የሠራዊቱ እንቅስቃሴ በኋላ እንዳሳየው ይህ ሁሉ ተስፋ የህልም እንጀራ ሆኖአል፡፡ሁለተኛው፣ከዲስኩሩ የሚታየው ነገር በገዥ መደቦች ውስጥ በዚያን ጊዜ ስለህዝቡ የነበረው የግምት ስህተተኛነት ነው፡፡ኃይለ ስላሴ በዚያ ወቅት ያለቀለት ሰው እንደነበር እነእንዳልካቸው አልተገነዘቡም፡፡ የገዥ መደቦችን ከውድቀት የሚያድን የመጨረሻው መጠለያ መስሏቸዋል፡፡ይህም በዚያን ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንደ ነበሩ ያሳያል፡፡

ይሁንናም፣ከላይ እንደተባለው ሁሉ፣ገዥ መደቦች የሚረባቸውን ፀረረቮሉሽን ሰፋ ባለ አኳኋን ለማዘጋጀት ሳይችሉ እስከ ሰኔ ወር ቆዩ

ተዋለ፡፡ሰኔ 19 ቀን በኃይለ ስላሴ ሊቀ መንበርነት የዘውዱ ምክር ቤትና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባንድነት ተሰብስበው "አገሪቱን ስለሚመለከቱ ታላላቅ ጉዳዮች ላይ"ሁለት ሰዓት የፈጀ ውይይት ያደርጋሉ፡፡እነዚህ "ታላላቅ ጉዳዮች" የትኞቹ እንደሆኑ በመንግስቱ ጋዜጦች አልተነገረም፡፡የተወሰኑ ነገሮች እንዳሉና ውሳኔያቹ የትኞቹ እንደሆኑ አልተነገረም፡፡ነገር ግን፤ይህንን "ታላቅ"ስብሰባ ከተከተሉት እርምጃዎችና ተቾቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ሁሉ፤የውይይት ዋና አርእስት የሰፊውን ህዝብ እንቅስቃሴ በምን ዘዴ ለመደምሰስ ይቻላል የሚለው ሳይሆን አልቀረም፡፡ለማንኛውም በማግስቱ በሻለቃ አድማሴ መሪነት ስምንት መማክርት ወደአራተኛ ክፍለጦር ሄደው የታሰሩትን ሚኒስቴሮች መለቀቅ ይጠይቃሉ፡፡ሰኔ 21 ቀን የአዲስ አበባ አርኘላን ማረፊያ፤ራዲዮ ጣቢያዎችና የከተማው ዋና ዋና ቦታዎች በሠራዊቱ ይያዛሉ፡፡ከዚህ ቀን ወዲያ ሠራዊቱ ትላልቅ ባላባቶችን፤መሳፍንትንና ታላላቅ የቢሮ ከበርቴዎችን አንዱ በአንዱ መለቀም ይጀምራል፡፡ይህ እንግዲህ ያዲሱ የጦር ሃይሎች ደርግ የመጀመሪያ ድርጊት መሆኑ ነው፡፡

የጦር ሃይሎች ደርግ እውነተኛውን የመንግስት ሥልጣን የያዘው በሰኔ 26 ቀን ከንጉሡ ፊት ቀርቦ የታወቁትን አምስት ጥያቄዎችን አቅርቦ ንጉሡን ሲያስገድዱና በኋላም በሀምሌ 2 ቀን የታወቁትን 13 ነጥቦችን ሲያወጣ ነበር፡፡ከሠራዊቱ ማመንታትና የሚፈልገውን አለማወቅ የተነሳ፤ ይህ የመንግስት ስልጣን አያያዝ ቁርጥ ያለ አልነበረም፡፡መጀመሪያ፤ሰኔ 26 ቀን ለንጉሡ ባቀረባቸው ነጥቦች ውስጥ ደርጉ "ከመንግሥቱ ባለስልጣኖች ጋር የቀርብ ግንኙነት እንዲያደርግ" ከንጉሡ ፈቃድ ይጠይቃል፡፡በሀምሌ 2 ባወጣው 13 ነጥቦች ደግሞ ትንሽ ከዚህ ጠንከር ይልና "የሚያቀርባቸውና የሚያስፈጽማቸው" ያገር ጉዳዮች እንዳሉ ይገልጻል፡፡ሆኖም፤የወታደሩ የሀምሌ የሥልጣን አያያዝ ቁርጥ ነገር አልነበረም፡፡ይህም የሆነው ሠራዊቱ ምን እንደሚፈልግና እንዴት እንደሚራመድ እራሱ የማያውቅ ስለነበረ ነው፡፡ይህ የሀምሌ ሁኔታ ሲሆን፤አሁንም ኃይለ ስላሴ ከወደቀ በኋላ ሠራዊቱ —ደርጉ— መንግስትን ሥልጣን የያዘበት አኳኋን የተጣራ አይደለም፡፡በኛ አስተያየት፤አሁንም ቢሆንደርጉ የሚፈልገውን በተጣራ አኳኋን አያውቀውም፡፡ይህንን ለመረዳት ደርጉ የወሰዳቸውን እርምጃዎችና በየጊዜው የጻፋቸውን ነገሮች ማመሳሰልና ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ለዚሁም እንደሚከተለው መራመድ ይቻላል፡፡ መጀመሪያ፤ደርጉ ለንጉሡ የነበረው አቋም ምን ነበር? ደርጉ 'ህዝቡ' የሚለው ማንን ነው? ደርጉ የኢትዮጵያን "አንድነት" እንዴት ያየዋል? ደግሞስ "የህዝብን ድምጽ" እንዴት ተከተለ?በተለይም ያገሪቱ አጣዳፊ ጥያቄ ከሆኑት ውስጥ የኤርትራን ጉዳይ እንዴት ይመለከተዋል?በመጨረሻም፤የደርጉ "ዓላማዎች"ምንድንናቸው? "ኢትዮጵያ ትቅደም"ምን ይዘት አለው?



ከሰኔ 22 ጀምሮ የጦር ሃይሎች ደርግ የወሰዳቸውን እርምጃዎችና በጋዜጦች ያሰፈራቸውን ጽሁፎች ብንመለከት፤ እንዳቸም የተቀናበረና አስቀድሞ በጥብቅ ታስቦበት በፕሮግራም መልክ የተዘጋጀ ነገር እንደሌለ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አሁንም ቢሆን፤ኃይለ ስላሴ ከተገለበጠ በኋላ፤ደርጉ ምንም ዓይነት የተጣራ ፕሮግራም የለውም፡፡"የደርጉ ዓላማዎች" የሚለውን ድርድር እንመለከታለን፤ይሁን እንጂ አሁን ደርጉ በመስከረም መጨረሻ የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚያሳዩት ታስቦበት፤ተቀናብሮ፤በፕሮግራም መልክ የወጣ ወይንም የተዘጋጀ ነገር እንደሌለ ነው፡፡

ወታደሩ በሰኔ 22 እንደገና በፖለቲካ መድረክ ላይ ብቅ በሚልበት ጊዜ ምን እንደሚፈልግ በግልጽ የማያውቅ እንደነበረ ከሚያሳዩት ነገሮች አንዱ ለንጉሡ የነበረው አቀራረብ ነበር፡፡ከንጉሡ ፊት ቀርበው የደርጉ ወኪሎች የተናገሩትን ሁሉ እዚህ ላይ ለመዘርዘር የማይመች ሆኖ ነው እንጂ፤ደርጉ ከአነጋገሩ በርግጥም ለንጉሠ ነገስቱ "ታማኝነት" እንደነበረው ምንም አያጠራጥርም፡፡ይህ"ታማኝነት" የጥንቱ ዓይነት የንጉሡ መሳሪያነት አይደለም፤ይህ እውነት ነው፡፡ደርጉ ያኔ "ታማኝነት" ሲል ኃይለ ስላሴን እንነካም ማለቱ ብቻ ነበር፡፡ደርጉ በሰኔ 23፤በሰኔ25፤በሰኔ 26 በተናገራቸውና በጋዜጣ በሰፈሩት ቃሎች ሁሉ "ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነቱን" በደንብ ገልጿል፡፡በሰኔ 27 በአዲስ ዘመን "ከጦር ኃይሎች የተሰጠ መግለጫ" የሚለው ውስጥ የሚከተለው ሰፍሯል፡፡—

> "የጦር ኃይሎች፤ይኸውም የምድር ጦር፤የአየር ሃይል፤የባህር ሃይል፤የክብር ዘበኛ፤የወህኒ ቤት ፖሊስ ሠራዊትና የብሄራዊ ጦር አባሎች፤በጠቅላላው የአሁኑን ወታደራዊ ንቅናቄ የፈጠሩት ሁሉ፤ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጡ እንደመሆናቸው መጠን፤በኢትዮጵያዊነት ስሜት የተቃጠሉ፤ለኢትዮጵያ ህዝብና ለንጉሠ ነገስታቸው ደህንነት እጅግ በጣም የሚያስቡና የሚጨነቁ የሚሰሩትም ስራ ሁሉ በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ላይ የተመሰረተ መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲረዳልንና የዕለት ሥራውን በረጋ መንፈስ እንዲያከናውን አጥብቀን አደራ እንላለን፡፡"/ሥርዝ የተጨመረ/

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከሚታዩት ሀሳቦች አንዳንዶቹ ሁል ጊዜ ተመላልሰው የሚመጡ የደርጉ "እምነት"መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡"ኢትዮጵያዊ ስሜት"፤"ኢትዮጵያዊ መንፈስ"፤የሚሉት ከ"ኢትዮጵያ ትቅደም"ጋር የተያያዙ ተደጋግመው የሚመጡ አሳቦች ናቸው፡፡እንደዚሁም"ህዝቡ" በየሥራው በያለበት እንዲረጋ የሚጠይቀው ሀሳብ እስከአሁን ድረስ ሳያቋርጥ የመጣ፤የተደጋገመ ነገር ነው፡፡ገበሬም አረስ፤ነጋዴም ነግድ፤ሁሉም ባለበት ይርጋ፤እና "ለውጡን"ሁሉ እናመጣለታለን የሚል ነው፡፡

ወደ ንጉሡ ጉዳይ ለመመለስ፣ደርጉ በሰኔ 27 ለጦር አዛዦች– ማለትም ለአማን ሚካኤል አንዶም፣በዚያው ሰሞን ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም ለሆነው ለዷገማ ኬሉ የብሄራዊ ጦር አዛዥ፣ለገዛው በላይነህ የምድር ጦር ዋና አዛዥ፣ለታደሰ ገብሬ የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ፣ለታደሰ ወልኬ የአራተኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ፣ለታረሰ ለማ የክቡር ዘበኛ ዋና አዛዥ– በሰጠው ገለጻ፣"የገርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ እንዳለ ሆኖ" ይላል።በተረፈም፣በሀምሌ 2 ከወጡት የታወቁ 13 ነጥቦች በመጀመሪያው ነጥብ ደርጉ "ለገርማዊ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ያለውን ታማኝነት"ደገሞ ከገለጠ በኋላ በሁለተኛው ነጥብ የሚከተለውን ያስፍራል።

"<u>የዚህ ደርግ ተቀዳሚና መሠረታዊ አላማ የገርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ፍጹም እንዳለ</u> ሆኖ አዲሱ ካቢኔ ውስጥም ሆነ ውጭ ያለውን እንቅፋት በማስወገድ ካቢኔው በተሻሻለ ሁኔታ በተከከለ እንዲሰራ ማድረግ ነው" /አዲስ ዘመን ሀምሌ3፣1966።ሥርዝ የተጨመረ/

ደርጉ፣ከሰኔ 22 ጀምሮ ታላላቅ ባላባቶችንና ታላላቅ ቢሮክራቶችን ሁሉ ሲያድን፣ምናልባት እስከ ነሀሴ 19 ቀን፣የንጉሱ ቤተ መንግስቶች እስከ ተወረሱበት ቀን ድረስ፣ ንጉሡን ፈጽሞ ለመንካት ያሰበ አልነበረም።እንዲያውም፣ኮሎኔል ተሰማ አባደራሽ የተባለ የአየር ኃይል አባልና የደርቁ ቀበሌያች ኮሚሽነር፣ንጉሡ እንደተገለበጠ "<u>ስቴርን</u>"ለተባለው የጀርመን መጽሄት በሰጠው ውይይት መሰረት፣ደርጉ የፈለገው ንጉሡ "ለለውጡ" ከርሱ ጋር፣ከደርጉ ጋር እንዲሰለፍና እንዲመራ ነበር ! በዚህ ኮሎኔል አባባል፣ንጉሡ "የለውጡ" መሪ እንዲሆን ተጠይቆ እምቢ ስላለ ነው ደርጉ የገለበጠው !

የዛሬን አያድርገውና የጦር ኃይሎች ደርግ በሰኔ 21 አዲስ አበባን ሲይዝና ከሰኔ 22 ጀምሮ የኢትዮጵያን ህዝብ መዥገሮች ሲለቅም ኃይለ ስላሴን አገለብጣለሁ፣ሥልጣንን እይዛለሁ ብሎ፣አሳስቦም ነበር።ደርጉ ደጋግሞ እንደተናገረው ሁሉ፣ያን ጊዜ የተነሳው የመንግስትን ሥልጣን ለመያዝ አልነበረም።ባንዳንዶቹ መሪዎች ዘንድ ስልጣንን የመያዝ <u>ፍላጐት</u> በመጥፋቱ ሳይሆን፣ለዚህ ዝግጅት ስላልተደረገና ምናልባትም በሠራዊቱ ውስጥ የአስተሳሰብና የዓላማ ልዩነት ስለነበረ፣በመጨረሻም፣የንጉሡን ስልጣን በመፍራት ሳይሆን አይቀርም። ከሁሉም በላይ ግን፣ አሁን ወታደሩ"ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርን" ለማስፈር የወሰደው እርምጃ፤ አረማመዱ፣አቀራረቡ ... እንደሚያሳየው ሁሉ የመንግስትን ስራ እንዴት ለማካሄድ እንደሚቻል ስለማያውቅ በመፍራት ሳይሆን አይቀ



ርም።"አገዛዝን"ባለማወቅ ሳይሆን አይቀርም።

ወታደሩ በርግጥ ታላላቅ ባላባቶችንና የቢሮ ከበርቴዎችን፣ህዝቡን ስለዘረፉት፣በወሎ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ በረሃብ እንደቅጠል እንዲረገፍ ስላደረጉ፣እነርሱን ይዞ "ለፍርድ ለማቅረብ" ነበር የተነሳው።በነገራችን ላይ ደርጉ ከሰኔ 23 ጀምሮ ባወጣቸው፣የታሰሩትንና የሚታሰሩትን ሰዎች በሚመለከቱ መግለጫዎች ሁሉ"በህግ" እንደሚሰራ ደጋግሞ ተናገሯል።ለማንኛውም፣እንቅስቃሴው ሲጀመር ደርጉ ንጉሡን ለመገልበጥና ስልጣኑን ለመያዝ እንዳልተነሳ በርግጥ ለማየት ይቻላል ባይ ነኝ። የተነሳው የተባሉትን "እንቅፋቶች" አስወግዶ፣"አዲሱ ካቢኔ"ሥራውን ደህና እንዲያካሄድ ለማድረግ ነበር።የተነሳው የተባለው ህገመንግስት ተዘጋጅቶ ኢትዮጵያ ህገመንግስታዊ የንጉሥ አገዛዝ – ኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ – እንድትሆን ለማስደረግ ነበር።ንጉሡን ለመገልበጥና የመንግስትን ስልጣን ለመጨበጥ አልነበረም።

ሠራዊቱ ከመጀመሪያውም –ማለት በሰኔ ወር መጨረሻ ሲንቀሳቀስ – ምንም ያህል የተጣራ ፕሮግራም አልነበረውም።የከተማው ህዝብ "ፕሮግራማቸሁን አስታውቁን" ብሎ ሲወተውት፣እነዚያን የጠርቀና የአፈር፣የቁም ነገርና የትርኪምርኪ ድብልቅ የሆኑትን የሀምሌ ሁለት 13 ነጥቦች አቀረበ።ወደ ነዚህ እንመለሳለን። ገን ደርጉ"ህዝቡ"ሲል ማንን እንደሆነ እዚህ ላይ እንመልከት።

ሀምሌ 14 ቀን በወጣው አዲስ ዘመን፣የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ወታደራዊውን እንቅስቃሴ እንደሚደገፍ ከተገለፀ በኋላ፣"... ደርጉ የሚወስደው እርምጃ <u>የህዝቡን አስተሳሰብ</u> በመከተል መሆኑ"በደርጉ ተገልጧል።በሀምሌ 23 በወጣው አዲስ ዘመን፣ ደርጉ "...የኛ እምነት <u>የህዝቡን ድምጽ</u> በመከተል ዓላማችንን በስራ ለመገለጥ ነው።...."ይላል። የዚህ ዓይነቱን ምሳሌያች ከደርጉ ጽሁፎች ውስጥ ደጋግሞ ለማውጣት ይቻላል።ወታደሩ የሚለው የወሰደው እርምጃ ሁሉ"የህዝቡን ድምጽ"በመከተል መሆኑን ነው።

ከዚህ በፊት በመጽሄቶቻችን ተደጋግሞ እንደተገለፀው ሁሉ፣በኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ በፖለቲካ በየመደቡ አልተደራጀም።ሰፊውን ገበሬና ወዝ አደሩን የሚወክሉና ለርሱ በቀጥታ የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች በሌሉበት አገር፣ደርጉ "የህዝብ ድምጽ"የሚለው ማንን እንደሆነ ገልጽ ነው።የከተማውን ንዑስ ከበርቴ፣ማለትም የሰራተኛው ማህበር መሪዎችን፣ተማሪዎችን፣ምሁራንና የመሳሰሉትን ማለቱ ነው።ደርጉ "ህዝቡ ሀሳቡን ይስጥ"ብሎ የፖስታ ሳጥን ቁጥርና የደብዳቤ ሳጥኖች በአዲስ አበባ ያስቀመጠው እነዚህ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ነው።በርግጥም ደግሞ ይህ የነቃው የህዝብ

ክፍል የአንጓለካቸውን መገለበጥ ጠየቀ፤አንጓለካቸው ተገለበጠ::የኃይለ ስላሴንም መገለበጥ ጠየቀ፤ኃይለ ስላሴም ተገለበጠ::ደርጉ እስካሁን 'ተከተልኩት' የሚለው ድምጽ የትንሽ ከበርቴው ዲሞክራሲያዊ ድምጽ እንጂ የወዝአደሩና የገበሬው ሬቮሉሽናዊ ድምጽ አይደለም::ደግሞም ደርጉ እራሱ የፊተኛው መደብ አባል እንደመሆኑ መጠን፤የነዚህን የህብረሰባችንን ዋና መደቦች 'ድምጽ' ለመከተልና የሚጠይቁትን ለመፈጸም ችሎታ የለውም:: የመደብ ፍጥረቱ አይፈቅድለትም::እንኳንስ የነዚህን ሬቮሉሽናዊ ድምጽ ቀርቶ፤እስካሁን ሲከተለው የነበረውንም የከተማውን ንዑስ ከበርቴ ዲሞክራሲያዊ ድምጽ ከንግዲህ ማዳመጡን ያቆመ ይመስላል::

ደርጉ 'የህዝብ ድምጽ' የሚለው የከተማውን ትንሽ ከበርቴ ድምጽ ቢሆንም፤ያኛው፤ከዘጠና በመቶው በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ዙጋ መኖሩን ይረሳል ማለታችን አይደለም::የዚህን ሰፊ ህዝብ መኖርም ያውቃል፤ግን እርሱ እሩቅ ነው:: ደግሞም ይህኛው ህዝብ 'ከኢትዮጵያ ተራሮችና ሸንተረሮች' ወዘተ... ጋር ተያይዞ፤ያልተጨበጠ፤እራሱን በራሱ ነፃ የሚያወጣ ሳይሆን የሚሰዉለት መንፈስ—ነክ—አብስትራክት — አካል ነው::ወታደሩ 'የርሱን መብትና ደህንነት'ለማስከበር ነው የተነሳው::ይህ የደርጉ አስተሳሰብ አንዱ ጎን ነው::

ግን ከዚህ ጋር የተያያዘአንዱ ሌላ ጎን አለ፤ይኸውም ይህ ወታደሩ 'ነፃ የሚያወጣው' <u>ህዝብ</u>፤ ወታደሩ 'ክብሩን የሚያስጠብቅለት' <u>ህዝብ</u> እራሱ በገዛ እጁ የወደፊት እድሉን ለመጨበጥ በመነሳት ፈንታ፤በፀጥታ፤'በርጋታ'፤ሥራውን መቀጠል አለበት፤'ግዴታውን' መፈጸም አለበት::ገብር መክፈል አለበት፤ወዘተ...

እነዚህን ጥንዱ የደርጉን እምነቶች — ማለትም ወዛደሩና ገበሬው፤በተለይም ይህኛው፤የሚታሰብለትና በወታደሩ 'መስዋእትነት' ክብሩ የሚጠበቅለት መሆኑንና፤ደግሞም በስራው መርጋትና በፀጥታ ወታደሩ የሚያመጣለትን ለውጥ እየጠበቀ ያለበትን 'ግዴታ' መፈጸም እንዳለበት — እነዚህን ሁለት አስተሳሰቦች ከደርጉ ጽሁፎች በብዛት ጠቅሶ ለማሳየት ይቻላል::እንዳንዶቹን ብቻ ለመጥቀስ ያህል:—

ገና ስልጣኑን እንደያዘ ደርጉ፤በሀምሌ 2 ቀን፤'ሥራ ለማቆም ስላሰቡት መሥሪያ ቤቶች የጦር ኃይሎች ደርግ ማስጠንቀቂያ ሰጠ::' በዚህ ማስጠንቀቂያ ውስጥ 'አለቆቻቸውን የሚገላምጡት' ይወቀሱ! የሀምሌ 2ቱ የ13 ነጥቦች የደርጉ ኘሮግራም በቁጥር ሶስት የሚጠይቀው ህዝቡ ሥራውን እንዳያቋርጥ ነው::ሀምሌ 9 ቀን በወጣው አዲስ ዘመን የተሰጠው የደርጉ መግለጫ ከነአርእስቱ 'የጦር ኃይሎች ዓላማ የኢትዮጵያን ህዝብ መብት ለማስከበር ነው'ይላል::በሀምሌ 13 'የአገርና የወገን



ፍቅር ስሜት'በሚል አርእስት ስር፤ደርጉ ሰፊና የማይጨበጥ ሀተታ ካሰፈረ በኋላ ጽሁፉን እንደሚከተለው ይደመድማል:—

> 'እና ደግሞ በበኩላችን፤በአገሪቱ በጠቅላላው ህዝብና በጦር ሃይሎችስም በስክብርትና በፍቅር የምንለምነው፤ሁሉም በስራው ላይ እንዲተጋ... የእርሻና የንግዱ ስራ እንዳይቋረጥ፤የገብር በጊዜው አለመከፈልና የውጭ ዝብኚያች መቀነስ የእናት አገራችንን ምጣኔ ሀብት እንዳይጎዳ፤ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ... ነው::'

ሌሎችም ምሳሌያች ለመጥቀስ ይቻል ነበር::ይሁንናም በተለይ ባሁኑ ጊዜ በገጠሩ የተያዘው ዋና ስብከት 'ኢትዮጵያ ትቅደም'በሚለው አማካይነት ሁሉም ባለበት እንዲረጋ፤ነጋዴው ንግዱን፤ጭሰኛው እርሻውን እንዲቀጥልና ሁሉም የመንግስት ገብር እንዲከፍል ነው::ስለለውጥና ስለፖለቲካ ወዛደሩና ገበሬው መጨነቅ አያስፈልገውም፤ ደርጉ ያስብለታል!!

ንጉሡ ነገስቱን በሚመለከተው ሆነ እውነተኛውን ሰፊውን ህዝብ በሚመለከተው በኩል፤ የጦር ኃይሎች ደርግ የተጣራ ኘሮግራም ሆነ 'ፍልስፍና' አልነበረውም::የመንግስት ስልጣን ከያዘበት ቀን ጀምሮ እስከዛሬ የወሰዳቸው ተራማጅ እርምጃያች —ምናልባት ከታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት መያዝ በስተቀር — የተወሰዱት 'የህዝቡን ድምጽ'በመከተል ነበር::ይህንን ተከትሎ እስከዚህ መምጣቱም ጥሩ ነገር ነው:: ይሁንናም፤ደርጉ 'ዓላማያቼ ናቸው'፤'ፍልስፍናዬ ነው'' ወደሚላቸው ነገሮች አልፈን ከመተንተናችን በፊት፤የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አንዱ አጣዳፊ ጥያቄ ስለሆነው ስለኤርትራ ጥያቄ ምን እንደሚያስቡ ባጭሩ ለመመልከት እንፈልጋለን::—

እስካሁን ደርጉ ካበረከታቸው ሥነ ጽሁፎች ምናልባት ከሁሉ ያማረና ከሁሉ 'ልብ የሚነካው' የመጀመሪያው ስነጽሁፍ እራሱ ሳይሆን አይቀርም::ይኸውም በሀምሌ 3 አዲስ ዘመን የወጣው፤'ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች በፍጥነት እንዲመለሱ ተጠየቀ' የሚለው ድርሰት ነው::ጽሁፉ በርግጥ 'የፖለቲካ ስደተኞች' የሚለው ማንን እንደሆነ ግልጽ አይደለም::ይሁንናም በውጭ አገር የ ኖሩትን፤ወይንም ረዥም ሳለ ጊዜ የቆዩትን ሁሉ የሚመለከት ይመስላል::ብቻ ይህንን ነጥብ ለጊዜው ወደኋላ እንተውና የጽሁፉን ዋና ይዘት እናስተውል::...ጽሁፉ፤ከላይ እንደተባለው 'ልብ ለመንካት' የታቀደ ስለሆነ፤ስለውዲቷ አገራችን ተራሮችና ሸንተረሮች፤ከዚህ ለምለም አገር ተለይተን በባእድ አገር ስለመንከራተታችን፤ይህንን አስቃቂ ሁኔታ ከፍጻሜ የምናደርስበት ጊዜ መምጣቱን በሰፊው ያትታል::ከዚህ በኋላ ከዚህ በታች ሰሰፊው የምናስፍረውን ይዟል::

'በተጨማሪ ከአገራችን ወጥተው የሚገኙት ስደተኞች ብቻ ሳይሆኑ ቀድሞ በነበረት ባለስልጣኖች አስተዳደርና አመራር ተንገፍግፈው የባሕር መሳሪያ አንግተው ጥቃታቸውን ለመወጣት በዱር በገደሉ የሚንከራተቱ ወገኖቻችን እንዳሉ እናውቃለን፡፡ሆኖም እነዚህ ሰዎች የአገሪቱን አንድነትና ሰላም በማይፈልጉ ጠላቶቻችን ተገፋፍተው በተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ተመርዘው የያዙትን የሸፍተኝነት ተግባር ይቀጥሉ አንልም፡፡... ጠላቶቻችን በጉሳና በሃይማኖት እየከፋፈሉ ብዙ ገንዘብ የሚያፈሱት ለኛ አስበው ሳይሆን የሚኖሩበት መሬት የተፈጥሮ ፀጋና ውጤት የሌለው ዱርቅ ምድረ በዳ በመሆኑ በቀናት መንፈስ ይህንኑ በጅ አዙር ለመያዝ የታሰበ ዘዴ ሳይሆን አይቀርምና ሁላችሁም ከያላችሁበት ተመለሳችሁ በአዲስ መንፈስና በሙሉ ልብ ለኢትዮጵያ አገራችን ደህንነቱና ብልጽግና አብራችሁ እንድትሰለፉ አደራ እንላለን፡፡'

ከዚህ በላይ የሰፈረው የደርጉ ፍጹም የዋህ/ናኢፓ/ ሀተታ የኤርትራን ነፃነት ተዋጊዎች የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር የመሳሪያ ትግል ከጀመረ 13 ዓመታት ሆኖታል፡፡ የኃይለ ስላሴን መንግስት ካከሰረት ጉዳዮች አንዱ የኤርትራውያን ትግል መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ 'የባሕር መሳሪያ አንግተው'፣ 'የአገሪቱን አንድነትና ሰላም በማይፈልጉ ጠላቶቻችን ተገፋፍተው' ወዘተ... የሚለው፣ኃይለ ስላሴ ይህንኑ የኢትዮጵያን ሠራዊት ሲያሳጭ በሚያዝያ 27 ዲስኩሩ 'ብዙ የውጭ እጆች አሉበት' ካለው በፍጹም አይለይም፡፡ 'ጥቃት ለመወጣት' የሚለው መቸስ የዋህ አነጋገር ነው፣ሰው 13 ዓመት ሙሉ ለስሜት የመሳሪያ ትግል አያደርግም፡፡ 'ሸፍተኝነት' የሚለው የተለመደው የኃይለ ስላሴ መንግስት ስድብ ነው፡፡ 'በዱር በገደሉ የሚንከራተቱ ወንድሞቻችን' የሚለው አባታዊና የሸንገላ አነጋገር የኤርትራ ተዋጊዎች የኃይለ ስላሴን ወታደር — ይህንን ዛሬ ኃይለ ስላሴን ጥሎ 'ለኢትዮጵያ ህዝብ እቆማለሁ' የሚለውን ወታደር— ደጋግመው እንዳጠቁትና ጄኔራል ዱረስ እስከመገደል የደረሱ መሆናቸውን ለመካድ የተሰነዘረ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የየካቲት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ወዲህ እንኳን፣የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር ብዙ ፀረህዝብ ሹሞችንና የኃይለ ስላሴን መንግስት ወታደሮች በመሳሪያ ኃይል አላጠፋቸውምን? የሩቁን እንተወውና፣ሰኔ 14 ቀን 1966 ላይ ያሁኑ የሠራዊቱ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ ሳምንት አስቀድሞ የኤርትራ ግንባር የኤርትራን ገዥ የፖለቲካ አማካሪ የሆነውን ሹም ኢብራሂም ኢራይን በአስመራ ከተማ በቀን ገድሏል፡፡ እንግዲህ ሀቁ የተጨበጠው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ፣ደርጉ የኤርትራን ነፃ አውጭ ግንባር ስም ለመጥቀስ ከመጠየፉም በላይ፣ይህንን ትልቅ የአገሪቷን የፖለቲካ ጥያቄ እንደ ስሜት ጥያቄ አድርጉ ማቅረቡ የደርጉን የዋህነት/ናኢፓነት/ ያሳያል፡፡ደርጉ በአማን አንዶም



አማካይነት ስለኤርትራ ጉዳይ የያዘው አካሄድ፣ይህ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት እቆማለሁ የሚለው ደርግ፣የነኃይለ ስላሴን ጉዳና የያዘ ይመስላል፡፡ይህም ፈጽሞ የማያዋጣ ጉዳና መሆኑን ከነዚህ ከአስራ ሶስት ዓመታት የኤርትራ ህዝብ ተጋድሎ መረዳት በተገባው ነበር፡፡

በኤርትራ ጉዳይና በጠቅላላውም በብሄሮች ጥያቄ የደርጉ አስተሳሰብ ከኃይለ ስላሴ አስተሳሰብ ምንም ያህል የሚለይ አይመስልም፡፡እንዲያውም፣ ምናልባት ከደርጉ ይበልጥ 'ተራማጅ' የሚሆነው በነሃሴ 4 የወጣውን የህገመንግስት እቅድ ያዘጋጀው የህገመንግስት ኮሚሲዮን ሳይሆን አይቀርም!! የህገ መንግስቱ ንዑስ አንቀጽ 45 'የዚህ ህገ መንግስት ሌሎች አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው፣ኢትዮጵያውያን ነገዶችና ጎሳዎች [illegible] ባህላቸውን ለመጠበቅ፣ለማዳበርና ለማሻሻል መብት አላቸው' ይላል፡፡ይህ አንቀጽ ጥራት ይጎድለዋል፣ከሌሎች አንቀጾች ጋርም መቃረኑ አይቀርም፣የብሄሮች የፖለቲካ መብት አያውቅምና ፈጽሞ በቂ አይደለም፡፡ግን ከደርጉ የተምታቱ አሻሚ እሳቦች ተገን የተሻለ አንቀጽ ነው፡፡ ለማመሳሰል ያህል፣ከነዚያ መከረኛ 13 ነጥቦች ውስጥ ስድስተኛው እንዲህ ይላል:—

> 'በኢትዮጵያውያን መካከል ለብዙ ዘመናት የቆየውን በጎሳና በሃይማኖች የተመሰረተውን መለያየትና የኑሮ መራራቅ ኢትዮጵያ ትቅደም በሚል እምነት በብሄራዊ ስሜትና በእኩልነት ለአገር እድገትና መሻሻል ዓላማ ህዝቡ ታጥቆ እንዲነሳና ለዘመኑ ሥልጣኔ በይበልጥ ተካፋይ እንዲሆን የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡'

ደርጉ ምን ለማለት እንደፈለገ በፍጹም ገለጽ አይደለም፡፡ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለው <u>እምነት</u> የ'ጎሳና'የሃይማኖት እኩልነት እንዴት ሊያመጣ ይችላል? ለማለት የተፈለገው ይህ ከሆነ፡፡ 'ብሄራዊ ስሜት' እዚህ ላይ ምን ማለት ነው? የትኛው ብሄራዊ ስሜት?

ቀጥለን ለማንሳት የምንፈልገው ደርጉ ስለኢምፔሪያሊዝም በጠቅላላና ስለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ያለውን አቋም ነው፡፡ምንም እንኳን 'ኢትዮጵያ ትቅደም'ቢል፣ ደርጉ እስካሁን ፀረ ኢምፔሪያሊስት መሆኑን በጭርጊት አላሳየም፡፡ይሁንናም እዚህ ላይ ሁለት የደርጉን መግለጫዎች ለመጥቀስ እንወዳለን፡፡

1ኛ/በሀምሌ 20 ቀን 1966 በወጣው አዲስ ዘመን 'ከጠር ኃይሎች ደርግ የተሰጠ ማብራሪያ'በሚል አርእስት ስር ደርጉ የ'ኢትዮጵያ ትቅደም'ን ልዩ ልዩ ትርጉሞች ከሰጠ በኋላ፣ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት 'ከፖለቲካ ተጽእኖ፣የባሕር የምጣኔ

ሀብት ጥገኝነት ከሚያስከትለው ስውር ቀኝ ተገዥነት፣ወይንም ዘዴአዊ ብዝበዛ ወጥታ እራሷን እንድትችል በምስኩ ያልተቆጠበ ትግልና መስዋእትነት እንዲደረግ አጥብቆ የሚጠይቅ ነው "ይላል። ይህ ዓረፍተ ነገር ከዚህ በፊት በጠቀስነው የጥራት ጉድለት የተበከለ ቢሆንም፣/"በምስኩ ያልተቆጠበ ትግልና መስዋእትነት" የተጣራ አይደለም፣ ዓረፍተ ነገሩ "የኢምፔሪያሊስት ተጽእኖ ማስወገድ አለብን"፣ወይንም ይህን የመሰለ ነገር ብሎ መደምደም ነበረበት!/በመሰረቱ ፀረኢምፔሪያሊስት ነበር።...

25/ ኃይለ ስላሴ በተገለበጠ ሳምንት፣ደርጉ እነ በየነ ሰለሞንን ሲይዝ "የኢምፔሪያሊስት አገልጋዮች"ናቸው ብሎ ከመከሰሱ በላይ፣ በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተነገረው ከሆነ፣በዚሁ ሳምንት ውስጥ አንድ የደርጉ አባል በተማሪዎች ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ደርጉ "ፀረፊውዳሊስት ፀረኢምፔሪያሊስት ፀረካፒታሊስትና ፀረ ኮሙኒስት"መሆኑን ገልጿል። ከነዚህ አባባሎች ሁሉ የደርጉን ፀረ ኢምፔሪያሊስትነት ለመረዳት አይቻለም።

በዚህ ደረሲ አስተያየት፣ደርጉ ስለኢምፔሪያሊዝም ምንም የተጣራ አቋም የለውም። ለዚህ ምስክር የሚሆነው፣ከዚህ በላይ ከጠቀስነው የተዘባጭ አር ምጃ አለመውሰዱ ሊሳ፣ስለምጣኔ ሀብት"እና ስለ"ውጭ እርዳታ"ደርጉ አልፎ አልፎ የሚያወ ራው ነው። ለምሳሌ ከነዚያ ከታወቁት 13 ነጥቦች፣አንዱ የሚጠነቀው የውጭ እርዳታ እን ዳይቋረጥ ነው። ለደርቀ ቀበሌዎች ብቻ ሳይሆን በደፈናው "የወዳጅ አገሮች"እርዳታ። እንዲህ ከሆነ ከዚህ በላይ በቁጥር 1 በጠቀስነው ዓይነት፣ኢትዮጵያ ምኑን ነፃ ወጣች?

ኃይለ ስላሴ ከተገለበጠ ወዲህ፣ ንውስ ከበርቴው እርስ በርሱ መፋጨት በጀመረበት ባሁኑ ወቅት፣ባገር ቤት የሚወጡት የገራ ጋዜጦች —"የሰፊው ሕዝብ ድምጽ"፣"ዴሞክራሲያ— እንደሚሉት ከሆነ፣ደርጉ አሁን ፈጽሞ ከሲአይኤ ተጽእና ቁጥጥር ስር በመሆን ላይ ነው። ይህ ከሆነ እንግዲህ ደርጉ ፋሺስታዊ ጉዳናን በመያዝ፣ ከኃይለ ስላሴ እኩል የኢምፔሪያሊዝም ቡችላ ሆኗል ማለት ነው።

እስከዚህ ድረስ፣ደርጉ ለንጉሡ የነበረውን አቀራረብ፣ አየን። "የህዝብ ድምጽ" የሚለው የማንን እንደነበረና እርሱንም አሁን ማኘጥ ማቆሙን፣ ስለሰፊው የኢትዮጵያ ገበሬና ወዝአደር ያለውን አቋም፣ እንደዚሁም ኤርትራንና በጠቅላላ ውን የብሄረ ሰቦችን ጥያቄ በሚመለከተው በዚሁ "አስተሳሰቡ"እንዴት እንደሆነ፣በመጨረሻ ስለኢምፔሪያሊዝም ያለውን አቀራረብ በመጠኑ ተመለከትን። ደርጉ በሰኔ 26 ቀን ሥልጣን ሲይዝና መሳፍንትና መኳንንት ይዞ ሲያስር አንዳችም ፕሮግራም አልነበረውም። በተረፈም ደጋግሞ ከፕሮግራም ይልቅ የምንመርጠው ሥራን ነው በማለት፣የተቆናበረ በትርጉሙ የማያ



ሻማ ፕሮግራምና አስተሳሰብ በማቅረብ ፈንታ በድርጊት ብቻ ተወስኗል። እንዲያውም አንዳ ንዶቹ የደርጉ "አስተሳሰብ"እየተባሉ በመንግስቱ ጋዜጣ የወጡት ስነ ጽሁፎች ምንም ጥራት የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ የደርጉን ድርጊቶች የሚቃረኑ ሆነው ተገኝተዋል። ባይጻፉ ይሻል ነበር!

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ፣"ኢትዮጵያ ትቅደም"የሚለው፣ አሁን አገሪቷን ከዳር እስከዳር በማዳረስ ላይ ያለው"መሪ ቃል" ምን ትርጉም አለው? የጦር ሃይሎች ደርግ አሉን የሚላቸው "ዓላማዎች" የትኞቹ ናቸው? ደርጉ እፈልጋለሁ የሚለው ምንን ነው?፡ እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን በመመለስ የጦር ሃይሎችን ደርግ አቋም ጉዳይ እንደምድም።—

ከሁሉ አስቀድመን ደርጉ ለነዚህ ጥያቄዎች እራሱ የሚሰጣቸው መልሶች እንዳሉ ለቅመን እ እናስፍር።—

አዲስ ዘመን —ሀምሌ 3

"የዚህ ደርግ ተቀዳሚና መሰረታዊ ዓላማ የገርማዊ ንጉሠ ነገስት ዙፋን እንዳለ ሆኖ አዲሱ ካቢኔ ውስጥም ሆነ ውጭ ያለውን እንቅፋት በማስወ ገድ ካቢኔው በተሻሻለ ሁኔታ በትክክል እንዲሰራ ማድረግ ነው።..."

አዲስ ዘመን — ሀምሌ 9

"የጦር ሃይሎች ዓላማ የኢትዮጵያን ህዝብ መብት ለማስከበር ነው።... ለአገሩና ለህዝቡ የገባውን ቃል ከማስፈጸም የሚገታው እንደሌለና በአሁ ኑም ጊዜበአለኝታ የሚጠብቀውን ህዝብ ተቶ ወደሰፈሩ እንደማይመለስ ደርጉ አረጋግጧል።..."

አዲስ ዘመን —ሀምሌ 16 /ደርጉ በሀምሌ 15 ከንጉሡ ፊት ቀርቦ/

"የደርጉ ፍላጎት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሆኑትን ንጉሠ ነገስት የመሰረቷቸውና የደከሙባቸው የተቀደሱ ዓላማዎች በመከተል አገሩ ለማድ ረስ ስለሆነ፣በማናቸውም ረገድ ገርማዊ ንጉሠ ነገሥቱን የሚቃወመውን ሁሉ ተቃዋሚ ነው። ለሥራውም መሠረት ያደረገው የገርማዊ ንጉሠ ነገስ ቱን ዙፋን ፍጹም ሆኖ እንደተከበረና እንደተጠበቀ እንዲኖር ነው።..."

በዚሁ ጋዜጣ ውስጥ በዚሁ እለት፡—

"የጦር ኃይሉ የሚፈልገው አገሪቱ ሌላው ዓለም ከደረሰበት ደረጃ እንድት ደርስ፣ህዝቡ ታጥቆና በርትቶ እንዲሰራ እንቅፋቶች እንዲወገዱ ማድረግ እንጂ የማንንም ሀብትና ንብረት ለመውረስ ወይም ከሌላው ዓለም ህብረተ ሰብ ተገንጥሎ ብቸኛ ለመሆን አይደለም።..."

አዲስ ዘመን — ሀምሌ 20

"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን ደርጉ ሲተረጉም፣በፍጹም ባልተዛበጠ አኳኋን ከራስ ይልቅ ለአገር ማሰብ፣ታጥቆ ተነስቶ መስራት፣ጥልና መለያየት እን ዲቀር፣ወዘተ...ማለት ነው ካለ በኋላ፣ከዚህ በላይ የጠቀስነውን ፀረ ኢምፔሪያሊስት መሳይ ዓረፍተነገር አቅርቧል። ከዚህ ዓረፍተ ነገር

በኋላም እንደገና ዞር ወደአጠቃላይና ደግሞም ወደሁለተኛ ደረጃ ጥያቄያቸ ይመለስና የጥሪው ትርጉም የኑሮ ልዩነት ያስተካክል፣አለኩል፣ዝሙት፣ስንፍና፣ወዘተ. ይጥፋ ማለት ነው ይላል!!!

ከዚህ በላይ በጥቂቱ ከተጠቀሱት አባባሎችና ከደርጉ ሥራያቸ ምንን ለመደምደም ይቻላል? የጦር ኃይሎችን ደርግ አስተሳሰብና አቋቸ ምን ልንላቸው እንችላለን?እነዚህን አስተሳሰብና አቋቸ ዓይነተኛ የሚያደርጋቸው ምንድነው?

ትንሽ ወደኋላ ራቅ ብለን ብንመለከት፣የካቲት 21 ቀን የአራተኛው ክፍለ ጦር አባሎች አዲስ አበባ በሄሊኮፕተር በበተኑት ወረቀት ውስጥ፣በ11 ነጥቦቻቸው ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄያችን አቀርበው ነበር:: የዘረጡን አያድርገውና የነዚያን 11 ነጥቦች ከሥራ ላይ መዋል ምናልባት በዚያን ጊዜ ሳይፈልጉ አልቀሩም::

ግን የዘረያቹ ወታደሮች 'ኢትዮጵያ ትቅደም'በማለት ተነሳሳን ይላሉ::ይህ መሪ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በወታደሩ የተወረወረው/እና እስከምናውቀው ድረስ/ ሰኔ 26 ቀን የደርጉ አባሎች ከንጉሡ ፊት ቀርበው አምስት ጥያቄያቸውን ባቀረቡበት ጊዜ ነበር:: ደጋግሞ ተደጋግሞ ቢጠየቅም፣ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሁሉ ለዚህ መሪ ቃል ትርጉም ሊሰጠው አልቻለም:: ደርጉ ለዚህ 'መመሪያው' የሰጠው አጠቃላይ ትርጉም፣ለራሳችን ከማሰባችን በፊት ለአገራችን እናስብ፣ታጥቀን እንስራ፣መጠጥ እናብዛ፣ወዘተ. የሚል የቤተክርስቲያን ስብከት የሚመስል እንጂ የተጨበጠ የፖለቲካ ይዘት አይደለም:: ምናልባት አንዳንድ የተጨበጡ ይዘቶች አልፎ አልፎ ጣል ጣል ቢደረጉም፣በብዙ ያልተጨበጠ 'የግብረ ገብነት'ስብከት በመሸፈናቸውና፣ደግሞም ለዚያውም እንኳ ቁልጭ ባለ አነጋገር ባለመቀረባቸው በርግጥ ደርጉ ያምንባቸው እንደሆነ አይታወቅም::በጠቅላላው ግን ከነዚያ በየካቲት ከቀረቡት 11 ነጥቦች እጅግ በጣም ወደኋላ የቀረ ሥነጽሁፍ ነበር እስካሁን የሚቀርበው::

ስለዚህም፣ደርጉን በስነጽሁፍ ዓይነተኛነቱን ለማሳየት ከተፈለገ፣ዋናው የሚገኘው ምልክቱ አገር ወዳድ መሆኑ ነው:: በስነጽሁፍ ላይ በተጨማሪ እስካሁን የወሰዳቸውን ተራማጅ እርምጃያቸ ደርበን ብንመለከት —አድሃሪ እርምጃያቹን ለጊዜው ወደጎን ትተን — ደርጉ በርግጥ አገር ወዳድ መሆኑ የሚያጠራጥር አይመስለንም:: ነገር ግን በአገር ወዳድነት ብቻ ወደፊት መራመድ አይቻልም::እንዲያውም አገርወዳድነት ያለፖለቲካ ንቃት ብቻውን ከመጣ ወደብሄራዊነትና ወደፋሽዝም ሊለወጥ ይችላል::ይህ ክፉ አደጋ አሁንም በኢትዮጵያ ላይ አለ::

ደርጉን አገርወዳድነት ዓይነተኛ ያደርገዋል፣ግን'ኢትዮጵያ ትቅደም'የሚለው በዚህ መንፈስ ከተተረጐመ፣ከመጀመሪያዎቹ ነገሮች አንዱ የዚህ



መሪ ቃል ፀረኢምፔሪያሊስት ሆኖ መገኘት ነበር::'ኢትዮጵያ ትቅደም'በመሰረቱ ፀረኢምፔሪያሊስት መሆን ነበረበት::ደርጉ ግን እስኪሁን በወሰዳቸው እርምጃያቸ ፀረኢምፔሪያሊስትነቱን አላሳየም::ስለዚህ እራሱ የመሪ ቃሉን ትርጉም ከማፍረሱም በላይ፣አገርወዳድነቱን እራሱን የሚቃረን ሆኖ ይገኛል::ብሄራዊ ነፃነት፣ሙሉ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የአገር ነፃነት ከሌለን፣ለዚህ ነፃነት መታገል የመጀመሪያ ተግባራችን መሆን አለበት::ያለበለዚያማ አገርወዳድነታችን ከምኑ ላይ ነው?አገሪቷን ከለማኝነት ሳያወጡ አገር ወዳድነት ምንም ትርጉም የለውም::

ደርጉ አገር ወዳድ ቢሆንም፣ከዚህ በፊት በታጠቅ እንደተባለው ሁሉ በፖለቲካ ንቃት በኩል ወደኋላ የቀረ ነው::ይህንንም ከሚያሳዩት ነገሮች አንዱ ይኸው 'የኢትዮጵያ ትቅደም' ተቃናበር አለመቀረብና ደግሞም ከስራ ላይ አለመዋል ነው::መሪ ቃሉ ጠብቦ ተጣቦ አውር ብሄራዊነትን፣ከዚያም ፋሺስታዊነትን ብቻ ይዞ ሳያርፍ አይቀርም:: ይሁንናም፣የደርጉን በፖለቲካ ንቃት ወደኋላ መቅረት የሚያሳዩትን ሌሎች ምልክቶች እንጥቀስ::

የቀድሞ አድሃሪ ጄኔራሎች በየቦታው አዛዥ መሆንና መሾም የደርጉን የፖለቲካ ንቃት ዝቅተኛነት ያሳያል::ደርጉ ህዝቡን ስለማያምን፣ትላልቅ መኰንኖችን፣ጄኔራሎችን ካላቀረበና ካላሾመ፣ በህዝቡ ዘንድ የማይደመጥ ወይም የማይከበር መስሎታል! የወታደር አስተዳደር ማስፈሩ ፍጹም ትክክለኛ ነገር አይደለም፣ይሁንና ደርጉ ይህንን እርምጃ ከወሰደ አይቀር፣በአስተዳደሩ ላይ የሚሾሙት ግለሰቦች ለምን በድምጽ ብልጫ የተመረጡ ሻለቆች፣መቶአለቆች ወይንም አስርአለቆች ተራ ወታደሮች አይሆኑም? ለምን አድሃሪ ጄኔራሎች ከስልጣን ላይ እንዲወጡ ይደረጋል::ደርጉ እነአማን እንደምን ዓይነት 'የታወቁ'ወይንም 'የተከበሩ'ጄኔራሎች በየቦታው፣በራሱም ላይ መሾሙ፣በራሱ ምንም ያህል እምነት እንደሌለው ያሳያል::

የደርጉን የፖለቲካ ንቃት ውስንነት የሚያሳየው ሌላው ድርጊት ኃይለ ስላሴን እንደገለበጠ ዲሞክራሲያዊ ሬፐብሊክን አለማወጁና በርሱ ፈንታ 'ጊዜያዊ የወታደር አስተዳደርን'አውጀ፣በዚህ ላይ ደግሞ የንጉሡ ልጅ ተመልሶ እንዲነገስ መጠየቁ ነው::በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ፣የተባለው 'ጊዜያዊ'አስተዳደር እስከመቼ እንደሚቆይ አለማስታወቁ ነው::

የአልጋወራሽን ተመልሶ መንገስ በሚመለከተው በኩል፣አንዳንድ ተመልካቾች እንደሚሉት ከሆነ፣ደርጉ ይህንን የፈለገው ንጉሡ የሰረቀውን የኢትዮጵያን ህዝብ ሀብት ባልጋወራሹ መንገስ በዘውዱ ስም ለማስመለስ ስለፈለገ ነው ይላሉ::

ይህ በርግጥ የደርጉ ፍላጎት ከሆነና ደግሞም በዚህ አኳኋን ሊፈጸም የሚችል ከሆነ ይህም ራሱ በደርጉ በኩል ያለውን ያስተሳሰብ ደካማነት ያሳያል፡፡ የህዝቦች ነፃነት በገንዘብ የሚሸጥ የሚለወጥ አይደለም፡፡ ሀብትን የሚፈጥረው የሠርቶአደሩ ህዝብ ለፋት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሰርቶአደር ህዝብም እንዲ ተደራጅቶ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ከደመሰሰ፤እውነተኛ ነፃነቱን ከተቀዳጀ፤ኃይለ ስላሴ በስድሳ ዓመታት ያጠራቀመውን የሰርቆት ሀብት በጥቂት ወራት ውስጥ ሊፈጥረው ይችላል፡፡ ንጉሡ የሰረቀው ሀብት በማንኛውም ዘዴ ለህዝቡ እንዲመለስ ማድረጉ ትክክለኛ ነገር ሆኖ ሳለ፤ይህ ዘዴ ግን የኢትዮጵያን ህዝቦች የፖለቲካ ዓላማ የሚቃረን መሆን ፈጽሞ የለበትም፡፡

ደርጉ በፖለቲካ አስተሳሰብ በኩል የተራመደ ቢሆን ኖሮ፤እንደሚለው ለሰፊው ህዝብ የቆመ ቢሆን ኖሮ፤ንጉሡን እንደገለበጠ ወዲያውኑ የዘውዱ አገዛዝን ደምስሶ ፤የዚህን ሪፓብሊክ ህገመንግስት የሚነድፍ፤መይንም የተነደፈውን የሚያርም የህገመንግስት ምክር ቤት — ኮንስቲቱኤንት አሰምብሊ — ወዲያውኑ እንዲመረጥ ባደረገ ነበር፡፡፡..

ተራማጅ የኢትዮጵያ ወታደሮች ስለነዚህ ጉዳዮች ሁሉ ማሰብ ይገባቸዋል፡፡ ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ የሚፈልጋቸው ነገሮች የታወቁ ናቸው፡፡ ደርጉ 'የህዝቡን ድምጽ' መስማቱን አቁሞ፤እስካሁን የወሰዳቸውን ተራማጅ እርምጃዎች መቀለበስ ከጀመረ፤በህዝቡ ፊንታ ኢምፔሪያሊዝምን ካጣመጠና የኃይለ ስላሴን ጎዳና ከተከተለ፤ፍጻሜው እንደኃይለ ስላሴ የማያምር ይሆናል፡፡ አገሪቷ የያዘችው ጎዳና ወደዲሞክራሲ የሚያመራ ነው፡፡ በዚህ ጎዳና ላይ ማንም መሰናከል ሆኖ ሊቆይ አይችልም፡፡ የታሪክን እርምጃ፤ማለትም የህዝቦችን የወደፊት ግስጋሴ ሊያስቀር የሚችል ኃይል በዚህ ዓለም ላይ የለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ረቮሉሽን ማድረጋቸው ፈጽሞ አይቀርም፡፡

## 3. የኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ መደቦችና የኢትዮጵያ ረቮሉሽን

በኢትዮጵያ ተማሪያች እንቅስቃሴ ውስጥ፤በተለይም በውጭ አገሩ፤የኢትዮጵያ አሁን ሁኔታ ካስከተላቸው ነገሮች አንዱ፤የክርክር ብዛትና በዚህም ክርክር አማካይነት ያስተሳሰብ መጥራት ነው፡፡ የዲሞክራሲያዊ አሰራርና ኑሮ ዋና ጥቅም እዚህ ላይ ነው፡፡ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በነፃ ሀሳብ ለማቅረብ ስለሚችሉ አስተሳሰቦችና ርዕዮተ ዓለሞች ይጋጫሉ፤ይፋጫሉ፡፡ በዚህም መፋጨት ውስጥ ብዙውን ጊዜ የጠራና የብዙሃንን ተቀባይነት የሚያገኝ ያስተሳሰብና ያሰራር መስመር ወጥቶ ወደ ድርጊት



ይመራል፡፡ በዚህ ዓይነት ወደፊት መራመድ ይቻላል፡፡

ዲሞክራሲያዊ አሠራርና ዲሞክራሲያዊ ኑሮ በኢትዮጵያ እንዲሰፍን የምንታገለው እንዲሁም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ አሁን ባለንበት ሰዓት ያለፍርሃትና ያለገደብ ቁጥጥር አሳብ ሊያቀርብ የሚችለው ደርጉና ምናልባትም በአድርባይነታቸው የታወቁት የኢትዮጵያ 'ጋዜጠኞች' ብቻ ናቸው፡፡ ለሰፊው ህዝብ፤ማለትም ለገበሬው፤ለወዛደሩ፤ለተበዳዩ የከተማ ነዋሪ ጥቅም የሚቆሙት፤ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃነትና እርምጃ የሚቆሙት፤አሳባቸውን በይፋ ለመግለጽ አይችሉም፡፡ ሁኔታው ዘር ዘር እንደ ኃይለ ስላሴ ዘመን ሆኗል፡፡ የዛሬዎቹ 'ገዥዎቻችን' የንግግርን፤የጽሁፍንና የመሰብሰብን ወዘተ ነፃነት በተለይ በዛሬው ወቅት፤ እነዚህን ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች መከልከል ትልቅ ወንጀል መሆኑን መገንዘብ ይገባቸዋል፡፡ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ እነዚህ ነፃነቶች መኖር አለባቸው፡፡ የህብረተ ሰባችን ንቁ ክፍል ሁሉ ያለውን አስተሳሰብ ለማቅረብና ከሌሎች አስተሳሰቦች ጋር ተጋጭተው ሰፊው ህዝብ የሚፈልገው የትኛው እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ይህ አጣዳፊ ጉዳይ ነው፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር ጠቅላላ ስብሰባዎች የሃሳብ መጋጫ፤ያስተሳሰብ መጣሪያ ስብሰባዎች ዲሞክራሲያዊ ሸንጎዎች ሁነው ቆይተዋል፡፡ በነሀሴ 1966፤ባገራችን በየካቲት የጀመረው ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ በቀጠለበት ወቅት፤የ14ኛው ጠቅላላ ጉባዔያችን አንዱ ትልቅ ያከራከር የነበረ ጥያቄ የየካቲትን እንቅስቃሴ የመራው የትኛው መደብ ነው፡ያሚል ነበር፡፡ በቲዎሪ ደረጃም ሆነ ለቀን ተቀን ተግባር ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መቻል የግድ ያስፈልግ ነበር፡፡ አሁንም ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ መደቦች የትኞቹ እንደሆኑ፤እነዚህ መደቦች በየካቲት እንዴት እንደተሰለፉና አሁንም እንዴት እንደሚሰለፉ የግድ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ወዳጅና ጠላትን፤ጊዜያዊ ጓደኛንና ዘላቂ ወገንን ለማወቅ፤በዚህም ላይ ተመስርቶ የፖለቲካ መስመርን መቀየስ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ያለበለዚያ የዓር የድንበሩን በጨለማ ወደቀኝም ወደግራም እየዳሰሰ እንደሚደናበር ሰው ይከናል፡፡

ያውሮፓን ማህበር 14ኛ ጉባዔ በሚመለከተው በኩል የነበረው የአባላት አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር፡፡ ብዙሃኑ የየካቲትን እንቅስቃሴ የመራው የተንበ ከበርቴው መደብ ነው የሚለውን ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር የሚሄደውን አቋም ተቀብሏል፡፡ ከቀረው አነስተኛ ክፍል ይበልጡ እጅ ይህንን እንቅስቃሴ የመራው 'የሠራተኛው መደብ' ነው ሲል፤ ጥቂቶች ደግሞ ማንም አልመራው የሚል 'እስታራቲ' አቋም ነበራቸው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ያውሮፓው ማህበር ያወጣውን ሪፖርት አንባቢ እንዲመለከተው

እየጋበዝን፣ እና ግን ካሁኑ አንድ ነገር ለማመልከት እንፈልጋለን፡፡ይኸውም፣'ሠራተኛው' መራ ይሉ የነበሩት ጓደኞች ስለመደብ ስለራሱ ያላቸው አስተሳሰብ የተምታታ እንደነበር ነው፡፡በመደብ ትርጉም ላይ ተደጋግሞ የተፈጠረውንና አሁንም ደርጉና የደርጉ ጋዜጦች እንዳሻቸው የሚጠቀሙበትን የመደብ ውዥንብር ለማጣራት ያመቸን ዘንድ፣መጀመሪያ ነገር መደብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናመለከት፡፡ከዚያ በኋላ፣የኢትዮጵያ ህብረተሰባዊ መደቦች የትኞቹ እንደሆኑና የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ጉዳይ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡

እንግዲህ መደብ ማለት ምን ማለት ነው?

መደብ ለሚለው ቃል ከሁሉም የተሟላና የማያሻማ ትርጉም ሰጥቶ የጻፈው ሌኒን ነው፡፡ሌኒን ለመደብ የሚሰጠውን ገለጻ እንኳንስ ረቮሉሽናዊያን ቀርተው፣የከበርቴ ሊቃውንት እንኳ ሊቀበሉት ተገደዋል፡፡የሌኒን ገለጣ ከሁሉም ሳይንሳዊና ጥልቅ ስለሆነ ነው፡፡ይህንን ገለጻ ከዚህ በታች ተርጉመን ስናቀርብ፣ለእንግሊዝ ቋንቋ አንባቢያች የንግሊዝናውን አባባል በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ አስፍረናል፡፡ሌኒን መደቦችን ሲገልጽ እንዲህ ይላል:—

> 'መደቦች፣በታሪክ በተወሰነ ባንድ ህብረተሰባዊ የርባታ ቀንበር/ሲስተም/ ውስጥ በያዙት ቦታ፣ከርባታ መሳሪያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት/ይህም ብዙውን ጊዜ በህግ የተጠበቀና የተወሰነ ሆኖ/፣በህብረተ ሰባዊ የሥራ አደረጃጀት ውስጥ ባላቸው ሚና፣እና ከዚህም የተነሳ ከህብረተ ሰባዊው ሀብት ከሚያገኙት ድርሻ ብዛትና በማግኛው ዘዴ የሚለያዩ ትላልቅ የሰዎች ክምችቶች/ግሩፖች/ ናቸው፡፡መደቦች፣ባንድ በተወሰነ ህብረተሰብ ኢኮኖሚ ቀንበር ውስጥ ከያዙት ቦታ የተነሳ አንዱ የሌላውን የሥራ ፍሬ ሊቀማ የሚችል የሰዎች ክምችቶች ናቸው፡፡'

ይህንን ገለጻ ቀረብ ብለን መመልከት አለብን፡፡

መጀመሪያ ነገር 'የርባታ ቀንበር —ሲስተም ኦፍ ፕሮዳክሽን— ማለት፣ወይንም የርባታ ዓይነት ማለት በጠቅላላው ህብረተ ሰቡ የተሰማራበት የሀብት ማፍሪያ ዓይነት ማለት ነው፡፡በዚህም መንገድ የርባታ ዓይነት ወይንም ቀንበር የሁለት ነገሮች ድምር ነው፣ይኸውም የርባታ ኃይሎችና የርባታ ግንኙነቶች፡፡<u>የርባታ ኃይሎች</u> የሚባሉት የሰው ጉልበትና እውቀት፣የሥራ መሳሪያው፣የሚሰራበት የተፈጥሮ ሀብት እንደ መሬት፣ውሃ፣ወዘተ... ያሉትን ያጠቃልላል፡፡<u>የርባታ ግንኙነት</u> የሚባለው በህብር ተሰቡ ውስጥ ሰዎችን የሚያያይዘውን ግንኙነት ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ለምሳሌ ህጋጋት፣ልማዶች፣ፍል



ስፍናዎች፣ሃይማኖቶችና በጠቅላላውም የሰዎችን የርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከቱትን ሁሉ ማለት ነው፡፡እነዚህ ግንኙነቶች ዘረው ዘረው የሚመለከቱት የማፍሪያ መሳሪያዎችን ባለቤትነት ነት ነው፡፡

እንግዲህ ሌኒን 'ህብረተሰባዊ የርባታ ቀንበር' ወይንም ዝም ብሎ 'የህብረተ ሰብ ኢኮኖሚ ቀንበር' የሚለው ይህንን፣ባንድ በተወሰነ ዘመን አንዱን ህብረተ ሰብ ዓይነተኛ የሚያደርገውን አጠቃላይ የሀብት ማፍሪያ ዓይነት ነው፡፡ 'ባንድ በተወሰነ ዘመን' ብለናል፡፡ሌኒን 'በታሪክ በተወሰነ' የሚለውን ነው፡፡በህብረተ ሰብ ታሪክ ውስጥ እስካሁን የታዩት የርባታ ዓይነቶች፣ወይንም ህብረተሰባዊ የአርባታ ቀንበሮች፣1/. የጥንት የጋርዮሽ፣ 2/. የባሪያ፣ 3/. የባላባት፣ 4/. የከበርቴና 6/. የሶሺያሊስት ናቸው፡፡ከነዚህ በመጀመሪያው ውስጥ መደቦች አልነበሩም፡፡በተረፉት አራት የርባታ ዓይነቶች ውስጥ ግን መደቦች አሉ፡፡በአገራችን <u>ዋናው የርባታ ዓይነት</u> ባላባታዊ ነው፡፡ስለዚህም በዚህ የርባታ ዓይነት ውስጥ የሚገኙት መደቦች ህብረተሰባችንን ዓይነተኛ ያደርጉታል፡፡

ሌኒን 'በታሪክ በተወሰነ በአንድ ህብረተሰባዊ የርባታ ቀንበር' የሚለውን አየን፡፡መደቦች እንግዲህ በዚህ ዓይነት በህብረተሰብ ኑሮ ውስጥ በያዙት ቦታ ይለያያሉ፡፡አንዳንዶች የአዛዥነት ቦታ፣ሌሎች የታዛዥነት ቦታ፣አንዳንዶች የበላይ ሌሎች የበታች ሆነው ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ከዚህ ከቦታቸው ጋር የሚያያዘው፣እንዲያውም ይህንን ቦታቸውን የሚሰጣቸው ነገር 'ከርባታ መሳሪያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት'፣ማለትም የባለቤትነት ግንኙነት ነው፡፡ለምሳሌ፣በኢትዮጵያ ዋናው የሀብት ማፍሪያ 'መሳሪያ' መሬት ነው፡፡ስለዚህም የመሬት ባለቤትነት በሰዎች ከዚያም በመደቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ይወስናል፡፡መሬት ያለው ባላባት፣ባለትልቅ መሬት ጌታ ነው፣አዛዥ ነው፣የበላይ ነው፡፡በርሱ መሬት ላይ የሚሰራውና የስራውን ፍሬ ከግማሽ በላይ ማበርከት ያለበት ደግሞ የበታች፣ታዛዥ፣ሎሌው ጪሰኛ ነው፡፡በምእራብ አገሮችና በኢትዮጵያም በመጠኑ በገባው በከበርቴ ኢኮኖሚ ውስጥ፣ባለፋብሪካው አዛዥ፣ወዛደሩ ታዛዥ ነው፡፡ምንም እንኳ በሥራው ሀብትን የሚፈጥረው ሠርቶአደሩ ህዝብ ቢሆንም፣በባላባታዊና በከበርቴ ህብረተሰቦች ውስጥ ሠርቶአደሩ ህዝብ ያለው ቦታ የታዛዥነት፣የመጨቆንና የመበዝበዝ ቦታ ነው፡፡ይህም የሆነው የማፍሪያ መሳሪያዎች ባለቤት ሌሎች መደቦች ስለሆኑ ነው፡፡

መደቦች የሚለዩበት፣ሌኒን የሚሰጠው ሌላ መለኪያ ከህብረተሰቡ የሥራ ፍሬ ምን ያህሉን እንደሚያገኙና ይህንንም በምን ዘዴ እንደሚያገኙት ነው፡፡በኢትዮጵያ ባላባታዊው መደብ ከህብረተ ሰቡ የሥራ ፍሬ ዋናውን ድርሻ ይወስዳል፡፡

የሚወስዱበትም ዘዴ በህግ፣በመንግስትና በፖሊስ በማስገደድ ነው። ይህንን ክፍያ የሚወስደው ሳይሰራ ነው። ጪሰኛው ግን የሚያገኘውን አነስተኛ ክፍያ የሚወስደው እራሱ ሰርቶ ካፈራ በኋላ ነው። እንዲሁም ወዛደሩ ጉልበቱን አየሸጠ ከሚያፈራው ሀብት የሚወስደው እጅግ ያነሰውን ክፍል ሲሆን፣ከበርቴው ግን የማፍሪያው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ዋናውን ክፍያ ይወስዳል። አንዱ መደብ የሌላውን የሥራ ፍሬ የሚቀማው በዚህ ዐይነት ነው።

እንግዲህ ለማጠቃለል ያህል፣መደቦች በህብረተሰብ የርባታ አቀነባበር ውስጥ በያዙት ቦታ፣ከማፍሪያ መሳሪያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ከህብረተሰቡ የሥራ ፍሬ በሚወስዱት የሀብት መጠንና በአወሳሰዳቸውም ዘዴ እርስ በርስ የሚለያዩ የሰዎች ክምችቶች ናቸው። መደብ ማለት የደሞዝ ክፍል፣ወይንም ሞያ ዓይነት፣ ወይንም ጎሳ ማለት አይደለም። በደሞዝ ከፍተኛነት ወይንም ዝቅተኛነት መደቦችን ለመለየት አይቻለም። ወይንም እንደሸክላ ሰሪ፣የፋብሪካ ወዛደር፣አነስተኛ ነጋዴ ያሉትን ክፍሎች በኑሮ ደረጃቸው ተመሳሳይነት ብቻ አንድ መደብ ማድረግ አይቻለም።

በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ጸሁፎች ውስጥ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ አሉ የተባሉት መደቦች የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ. የባላባት መደብ /ይህም ለሁለት ተከፍሎ የትላልቅ ባላባቶችና የዝቅተኛ ባላባቶች መደብ/፣2ኛ. የቢሮ ከበርቴ መደብ፣ 3ኛ. የኮምፕራዶር —ከባዕድ ጋር የተሻረከ ቱጃር — መደብ፣4ኛ. ምናልባትም የብሄራዊ ከበርቴ መደብ፣ 5ኛ. የትንሽ ወይንም የንዑስ ከበርቴ መደብ፣6ኛ. የወዛደር መደብ፣ 7ኛ. የድሀ ገበሬና የጪሰኛ መደብ።

ባንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን መደቦች በርግጥ ለማወቅ የሚቻለው የየካቲትን እንቅስቃሴ የመሰለ ትልቅ የህዝብ እንቅስቃሴ ሲነሳ፣ረቮሉሽን ሲጀመርና ሲካሄድ፣ወይንም በቦታው ላይ ሆኖ የረዥም ጊዜ ጥናት ሲደረግ ብቻ ነው። የሆነ ሆኖ፣ከየካቲት እንቅስቃሴ በፊት የነበረውን የኢትዮጵያ ተማሪዎችን የመደብ ትንተና እንቅስቃሴው ሳያሻሽለው አልቀረም ብለን እንገምታለን። ለምሳሌ ብሄራዊ ከበርቴ ባለ የሚቻለው የተናው መደብ እንደሆነ በግልጽ አልታየም። በተረፈም፣በጠቅላላው በቴሪ ደረጃ 'ገበሬው' የትንሽ ከበርቴው መደብ ነው እንጂ እራሱን የቻለ መደብ፣አንድ መደብ አይደለም የሚል ክርክር አለ። እነዚህንና ሌሎችንም የመደብ ጥያቄዎች ለመመለስ በቦታው ላይ ጥናት እስኪደረግ ድረስ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መደቦች እንዳሉ አድርጎ ለመውሰድ ይቻላል።



በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ፣እስከየካቲት እንቅስቃሴ ድረስ የመንግስት ስልጣን ይዘው የነበሩት የትላልቅ ባላባቶች መደብና የቢሮ ከበርቴው መደብ ነበሩ። ዋናውን የመንግስት ስልጣን የመሩት በነአክሊሉ አካለወርቅ-ማሞ ታደሰ የሚመራው የቢሮ ከበርቴ መደብ ነበር። ይህ መደብ በየካቲት ከመንግስት ሥልጣን እንደተወገደ የትላልቅ ባላባቶች መደብ የተማረው ክንፍ በእንዳልካቸው ተመርቶ ሥልጣንን ይዞ ነበር። ግን እራሱም ከስልጣን እንዲወርድ ተደርጓል። ምንም እንኳ ገና የመንግስት ሥልጣን ጥያቄ ቁርጥ ባለ መንገድ ባይደላደልም፣አሁን ይህንን ስልጣን የያዘው የትንሽ ከበርቴው መደብ ነው። በዚህ ዓይነት ከየካቲት ወዲህ በሥልጣን ሦስት መደቦች ተፈራርቀውበታል።— የቢሮው ከበርቴ መደብ፣የትላልቅ ባላባቶች መደብ የተማረው ክንፍና አሁን ደግሞ የትንሽ ከበርቴው መደብ አንዱ ክፍል።

ከዚህ በላይ በጠቀስነው ያውሮፓ ማህበር ጉባዔ ላይ ትልቅ ውዝግብርን ያስከተለው፣ 'ሠራተኛው መሪ' ይሉ የነበሩት ጓዶች የትንሽ ከበርቴውንና የወዛደሩን መደቦች ለመለየት አለመቻላቸው ነበር። በነሱ አስተያየት የባንክ ሠራተኞች፣የአየር መንገድ ሰራተኞች፣የኤሰአማ መሪዎችና የመሳሰሉት ሁሉ 'የሠራተኛው መደብ' አባሎች ናቸው። ይህ መቸስ ትልቅ ስህተት ነው። እና ግን፣አንደኛ ነገር፣ባሁኑ ወቅት በጣም ግልጽ መሆን ስለሚያስፈልግ፣የተጣራ አስተሳሰብን ማቅረብ ስለሚያስፈልግ፣ 'የሠራተኛ መደብ' በማለት ፈንታ 'የወዝአደር መደብ' እንዲባል ሃሳብ አናቀርባለን። ሁለተኛ ነገር፣ወዛደር ማለት የሥራ ጉልበቱን ብቻ በመሸጥ የሚኖር፣በፋብሪካዎች ውስጥ፣በህንጻና በመንገድ ስራዎች ላይ፣በወደቦችና በትራንስፖርት፣በትላልቅ ዘመናዊ የእርሻ ቦታዎች ላይ የሚገኘውን፣ሰርቶ ትርፍ የሚፈጥረውን/ሰርፕለስ ቫሊዩ/ የህዝብ ክፍል ነው። በዚህ አገላለጽ ከሄድን ስህተት ሊደረግ አይቸለም። ምክንያቱም የባንክ ሰራተኞችና ሌሎችም የቢሮ ፀሀፊዎች ወዘተ. ጉልበታቸውን ብቻ በመሸጥ ቢኖሩም በዚህ ሥራቸው በቀጥታ ትርፍን/ሰርፕለስ ቫሊዩን/ የሚፈጥሩ አይደሉም። እነዚህ የትንሽ ከበርቴው መደብ አባሎች ናቸው። ሁለቱ መደቦች፣ወዛደሩና ትንሽ ከበርቴው የያዟቸው ቦታዎች የተለያዩ ናቸው።

በዚህ አጋጣሚ የዚህ የትንሽ ወይም ንዑስ ከበርቴ መደብ አባሎች የትኞቹ የህዝብ ክፍሎች እንደሆኑ እንገልጽ። ዝቅተኛ የመንግስትና የቢሮ ሠራተኞች፣ዝቅተኛ ነጋዴዎች፣ዝቅተኛ ባለሀብቶች/ለምሳሌ እንደባለታክሲዎች፣ሁለት ሦስት ሰዎች ቀጥረው እንደሚያሰሩ ሸማኔዎች ያሉ/፣ተማሪዎች፣ምሁራን፣አስተማሪዎች፣ተራ ወዛደር ሳይሆኑ ሳይመረጡ በወዛደሩ ላይ የተሾሙ የሠራተኛ ማህበራት መሪዎች፣የወታደሩ ዝቅተኛ መኮንኖች፣በገጠር ትንሽ ሰፋ ያለ መሬት ና የራሳቸው ከብት ያላቸው ገበሬዎች፣ወዘተ.

የዚህ መደብ አባሎች ናቸው። ማንኛውንም መደብ ከሌላው የሚለየው መስመር ቁርጥ ያለ ስላልሆነና በተለይም ንዑስ ከበርቴው ከሁለት ትላልቅ መደቦች —ማለትም ከከበርቴውና ከወዝአደሩ —መካከል ስለሆነ፣ካንዱ መደብ ወደሌላው የሚተላለፍበት ድንበር ሰፊ ነው። እንደመስመር ቀጭን አይደለም። ለምሳሌ ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው የህዝብ ክፍሎች ውስጥ "ምሁራን"ብለናል። አንዳንድ ምሁራን ከንዑስ ከበርቴውም ይልቅ ወደከበርቴው ሊጠጉና "የከበርቴ ምሁራን"/ቡርዧ ኢንቴሌክቹዋለስ/ሊሆኑ ይችላሉ። ባገራችንም ቢሆን እነዚህ አሉ። ለምሳሌ "መነን"በሚባለው መጽሄት ዙሪያ የተሰበሰቡት። እንደዚሁም የመንግስት የቢሮ ሰራተኞች የተባለው ቁርጥ ያለ ድንበር የለውም። ከፍ ሲል የቢሮ ከበርቴ ይሆናል። ወታደሩንም በሚመለከተው በኩል እንደዚሁ ነው። "ዝቅተኛ መኮንኖች"ሲባል በአጠቃላይ መንገድ በመሆኑ ሊያሳስት አይገባም፣መቶአለቃ ሆኖ የከበርቴው ወይንም የባላባቱ መደብ አባል ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም ገን፣ መደብ ሲባል ከሌኒን በተሰጠው ገለጻ መሰረት በመደቦች መካከል ያለው ድንበር እንደ ሂሳብ — ሁለትና ሁለት አራት እንደሚባለው — ሳይሆን፣ካንዱ ወደሌላው የሚታለፈው አጠራጣሪ የሆነ ሥፍራን ካቋረጡ በኋላ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም፣ ተማሪያች ከልዩ ልዩ መደቦች የተውጣጡ መሆናቸው እየታወቀ፣እንዴት የትንሽ ከበርቴው መደብ አባሎች ይባሏሉ የሚለው ጥያቄ ደጋግሞ ቀርቧል። አንዱ ጓድማ አንድ ጊዜ ለዚሁ የተማሪ ክፍል ልዩ መደብ በመፍጠር ቀዳሚ ንዑስ ከበርቴ/ሻጤፔቲ ቡርዧ/እንጂ ንዑስ ከበርቴ አይደሉም የሚል ፈሊጥ አምጥቶ ነበር። እርግጥ ተማሪው ልዩ ልዩ የመደብ ምንጮች አሉት። ግን በተማሪነቱ በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው ቦታ፣አኳኋኑና አስተሳሰቡ ሁሉ የትንሽ ከበርቴው መደብ አንዱ ክፍል ያደርገዋል። ይህ በጥራሽ የሚያጠራጥር አይደለም። ሆኖም አንዳንድ ጓዶች የወዝ አደሩን ርዕዮተዓለም "ተቀብለናል"/ቁርባን ይመስል /ወዛደሮች እንጂ ትንሽ ከበርቴ አይደለንም ይላሉ። ይህ ወቸስ "ተቀብለናል" የሚሉትን ርዕዮተዓለም ምንም ያህል እንዳል ተረዱት ከማሳየት ሌላ ምንም ትርጉም የለውም።

በየካቲት እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ መደቦች አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር። ትላልቅ ባላባቶች፣ኮምፕራዶርና የቢሮ ከበርቴያች ባንዱ ወገን፣ትንሽ ከበርቴው፣ወዛደሩና ገበሬው በሌላው ወገን ነበር የተሰለፉት። የፊተኞቹ የጥንቱ እንዳለ እንዲቀጥል፣የነበራቸው ቦታ እንዳይነካባቸው የሚፈልጉ ነበሩ። እነዚህኞቹ ደግሞ ለውጥ እንዲደረግ፣የቀደመው ስርዐት እንዲቀየርና በቦታው ሌላ እንዲተካ



ይፈልጉ ነበር። የነዚህ መሪ የትንሽ ከበርቴው መደብ ሲሆን፣ አሁንም በመጨረሻ የመንግስትን ስልጣን የያዘው ከዚህ መደብ አንዱ ክፍል፣ማለትም ወታደሩ፣ ነው።

በኢትዮጵያ ህብረተሰብም ሆነ በሌሎቹ በዛሬይቱ ዓለም ህብረተሰቦች ውስጥ፣ከመደቦች ሁሉ ዋና ረቮሉሽናዊ መደብ የወዛደሩ መደብ ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ/. ይህ መደብ ከሁሉ ዘመናዊ ከሆነው የኢኮኖሚ ክፍል፣ ማለትም ከኢንዱስትሪ ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህም፣ከሌሎች መደቦች ሁሉ፣ማለትም በርባታ ስራ ከሚካፈሉት መደቦች ሁሉ የሰለጠነ መደብ ነው። 2ኛ/. መደቡ የሚገኘው በየቦታው ሰብሰብ ብሎ ነው። እንደገበሬው የተበታተነ አይደለም። ስለዚህም ለማደራጀት ይመቻል። ደግሞም የኑሮ ሁኔታው፣ማለትም በሰዓት ሥራ ላይ መገኘት፣ ከሌሎች ጋር ቅጥና ወግ ባለው ሁኔታ ተባብሮ አንድን ስራ መስራት፣ወዘተ. "ሥልጡን" ስላደረገው ዲሲፕሊን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። በዚህም የመደራጀት ችሎታው ከፍ ያለ ነው። 3ኛ/. ይህ መደብ በመታገሉ፣ለመብቱ በመቆሙ፣ያለውን ስርዐት በማፍረሱ "ከታሰረበት ሰንሰለት በስተቀር የሚያጣው ነገር ስለሌለ" በቆራጥነት ለመታገል ችሎታ ያለው እርሱ ብቻ ነው። 4ኛ/. የወዝአደር መደብ በፍጥረቱ ዓለም ዐቀፋዊ — ኢንተርናሽናሊስት — ነው።

የወዛደሩ መደብ ከህብረተሰቦች መደቦች ሁሉ ዋና ረቮሉሽናዊ ስለሆነ፣ህብረተሰቡን ነፃ የማውጣት፣ማለትም በጠቅላላው መደቦች ወደሌሉበት/ጭቆናና ብዝበዛ ወደሌለበት/ ህብረተሰብ የሰውን ልጅ ለማድረስ ታሪካዊ ሃላፊነት የተጣለው በርሱ ላይ ነው። ይህንንም ሊያደርግ የሚችለው መጀመሪያ የራሱን የወዛደር ፓርቲ የፈጠረ እንደሆነና ረቮሉሽኖችን እንደየደረጃቸው ያደረገ እንደሆነ ነው። በዚህ ዓይነት ይህ መደብ እስካሁን ድረስ ከሰው ልጅ ዘር ሲሰውን ነፃ አውጥቷል። ወደፊትም ይቀጥላል።

በኢትዮጵያ ያለው የወዛደር መደብ በቁጥርም ሆነ በፖለቲካ ንቃቱ ባለፈት አስር አሥራአምስት ዓመታት ውስጥ አድጓል። ይህ መደብ አሁን ተከማችቶ የሚገኘው በትላልቅ ከተሞች፣ባዲስ አበባ፣በድሬደዋ፣በአሰብ፣በአስመራና እንዲሁም እንደተንዳሆ፣ስቴት ሀመራ ወዘተ. ባሉት ትላልቅ የርሻ ቦታዎች ላይ ነው። በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥ የኢትዮጵያ ወዛደር ትልቅ ቆራጥነቱን አሳይቷል። አሁን የሚጎድለው የራሱ ፓርቲ ነው። ይህን ፓርቲ ካገኘ አሁኑን ዲሞክራቲክ ረቮሉሽን ወደመምራት ሊጓዝ ይችላል። ለዚህ ሁሉ ብቁ እንዲሆን ነው የወዝአደሩ መደብ መደራጀት አለበት

የምንለው:: ገና የረቮሉሽን ሣይንስና የዓለም ዐቀፍ ወዛደር እንቅስቃሴያቸ ትምህርትና ልምድ ከኢትዮጵያው ወዛደር እንቅስቃሴ ጋር መዋሃድ አለባቸው:: ይህ መደብ ገና ብዙ ትግሎችን ማድረግ አለበት:: በመጀመሪያ በራሱ ፓርቲ ተደራጅቶ ትግሉን ሲቀጥል ብቻ ነው የሰፊውን ህዝብ ትግል በአንድነት አቀናብሮ ለመምራትና የመምራት ችሎታውን ሊያረጋግጥ የሚችለው::

______________××______________

እንግዲህ እስካሁን ድረስ መደብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ መደቦች የትኞቹ እንደሆኑ፣ እነዚህ መደቦች እንዴት እንደተሰለፉና በመጨረሻም የወዛደሩ መደብ ያለበትን ታሪካዊ ኃላፊነት ከዚህ በላይ ተመለከትን:: አሁን ደግሞ የመደቦች ትግል እንዴት እንደሆነና ይህም ትግል እንዴት ወደረቮሉሽን እንደሚያመራ እንይ::—

ከዚህ በላይ ባንድ ቦታ ስለአርባታ ኃይሎችና ስለአርባታ ግንኙነት አንስተን ነበር:: ለመድገም ያህል የርባታ ኃይሎች የሚባሉት ሰዎች፣ የስራ ጉልበታቸውና እውቀታቸው፣ የሥራ መሳሪያዎቻቸውና የሚሰሩበት የተፈጥሮ ሀብት፣/እንደመሬት፣ወንዞች፣ወዘተ። ያሉት/ አንድነት ተደምረው ነው:: ከነዚህም ውስጥ ዋናው ሰው መሆኑ ግልጽ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ የርባታ ግንኙነት የሚባለው ዋናዉ የርባታ መሳሪያዎች ላይ ያለው የባለቤትነት ግንኙነት ሆኖ ይህንንም በልዩ ልዩ ደረጃ የሚያረጋግጡትን፣ ህግጋት፣ ወጎችን፣ ልማዶችን፣ ሀይማኖቶችን ወዘተ። ያጠቃልላል:: እንግዲህ አንዱን ህብረተ ሰብ ዓይነተኛ የሚያደርገው የነዚህ ሁለት ነገሮች — የርባታ ኃይሎችና የርባታ ግንኙት — ድምር ነው:: ይህም ከዚህ በላይ የርባታ ዓይነት ወይንም የርባታ ቅንብር ተብሏል::

በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ የርባታ ኃይሎች ሁል ጊዜ እንዳደጉ ናቸው:: ሰዎች ይበረክታሉ፣ እውቀታቸው እየጨመረ ይሄዳል፣ አዳዲስ የሥራ መሳሪያዎች አዳዲስ የሥራ ጥበቦች ይፈጠራሉ:: በዚህ ዓይነት የርባታ ኃይሎች እያደጉ ሄደው አንድ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የርባታ ግንኙነቱ ወደኋላ ይቀርና ይበልጥ እንዳያድጉ መንገድ ይዘጋባቸዋል:: የርባታ ግንኙነቱ ለርባታ ኃይሎች እድገት መሰናከል ይሆናል:: በዚህን ጊዜ ህብረተሰባዊ ረቮሉሽን ተደርጎ የቀድሞው የርባታ ግንኙነት ይደመሰስና በቦታው ለታዳጊዎቹ የርባታ ኃይሎች የሚስማማ ሌላ ከፍተኛ የርባታ ግንኙነት ይፈጠራል:: በዚህ አኳኋን የሰው ልጅ ህብረተሰብ ወደፊት ይራመዳል::



አንዱን ረቮሉሽን የሚመራውና ከፍጻሜ የሚያደርሰው ታሪክ ኃላፊነቱን የጣለበት የዚህ ህብረተሰብ መደብ ነው:: በባሪያ ህብረተሰብ ውስጥ ይህ ኃላፊነት የባላባቱ መደብ ነበር:: በባላባታዊ ህብረተሰብ ውስጥ ቀድሞ ኃላፊነቱ የከበርቴው ነበር:: አሁን ግን የኦክቶበር 1917/እኤአ/ የሶሺያሊስት ረቮሉሽን ከተደረገ ወዲህና ደግሞም ዛሬ ከኢምፔሪያሊዝም ነፃ የሆነ ባላባታዊ ህብረተሰብ የማይገኝ በመሆኑ ይህን ረቮሉሽን የመምራት ኃላፊነት በወዝአደሩ መደብ ላይ ወድቋል:: እንግዲህ፣ በዚህ አኳኋን፣ ህብረተሰብን ወደፊት የሚያራምደው የከፍተኛ የመደብ ትግል ውጤት የሆነው ረቮሉሽን ነው ማለት ነው::

አንዳንድ ጓዶችና የውጭ ጸሀፊዎች የየካቲትን እንቅስቃሴና የኃይለ ስላሴን መገልበጥ 'ረቮሉሽን' ነው ይሉታል:: እኛ ግን የየካቲትን እንቅስቃሴ 'ሰፊ የህዝቦች ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ' እንጂ ራሱን የቻለ ረቮሉሽን ነው አንልም:: ለምን? ለመሆኑ ረቮሉሽን ማለት ምን ማለት ነው?

ረቮሉሽን ያዲስ ህብረተሰብ አዋላጅ ነው:: ረቮሉሽን የህብረተሰብ ጠቅላላ ሽም ሽር ነው:: ረቮሉሽኖች የታሪክ ጉታች መኪናዎች /ሎኮሞቲቮች/ ናቸው ይላል ማርክስ:: ረቮሉሽን ማለት ጊዜው ያለፈበትን መንግስት በጉልበት በመገልበጥ ስልጣን መያዝ ነው ይላል ሌኒን:: ማኦ ሴቱንግም በበኩሉ ረቮሉሽን ቴንጥ፣ ወይንም ለስላሳና ያማረ የራት ግብዣ አለመሆኑን ካመለከተ በኋላ፣ አንዱ መደብ ሌላውን በጉልበት ገንጥሎ የሚጥልበትና በቦታው የሚተካበት የጉልበት ሥራ ነው ይላል::

እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ረቮሉሽን ማለት አንዱ የህብረተሰብ መደብ ሌላውን በኃይል ከስልጣን የሚያስወግድበት ውጊያ ነው ማለት ነው:: ግን ደግሞ ረቮሉሽን የህብረተሰብም ጠቅላላ ሽም ሽር ነው:: ማለትም የቀድሞዎቹ ጨቋኝ መደቦች ከሥልጣን ሲወገዱ ጊዜው ያለፈባቸው አድሃሪ መደቦች ሲደመሰሱ፣ የቀድሞ የህብረተሰብ ህግጋትም፣ ወጎችም ጨቋኝ ስርዐቶችም አብረው ይደመሰሳሉ:: አሮጌ አስተሳሰብና እምነት ሁሉ ተሽሮ በቦታው አዲስ ይተካል:: ባጭሩ፣ በዚህ ሰፊ ትርጉሙ ረቮሉሽን ማለት አንዱን ህብረተሰብ ከዳር እስከዳር አጥለቅልቆ፣ በተለይ በርባታ ግንኙነት ደረጃ ማለትም በህግጋት፣ በእምነቶችና በአስተሳሰብ ደረጃ፣ በማፍሪያ መሳሪያዎች ባለቤትነት ደረጃ፣ ሙሉ ለውጥን የሚያስከትል የኃይል ድርጊት ነው:: አሮጌውን ህብረተሰብ በአዲስ የሚተካ እንቅስቃሴ ነው::

ይህ አጠቃላዩ የሪቮሉሽን ትርጉም ሲሆን በሌላ በኩል ግን ቃሉ በሪቮሉሽናዊ ጽሁፎች ውስጥ በሁለት አቀጣጫዎች ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ አሁንም ያገለግላል፡፡ በዚህ ዓይነት፣ አንዱ ትርጉሙ የመጨረሻውን የጉልበት ድርጊት፣ ሪቮሉሽናዊ አመጽን ሲያመለክት፣ ሁለተኛ ትርጉሙ ደግሞ ወደዚህ ወደመጨረሻው ድርጊት የሚያመራውን፣ መንገዱን የሚያዘጋጀውን ድርጊት ሁሉ ያመለክታል፡፡ /በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ሪቮሉሽን —ኢንሰረክሽን" እና "ሪቮሉሽን — ፕሮሰስ" ማለት ነው፡፡/ አሁን ለምሳሌ በኢንዶቻይና በመደረግ ላይ ያለው ጦርነት የመጀመሪያው ዓይነት ነው፡፡ ግን ደግሞ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ፣ ይህ ድርጊታቸው የመጪው ሪቮሉሽን አዘጋጅ ነው፡፡ የመጪው ሪቮሉሽን አንድ አካል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት፣ የየካቲትን እንቅስቃሴ እንደመጪው ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን አንድ አካል እንመለከተዋለን፡፡

በሪቮሉሽናዊ ሥነጽሁፍ ደራሲው የትኛውን የሪቮሉሽን ትርጉም እንደሚጠቀም ብዙውን ጊዜ ከካባቢው ማለትም በቃሉ ዙሪያ ካሉት አሳቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም፣ እንደእውነቱ ከሆነ፣ ሁለቱ ትርጉሞች የማይነጣጠሉ መሆናቸውን መረዳት አያዳግትም፡፡ በተረፈም፣ ሰፋ ባለ አነጋገር ስለሳይንስ ሪቮሉሽን፣ ስለባህል ሪቮሉሽን፣ ወዘተ. እንደሚነገር እናስታውስ፡፡ እዚህ ላይ ቃሉ በደፈናው "ትልቅ ለውጥ" ማለት ነው፡፡

አንዱን ሪቮሉሽን ዓይነተኛ የሚያደርጉት ሶስት ነገሮች ናቸው፡፡ እነሱም፣ አንደኛ ሪቮሉሽኑ ሊደርስበት የሚፈልገው ግብ ወይንም ሊያስከትል የሚፈልገው የህብረተሰብ ዓይነት፣ ሁለተኛ የሪቮሉሽኑ መሪ መደብ ማን እንደሆነ፣ ሶስተኛ ሪቮሉሽኑ የሚደረግበት የዓለም የታሪክ ዘመን ናቸው፡፡ በአስራ ስምንተኛውና በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመኖች በምዕራብ አውሮፓ የተደረጉት ሪቮሉሽኖች የነበራቸው ግብ ባላባታዊ ስርዐትን አስወግዶ የከበርቴ ህብረተሰብን መገንባት ነበር፡፡ የነዚህ ሪቮሉሽኖች መሪም የከበርቴው መደብ ነበር፡፡ ዘመኑም የከበርቴ ሪቮሉሽን ዘመን ነበር፡፡

በዛሬይቱ ዓለም፣ በ1917/እኤአ/ የመጀመሪያው ሶሺያሊስት ሪቮሉሽን ከተደረገ ወዲህ በማነኛውም አገር ሊደረግ የሚችል ሪቮሉሽን ከሁለት አንዱ ነው፡፡ /ከሶስት አንዱ ነው የሚሉም አሉ ግን ለጊዜው ወደጎን እንተዋቸዋለን/ የመጀመሪያው ዓይነት ሪቮሉሽን "ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ" ወይንም "ያዲሱ ዴሞክራሲያዊ" ወይንም "ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ" ሪቮሉሽን ሲሆን፣ ይህም የሚደረገው እንደኢትዮጵያ ባሉት በኢምፔሪያሊዝም ቀንበር ስር በሚኖሩበት የሶስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ ነው፡፡



ሁለተኛው ደግሞ በዳበሩት የምዕራብ አገሮች ሊደረግ የሚችለው ሶሺያሊስት ሪቮሉሽን ነው፡፡ በሶሺያሊስት አገሮች ይኸው ሶሺያሊስት ሪቮሉሽን በተለየ ሁኔታና ዘዴ ይቀጥላል፡፡ አንዳንድ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል፣ በኢንዶቻይና በመካሄድ ላይ ያለው ህዝባዊ የነፃነት ትግል በመሰረቱ የብሄራዊ ዴሞክራቲክ ሪቮሉሽን ነው፡፡ የምእራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አገሮች የወዛደሩ መደብ በየጊዜው የሥራ ማቆም፣ የሰላማዊ ሰልፍና የተቃውሞ ትግሎች ወደ ሶሺያሊስት ሪቮሉሽን የሚመሩ ታሪካዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በቻይና "ታላቁ የወዛደር የባህል ሪቮሉሽን" በሶሺያሊዝም ስር የተደረገና በመደረግ ላይ ያለ የሶሺያሊስት ሪቮሉሽን ከፍተኛ ደረጃ ነው፡፡

ከታላቁ የኦክቶበር ሶሺያሊስት ሪቮሉሽን ወዲህ ከከበርቴው ስርዐት ሆነ ከባላባታዊ ስርዐት ለመውጣት የሚደረገውን ሪቮሉሽን ለመራና ከፍጻሜ ሊያደርስ የሚችለው የወዛደሩ መደብ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ያሰራዘጠነኛው ክፍለዘመን ካፒታሊዝም /የከበርቴ ኢኮኖሚ/ ወደኢምፔሪያሊዝም በመቀየሩና ዓለምን በሙሉ በማያያዙ እንደኢትዮጵያ ባሉት አገሮች ራሱን የቻለ፣ ከኢምፔሪያሊዝም ነፃ የሆነ፣ ሃይለኛና ብሄራዊ የከበርቴ መደብ ስለሌላቸውና ደግሞም ቢኖርም በዛሬይቱ አለም አካባቢ ሪቮሉሽኖችን መርቶ ከፍጻሜ ለማድረስ ስለማይችል ነው፡፡ ስለዚህም አዲሱን ዴሞክራቲክ ሪቮሉሽን የመምራት ኃላፊነት የወደቀው በወዛአደሩ ላይ ነው፡፡ ይህ መደብ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ተራማጅ መደቦችና የህዝብ ክፍሎች ሁሉ — ማለትም ዘጠና በመቶውን የአገሪቷን ህዝብ — አሰልፎ ኢምፔሪያሊዝምንና ባላባታዊ ሥርዐትን ሲደመስስና የመንግስት ሥልጣን በጉልበት ሲይዝ ሪቮሉሽን ተደረገ ይባላል፡፡

እንግዲህ በዚህ አኳያ ሲታይ በአገራችን የየካቲት የፈነዳው እንቅስቃሴ ያዲሱን ዴሞክራቲክ ሪቮሉሽን ጥርጊያ ጉዳና የሚያዘጋጅ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች የነጻነት ተጋድሎ አንድ ትልቅ ምእራፍ ነው ማለት ነው፡፡ ገና ግን የምንጠብቀው የምንታገልለት ሪቮሉሽን አልተደረገም፡፡ ብሄራዊ ዴሞክራቲክ ሪቮሉሽን አልተደረገም፡፡

ይሁንናም ይህንን ሪቮሉሽን ለማድረግ ተጨባጭና /ኦብጀክቲቭ/ ህሊናዊ /ሰብጀክቲቭ/ ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ይህ የሁኔታ "ምቹነት" በውጭ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ብዙ አከራክሯል፡፡ ስለዚህም ቀረብ ብሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች መጽሄቶች ላይ ተደጋግሞ እንደተጻፈው ሁሉ፣ በኢትዮጵያ ተጨባጩ ሁኔታ ለሪቮሉሽን የሚያመች ሆኖ ሳለ፣ ህሊናዊው ሁኔታ ግን ወደኋላ ቀርቷል፡፡ ይህም ማለት ወደአዲሱ ዴሞክራቲክ ሪቮሉሽን

ትግሉን ለማራመድ ህሊናዊ ሁኔታውን ማሳደግ ያስፈልጋል::ሰፊው ህዝብ ስሏል ተደራጀ—ይህም የህሊና ዊውን ሁኔታ ወደኋላ መቅረት ያመለክታል::—በአሁኑ ጊዜ የህዝቡ ትግል አጣዳፊ ጥያቄ የመደራጀት ጥያቄ ነው::

የሆነ ሆኖ ወደ ረቮሉሽናዊ ሁኔታ ጉዳይ እንመለስና የሌኒንን አቀራረብ እንመልከት::ሌኒን የሚለው ረቮሉሽናዊ ሁኔታ መጽሄቶቻችን 'ተጨባጭ ሁኔታ' ሲሉት ከነበረው ጋር አንድ ነው::ይህም ከሚቀጥለው የሉኒን ጥቅስ በደንብ የሚታይ ነው::/ይ የእንግሊዝኛው ጥቅስ በጽሁፉ መጨረሻ ላይ ሰፍሯል::/

'ላንድ ማርክሲስት ረቮሉሽናዊ ሁኔታ ከሌለ ረቮሉሽን እንደማይቻል ገለጽ ነው፤በተጨማሪም ማንኛውም ረቮሉሽናዊ ሁኔታ ረቮሉሽንን አያስከትለም:: በጠቅላላ አነጋገር የረቮሉሽናዊ ሁኔታ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው::የሚከተሉትን ሶስት ዋና ምልክቶች ብንሰጥ በርግጥ ለንሳሳት አንችለም::1. ገዥ መደቦች አገዳቸም ለውጥ ሳያደርጉ መግዛት መቀጠል ሲያቅታቸው፤ባንድ ወይም በሌላው መልክ ስላዩቹ መደቦች'ውስጥ ችግር /ክሪዝ/ሲፈጠር፤ይሆም የገዥው መደብ ፖሊሲ ችግር ሆኖ የተጨቆኑ መደቦች ቅሬታና ቁጣ ሊወጣ የሚችለበት ቀዳዳ ሲያገኝ::ረቮሉሽኑን ለማድረግ ብዙውን ጊዜ 'የበታች መደቦች'እንደድሮ መኖር 'አለመፈለግ'በቂ አይደለም፤የላይኞቹ መደቦች'በድሮው መንገድ'ለመኖር አለመቻላቸውም' ያስፈልጋል::2. የተጨቆኑ መደቦች ስቃይና ችግር ከተለመደው የበለጠ ከፍ ሲል::3. ከዚህ በላይ ከተነገረት ምክንያቶች የተነሳ የሰፊው ህዝብ ድርጊት በጣም ሲጨምር፤ይህም፤'በሰላም ጊዜ' ጭጭ ብሎ መዘረፉን የሚፈቅድ /ሰፊ ህዝብ/ግን፤በግርግር ጊዜያት፤በችግሩ ሁኔታ ሁሉና በበላይኞቹ መደቦች በራሳቸው ወደነፃ ታሪካዊ ድርጊት ሲገፋፉ::

እነዚህ ተጨባጭ ለውጦች ከሌሉ /እነርሱም ከያንዳንዱ ግሩፕና ፖርቲ ብቻ ሳይሆን ከያንዳንዱ መደብ ፍላጎት ቁጥጥር ውጭ ናቸው/በጠቅላላው ረቮሉሽን አይቻልም::የነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች ሙሉ ድምር ረቮሉሽናዊ ሁኔታ ይባላል::...ማንኛውም ረቮሉሽናዊ ሁኔታ ረቮሉሽን አንዲነሳ አያደርግም::ረቮሉሽን ሊነሳ የሚችለው አላይ ከተጠቀሱት ተጨባጭ ለውጦች ጋር ህሊናዊ ለውጥ ማለትም፤ረቮሉሽናዊው <u>መደብ</u> የሠፊ ህዝብ ረቮሉሽናዊ ድርጊትን ለማከናወን ሲችልና ይህም፤በችግርም ጊዜ ሆነ መቼም ካልተገፈተረ የማይወድቀውን መንግስት ለመሰባበር /ለማወላለቅ/<u>በቂ ጉልበት</u> ሲኖረው ብቻ ነው::'

ይህ የሌኒን ጥቅስ ብዙ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለንም::የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በሚመለከተው በኩል 'ረቮሉሽናዊ ሁኔታ' ከተፈጠረ ቆይቷል ለማለት ይቻላል::ዛሬ ከየካቲት እንቅስቃሴ በኋላም ይህ ሁኔታ ከድሮ የበለጠ ተሟልቶ ይገኛል::የኢትዮጵያ ህዝቦች የፖለቲካ ህሊናም በጣም ከፍ ብሏል::ግን



አሁንም ቢሆን ለሰፊው ህዝብ በህሊና ደረጃ ገልጽ ያልሆነ ነገር አለ::ይኸውም ኢምፔሪያሊዝምንና ባላባታዊ ስርዐትን በጉልበት መደምሰስና የመንግስትን ስልጣን በወዝአደሩ መሪነት ስር መያዝ ማስፈለጉን ነው::የወዝአደሩ መደብና ሌሎችም ጭቁን መደቦች እስኪል ተደራጁ ድረስ በተለይም የመጀመሪያው በፓርቲው አማካይነት ሰፊውን ህዝብ ለመጨረሻው ትግል እስኪያሰለፈ ድረስ በኢትዮጵያ ረቮሉሽን ለማድረግ ይቻላል፤ህዝባዊ ጦር ትግልን ለመጀመር ይቻላል ማለት ፍጹም 'ገራ' ቀደም አባባል ነው::... :

እንግዲህ ለማጠቃለል ያህል፤በኢትዮጵያ ሊደረግ የሚችለውና ደግሞም በመጀመሪያ ሊደረግ ላይ ያለው አዲሱ ዲሞክራሲያዊ ረቮሉሽን ነው::/በነገራችን ላይ 'አዲስ' የተባለበት ምክንያት ከ1917 በፊት ይደረጉ የነበረት <u>ዲሞክራሲያዊ</u> ረቮሉሽኖች በአመራሩ ሆነ በግቡና በውጤቱ የተለየ በኢምፔሪያሊዝምና በሶሺያሊስት ረቮሉሽኖች ዘመን የሚደረግ ስለሆነ ነው::/ሌላ ሊሆን ፍጹም አይችልም::ይህ ሪቮሉሽን የሚመራው በወዝአደሩ መደብ ሲሆን የዚህ መደብ ዋናው ወገን ገበሬው ነው::ይሁንና በህብረተሰባችን ተራማጅ መደቦች —ማለትም ትንሽ ከበርቴውና ከተገኘም ብሄራዊ ከበርቴው — በረቮሉሽኑ በአጋዥነት ይሰለፋሉ::የረቮሉሽኑ ግብ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክን መመስረትና የሶሺያሊዝምን ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰባዊ መሰረቶችን መጣል ነው::በዚህ አኳኋን ረቮሉሽኑን ለማድረግ የወዝደሩ መደብ መጀመሪያ የራሱን ፓርቲ ማግኘት አለበት::ከዚያም የተቀረትን የህብረተሰቡን ተጨቋኝ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ማደራጀት፤እነዚህን ሰብስቦ በአንድነት ግንባር ስር ማሰለፍና በኢምፔሪያሊዝምና በባላባታዊ ስርዐት ላይ መዝመት አለበት::

የረቮሉሽኑ አመጣጥ የግድ በነዚህ ደረጃዎች ማለፍ አለበት::ባሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛ ውጤትና ደረጃ የሆነውን ህዝባዊ የጦር ትግል ከሌላው ለማስቀደም መሞከር፤የኢትዮጵያን ህዝቦች ትግል ለማደናቀፍ እንደመሞከር ይቆጠራል::በዚህ ከተስማማን እንግዲህ ዋናው ጥያቄ በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ መወሰድ ያለባቸው የጊዜው እርምጃዎች የትኞቹ ናቸው የሚለው ነው::

## 4. <u>የሚከተለው እርምጃ ምን መሆን አለበት</u>

እስካሁን ድረስ ስለጦር ኃይሎች ደርግ በምንናገርበት ጊዜ የደርጉ አስተሳሰብ ይህ ነው፤እንዲህ እንደዚህ ነው እያልን ጽፈናል::እዚህ ውጭ አገር እንደተወራው ከሆነ ይህ ደርግ 120 አባሎች ሲኖሩት፤ሁሉም የተመረጡ ናቸው፡:

ደግሞም ከተራ ወታደር እስከኰሎኔል ድረስ የሆኑ አባሎች አሉበት ይባላል፡፡ይሁንና የደርጉ እርግጠኛ አሰራር እንዴት እንደሆነ አናውቅም፡፡ለምሳሌ ለትንተናችን አንድ መሠረት ያደረገናቸው በመንግስቱ ጋዜጦች ተደጋግመው የወጡት "መግለጫዎች"፣ማብራሪያዎች" ወዘተ. የሚሰሩት በማን ነው? ደርጉ የስነጽሁፍ ቦርድ አለው? ወይንስ አንድ ጸሀፊ? ወይንስ አባሎች በየተራ እየጻፉ ነው? ደግሞስ አንድ ጽሁፍ ከመውጣቱ በፊት ለደርጉ ጠቅላላ ስብሰባ ይቀርባል? ወዘተ...እነዚህን ጥያቄዎች ለመቅረብ የምንገደደው ከዚህ በፊት ባንድ ቦታ እንዳመለከትነው ሁሉ፣የደርጉ ጽሁፎችና ስራው፣እንደዚሁም የደርጉ መግለጫዎች እርስ በርስ ስለሚቃረኑ ነው፡፡ለማንኛውም በስሙ እስከወጡ ድረስ የጽሁፎቹ ሃላፊ ደርጉ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ስለዚህም፣ "የደርጉ አቋም"፣"የደርጉ አስተሳሰብ" በማለታችን ስህተት አላደረግንም፡፡

እንደሚታወቀው የጦር ኃይሎች ደርግ በሰኔ 26 የመንግስት ስልጣን ከያዘ በኋላ በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ንጉሡን ገልብጦ ሥልጣኑን ከነስሙ ይዟል፡፡ማለትም በፊት ለስሙ የመንግስት ሥልጣን የያዘው ሲቪል ነበር፡፡በመስከረም 2 ቀን 1967 ደርጉ ባወጣው አዋጅ ይህንን ያስታውቃል፡፡በተጨማሪም በዚሁ ቀን "የደርጉ ዓላማዎች" የተባለ አንድ ድርድርና ያሉትን መንግስት የውጭ ፖለቲካ የሚመለከት 5 ነጥቦች ማስታወቂያ ወጥቷል፡፡አሁን እንግዲህ በነዚህ ሶስት ጽሁፎች ላይ በመመስረት ያለንበትን ሁኔታ መመልከት አለብን፡፡በሚቀጥሉት ገጾች የደርጉ አዋጅና "ዓላማዎች" እንዴት ሊተረጎሙ እንደሚችሉ፣በየኪቴቱ እንቅስቃሴ የኢምፔሪያሊዝም ሚና እንዴት እንደሆነ ከልዩ ልዩ የህዝብ ክፍሎች ስለቀረበው "የጊዜያዊ መንግስት" ጥያቄ ጉዳይና በመጨረሻም ባሁኑ ጊዜ ልንጠይቃቸውና ልንፈጽማቸው ስለሚገቡን ነገሮች አሳብ ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡

ደርጉ ኃይለ ስላሴን የገለበጠበትን ምክንያት ሲሰጥ፣ "ከህዝብ የተሰጣቸውን ከፍተኛ የክብር ስልጣን"— የትኛው ህዝብ ነው ይህንን "የክብር" ሥልጣን ለንጉሡ የሰጠው? — ለራሱና ለቤተሰቡ ጥቅም ስላዋለና፣ ደግሞም በማርጀቱ ከንግዲህ ያለበትን ሃላፊነት ሊፈጽም ስለማይችል ነው ብሏል፡፡"ጊዜያዊ ወታደራዊ" አገዛዝን የፈጠረበትን ምክንያት ሲሰጥ ግን ሶስት ነገሮችን ይጠቅሳል፡፡—ሀ. የነበረው ፓርላማ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ባለመመረጡ፣ለ. የ1948 ህገመንግስትም ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑና እንዲያውም የኢትዮጵያን ህዝብ ስለሚጎዳበ፣ሐ."የፀጥታ ችግሮች"በመፈጠራቸው"፣ "ጠንካራ የአስተዳደር ስርዐት መፍጠር ስላስፈለገ" ነው ይላል፡፡እንደእውነቱ ከሆነ ግን፣የአዋጁን ነጥቦች ብንመለከት ወታደሩ"ጠንካራ አስተዳደርን"በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ እንዲያሰፍር



ያደረገው ዋናው ምክንያት በሶስተኛው ቦታ የተጠቀሰው ነው፡፡"የፀጥታ ችግሮች በመፈጠራቸው" የሚለው ነጥብ ነው፡፡የአዋጁ ይዘት ብቻ ሳይሆን ከዚያ ወዲህ ደርጉ የወሰዳቸው እርምጃዎች ስናይ "ጠንካራ አስተዳደርን"ማለትም በጉልበት የህዝቡን ድምጽ ጭጭ ማሰኘትን እንደፈለገ ነው፡፡እንግዲህ ካሁኑ በደርጉ ምክንያቶች መሃል ቅራኔ ይታያል፡፡ደርጉ ባንዱ በኩል ስለዴሞክራሲና ስለህዝብ መብት የተጨነቀ በማስመሰል ስለፓርላማውና ስለህገመንግስቱ ፀረዴሞክራሲያዊነት ያወራል፡፡ግን ወዲያውኑ ደግሞ ፀረዴሞክራሲያዊ የሆነ "ጠንካራ" የወታደር አገዛዝ በህዝቡ ላይ ያሰፍራል፡፡ሌላው ቢቀር ይህ "ጠንካራ" አገዛዝ ለምን ያህል ጊዜ ለማቆየት እንደታሰበ መገለጥ ነበረበት፡፡ ለምን አልተገለጠም?

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ሁሉ፣የጦር ኃይሎች ደርግ በሰኔ 26 የመንግስት ሥልጣን ሲይዝ ምንም ፕሮግራም አልነበረውም፡፡እስከመስከረም 2 ድረስ "የህዝቡን ድምጽ"እየተከተለ ብዙ ተራማጅ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቶ ኃይለ ስላሴን እንደገለበጠ "ከንግዲህ ወዴት"ለሚለው ጥያቄ የታሰበበትና የተጣራ መልስ ለማግኘት የቻለ አይመስለም፡፡ሥልጣኑን ተነስቶየቆ ያዘ ሃሳብ፣እንደሌሎች ሃሳቦች ሁሉ፣እንደአጋጣሚ ካንጮ ወይንም ከሌላው አማካሪው፣ምናልባትም ከያንኪዎች ከራሳቸው የመጣለት ሳይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን፡፡በራሱ የወሰነውና በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምክንያቶች የሚያምን ከሆነ ይህ እርምጃ ላገሪቷ ጊዜያዊ ችግሮች ምንም መፍትሄ እንዳይደለ በሚመጡት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሊረዳው ይቻላል፡፡ነገር ግን ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቀኝ እጅ ሆኖ የኃይለ ስላሴን ጉዳና ከተከተለ፣ወደፋሺስት አገዛዝ ይዟወራል፡፡ውሎ ይደር እንጂ የኃይለ ስላሴን ፍጻሜ ደርጉም ያገኘዋል፡፡

ወደመስከረም 2 አዋጅ ለመመለስ፣የአዋጁ ቁጥር 3 አለጋ ወራሹ ተመልሶ እንዲነግስ የሚጠይቀው አድሃሪ ነው፡፡ቁጥር 4 እና5 ስለፓርላማው መዘጋትና ስለአዲስ ህገመንግስት ተዘጋጅቶ መታወጅ የሚያወሩት አንቀጾች፣የወደፊቱ የ"እውነተኛ ወኪሎች"በህዝቡ መመረጥ እንዴት ሊመጣ እንደሚችልና ይህም ከድሮው የፓርላማ አመራረጥ በምን መንገድ "የበለጠ ዴሞክራሲያዊ"እንደሚሆን ካላመለከታቸውም በላይ፣የተባለው ህገመንግስት በምን ጊዜ ውስጥ ስራ ላይ እንደሚውል ፈጽሞ አይናገሩም፡፡እንዳልካቸው እንኳ በዘመኑ "በስድስት ወር ውስጥ"ብሎ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ወታደሩ ከነስሙ የመንግስት ስልጣን መያዙን የሚያስታውቀው የአዋጁ አንቀጽ 6 ነው፡፡"ሕዝቡ ህጋዊ እንደራሴዎችን መርጦ ህገመንግስቱ እስኪታወጅ መንግስት እስኪቋቋም ድረስ ወታደራዊው ደርግ የመንግስቱን ስልጣን ይዞ አገሪቱን

ይመራል"ይላል፡፡በዚሁ ቀን ስለመንግስት ባለሥልጣኖች ከደርጉ የተሰጠው ማስታወቂያ "በሚኒስትርነት ደረጃ የሚገኙ የካቢኔው አባሎችና ሌሎችም የመንግስት ባለሥልጣኖች ሁሉ አዲስ ውሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ባሉበት ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡"ይላል፡፡ይህ ከሆነ አዲሱ የመንግስት ሥልጣን ከመስከረም ሁለት በፊት ከነበረው ሁኔታ በስም ብቻ እንጂ በምን ይለያል?አሁን እንደሚነገረው ከሆነ በየገጠሩ "ንዑስ ደርግ" የሚባሉ የወታደሩ አገዛዝ ክፍሎች ተቋቁመዋል፡፡በነዚህ ደረጃም ሆነ በማእከላዊ መንግስት ደረጃ በወታደሩና በሲቪሉ አገዛዝ መሃል ያለው ግንኙነት ፍጹም ግልጽ አልሆነም፡፡የሆነ ሆኖ፣በጠቅላላው ባሁኑ ጊዜ ዋናው አዛዥ ያው ደርጉ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ከሁሉ ፀረዲሞክራሲያዊና ፈላጭ ቆራጭ የሆኑት አንቀጾች ቁጥር 8ና9 ናቸው፡፡ቁጥር 8 "ይህ አዋጁ እስከፀናበት ድረስ"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን አላማ የመቃወም አድማ የሚያደርግ፣ሥራ የሚያቆም፣ያለፈቃድ ሰላማዊ ሰልፍና ስብሰባ የማድረግ፣በጠቅላላው የህዝቡን ፀጥታና ሰላም የሚነካ ተግባር መፈጸም ክልክል ነው"ይላል፡፡/በነገራችን ላይ የአንቀጹ ሰዋሰው ለክ አይደለም፣ከዲስ ዘመን የተገለበጠ ነው፡፡/ አንቀጹ 9 በበኩሉ የጦር ፍርድቤት እንደሚቋቋምና የቁጥር ስምንትንም ሆነ ሌሎችን የደርጉን ትእዛዞች የሚያፈርስ በዚህ ፍርድ ቤት እንደሚፈረድበት፣ፍርዱም ይግባኝ እንደሌለው ይገልጻል፡፡ይህ የተባለው ፍርድ ቤት እስካሁን/መስከረም መጨረሻ/ ተቋቁሞ እንደሆን አናውቅም፡፡

የሆነ ሆኖ፣"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው መመሪያ ራሱ ያልተጣራ መሆኑን በሌላ ቦታ አመልክተናል፡፡በዚህ ዓይነት፣አንድ ሰው ይህንን "ዓላማ" ተቃወመ የሚባለው መቼ ነው? ምን ሲያደርግ ነው? የቁጥር ስምንት ይዘት ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ መሆኑን ለማስረዳት ጊዜና ወረቀት ማባከን አያስፈልግም፡፡ባጭሩ የመስከረም 2 የወታደር አገዛዝ አዋጁ በኢትዮጵያ ላይ መልሶ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን እንዳሰፈረ ግልጽ ነው፡፡እንግዲህ አሁን ያለንበት ሁኔታ ይህ ነው፡፡

የወታደሩ አገዛዝ "ጊዜያዊ የወታደር አገዛዝ" ተብሎ ቢሰየም፣በዚያው በመስከረም 2 የታወጁት "የደርጉ ዓላማዎች"ወታደሩ –ደርጉ– ሥልጣኑን ለረዥምና ላልተወሰነ ጊዜ ለመያዝ የተነሳ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ "ዓላማዎች"ከሞላ ጎደል የረዥም ጊዜ ፕሮግራም ናቸው፡፡"ጊዜያዊ" የሆነ አስተዳደር የመሬት ይዞታን አሻሽላለሁ፣የትምህርት የጤና ዘመቻን አደርጋለሁ፣ኢንዱስትሪን አስፋፋለሁ፣ወዘተ. እንዴት ለማለት ይችላል? "ከዓላማዎቹ"15 አንቀጾች በተለይ የመጨረሻው እንዲህ ይላል፡፡"ግንባር ቀደሙ ወታደራዊ ደርግ ለተነሳሳበት የአገር እድገትና አንድ



ነት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተባባሪ ሊሆን የሚገባው መሆኑን በማመን፣በፍርድ፣በእርሻ፣በአስተዳደር፣በንግድ፣በትምህርት፣በጤና ጥበቃ፣በማህበራዊ ኑሮ አገራችን ወደፊት ለተሻሻለና ለውጡ መሰረት ያለው እንዲሆን በማሰብ፣ወደፊት በሰፊው የሊገሪቱ መመሪያ/ፖሊሲ/ ይወጣል፡!ይኸ ታዲያ የረዥም ጊዜ እቅድ አይደለም ወይ? በነዚህ ሁሉ ምክንያት ይህ የወ የወታደር "ጊዜያዊ"አስተዳደር ምን ያህል እንደሚቆይ በትክክል ለማወቅ አይቻልም፡፡ ለጊዜው ግን በነዚህ የ15 ነጥብ "ዓላማዎች"ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎችና አደገኛ ይዘቶች ባጭሩ ለማመልከት እንፈልጋለን፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ ደርጉ "የማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩልነት...መብትና እድገት በሚገባ እንዲጠበቅለት ያደርጋል"ይላል፡፡እንዴት ለሚለው ጥያቄ የቀሩት 14 ነጥቦች በግልጽ ቋንቋ ይመልሷሉ ብሎ የሚጠብቅ አንባቢ 15ቱን ነጥቦች ሲወጣቸው እንደጠማው ይቀራል፡፡ከዚህ በላይ እንዳየነው 15ኛው ነጥብ "ወደፊት" ይላል፡፡ሁለተኛው የኘሮግራሙ ነጥብ በሀምሌ 2 ባዲስ ዘመን ከወጣው የ13 ነጥቦች መግለጫ ጋር ይመሳሰላል፡፡ያኛው ግልጽ እንዳልነበረ ሁሉ ይህኛውም ምን ለማለት እንደሚፈልግ ግልጽ አይደለም፡፡እነዚህ አንቀጾች ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ አጣዳፊ ጥያቄዎች አንደኛው የሆነውን የብሄረሰቦችን ጉዳይ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ሁለቱን ነጥቦች እናስፍር፡–

<u>የሀምሌ ሁለት መግለጫ</u>፡"በኢትዮጵያውያን መካከል ለብዙ ዘመናት የቆየውን በጎሳና በሃይማኖት የተመሰረተውን መለያየትና የኑሮ መራራቅ "ኢትዮጵያ ትቅደም"በሚለው እምነት በብሄራዊ ስሜትና በእኩልነት ለአገር እድገትና መሻሻል ዓላማ ህዝቡ ለሥራ ታጥቆ እንዲነሳና ለዘመኑ ሥልጣኔ በይበልጥ ተካፋይ እንዲሆን የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል"

የመስከረም 2መግለጫ፡"በኢትዮጵያውያን መካከል ለብዙ ዘመናት የቆየውን በጎሳና በሃይማኖት የተመሰረተውን መለያየትና የኑሮ መራራቅ "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚለው ዓላማ መሰረት ያስወግዳል፡፡"

እዚህ ላይ ቆም ብለን አንድ ነገር ማስተዋል አለብን፡፡የኃይለ ስላሴ መንግስት ከሃምሳ ዓመት በላይ የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች ሲጨቁንና ሲበዘብዝ የኖረው "በአንድነት"ስም ነው፡፡"ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን፣አማራ፣ጋላ ትግሬ፣ወዘተ. ምን አሰኘን" በማለት የብሄረሰቦች ጭቆና እንዳለ፣ከሸዋ አማራ በስተቀር የተቀሩት የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ የሁለተኛ ደረጃ ዜጎች ሆነው እንደቆዩ፣የእስልምና ሃይማኖትና ሌሎችም ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውጭ የሆኑ ሃይማኖቶች ሁሉ የሁለተኛ ደረጃ ሃይማኖቶች ሆነው መቆየታቸውን ለመሸሸግ፣ለመሸፋፈን የኃይለ ስላሴ መንግስት የማያቋርጥ ሙከራ አድርጓል፡፡የጦር ኃይሎች ደርግ "ኢትዮጵያ ትቅደም"በሚለው ተስምር የብሄረሰቦች

ጥቁና 'አስወግዳለሁ' ሲል፣ ለኢትዮጵያ ስትሉ ኦሮሞነታችሁን፣ ትግራይነታችሁን፣ ጉራጌነታችሁን፣ወዘተ. እርሱት፣ለቋንቋችሁ፣ለባህላችሁ መዳበር፣ደግሞ የራሳችሁን እድል በገዛ እጃችሁ ስለመወሰን ጉዳይ አትጨነቁ ማለቱ ስለሆነ፣ከኃይለ ስላሴ መንግስቱ የባሰ አደገና ይሆናል::እንደገና ለመድገም ያህል፣ በኢትዮጵያ ያሉት ብሄረሰቦች ሁሉ ተፈላልገውና ተፈቃቅደው እንዲኖሩ ከተፈለገ፣ ሙሉ እኩልነት እንዲኖራቸው አስቀድሞ ያስፈልጋል::ይህም እኩልነት የሚረጋገጠው ሁሉም ብሄረሰቦች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን መብት እንዳላቸው ሲታወቅ ብቻ ነው::በጉልበት ምንም አንድነት ሊመጣ አይችልም::

በሰስተኛው የዓላማዎች ነጥብ ውስጥ 'አንዳንድ ባህላዊ እምነቶች' የተባሉት የትኞቹ እንደሆኑ አልታወቀም::በተረፈ ግን፣'የግዛት አስተዳደር ዘይቤያችን ዘመናዊ' ማድረግ ስለሚለው አንድ ፍንጭ አግኝተናል ብለን እንገምታለን፣ ይኸውም 'ጠቅላይ ግዛት'በሚለው ፈንታ 'ክፍለ አገር' ማለት ወዘተ. ነው:: ይህ በውነቱ ምንም ለውጥ አይደለም::

ቁጥር አራት የመሬት ይዞታ እንደሚሻሻል፣ ቁጥር 5 ፍርድ ቀልጣፋ እንደሚሆን፣ስድስትና ሰባት የጤና የትምህርት ዘመቻዎች እንደሚደረጉ ያወራሉ:: ቁጥር 8 የሚናገረው በቀጥታም ባይሆን 'ስለዝሙት' እና ምናልባትም ስለመጠጥ ሳይሆን አይቀርም:: ቁጥር ዘጠኝ እንደ ቁጥር አንድ ሆኖ 'የህዝብ መብቶች' 'በህግ እንዲረጋገጡና እንዲከበሩ' ያደርጋል ይላል::በተረፈም፣ከ15ኛው ነጥብ በስተቀር፣የቀረት በጠቅላላው ፍቅርና 'ብሄራዊ ስሜት' እንዲኖሩ፣ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲተማመኑና ህብረት እንዲኖረን፣ የጅ ጥበብ ሥራና ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ደርጉ እንደሚያደርግ፣ያገር ቅርሶች እንዲጠበቁ የሚያትቱ ነጥቦች ናቸው::ባንድ በኩል፣ደርጉ እፈጽማቸዋለሁ የሚላቸውን ነገሮች፣ — የመሬትን ይዞታ ማሻሻል፣ኢንዱስትሪን ማስፋፋት፣ለምሳሌ — እንዴት ሊፈጽማቸው እንደሚችል አይታወቅም::ደርጉም ስለአፈጻጸሙ ምንም መንገድ አይጠቁምም::በሌላ በኩል ደግሞ 'ከለፉራል'፣'መተማመን'፣'ፍቅር'፣'ብሄራዊ ስሜት' የተሰበኩት ነጥቦች እንደእውነቱ ከሆነ በፖለቲካ ዓለም ቦታ የሌላቸው ነገሮች ናቸው::ለዚህ ለዚህማ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶችስ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ይሉት የለምን? ኃይለ ስላሴ ቢሆን በየጊዜው ሲናገራቸው የነበሩት ነገሮች 'እንደማር ወለላ' አልነበሩምን?

ለማንም በግልጽ እንደሚታየው፣ የደርጉ 'ዓላማዎች' ባንድ በኩል አንዳንድ አደገኛ ነጥቦች ሲይዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቀሩት ነጥቦች ተጨባጭነት የላቸውም::ያገሪቷ ችግሮች ግን በጠቅላላቸው ተጨባጭ ናቸው::ዓይናቸውን



አፍጣኝ መፍትሄ የሚጠይቁ ናቸው::ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ባሁኑ ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ የሚጠይቀው ዲሞክራሲያዊ ነጻነቶችን ነው፤ የመደራጀት፣ የንግግር፣ የመሰብሰብ፣ የመጻፍ፣ ወዘተ. ነጻነቶችን ነው::እነዚህ ነጻነቶች ካሁኑ ካልተሰጡ፣ሰፊው ህዝብ እንዴት አድርጎ ለመብቶቹ ይከራከራል? እንዴትስ አድርጎ ስለወደፊት እርምጃው ሊወያይ ይችላል? የዲሞክራሲ ነጻነቶች ጥያቄ፣ይህ በየካቲት በወታደሩ ጭምር ይጠየቅ የነበረው ጥያቄ፣አሁን ከወታደሩ መጠየቅ አለበት::በተረፈም፣ የቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥያቄዎች የታወቁ ናቸው:: 'መሬት ለአራሹ'፣ትምህርት ለሁሉም፣ የጤና ጥበቃ ለሁሉም፣ የብሄረሰቦች የሃይማኖቶችና የጾታዎች እውነተኛ እኩልነት፣...እነዚህ ሁሉ ሰፊው ህዝብ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ናቸው::

እነዚህ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ሊከናወኑ የሚችሉት ባላባታዊ ስርዐትና ኢምፔሪያሊዝም ሲደመሰሱ ብቻ መሆኑን ካሁኑ ለማስታወስ እንወዳለን:: የጦር ኃይሎች ደርግም ሆነ መላ ሠራዊቱ እነዚህን ሁለት የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅ ጠላቶች ፈጽሞ ለመደምሰስ አይችልም::ይህንን ሊያደርግ የሚችለው ሰፊው ህዝብ ራሱ ብቻ ነው:: ስለሆነም፣ህዝቡ የመደራጀትና በነፃ ሃሳቡን የማቅረብና የመከራከር መብቶች እንዲታወቁለት ያስፈልጋል::

ኃይለ ስላሴ እንደወደቀ ከሥራ ላይ ይውላሉ ተብለው ሲጠበቁ የነበሩትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ሠራዊቱ ራሱ ስድስት ወሮች ሙሉ ሲጠይቃቸው ከቆየ በኋላ፣አሁን እርሱ ራሱ እነዚህን የህዝብ መብቶች ገፏል::በጠቅላላውም ደርጉ በአሁኑ ጊዜ በሚወስዳቸው መብቶች አድሃሪ መንገዱ ለመያዙ ምንም ጥርጥር የለውም::ባገር ቤት ጓዶች አስተያየት፣ይህንን ጎዳና ደርጉ የያዘው፣በቀጥታ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የስለላ ድርጅት፣ በሲአይ ኤ ስር ስለወደቀ ነው::የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ፀረ ሬቮሉሽናዊ ድርጅቱ አማካይነት የየካቲትን እንቅስቃሴ ቀለበስ ለራሱ ዘረፋና ጭቁና ለማዋል እንደሚጥር ምንም ጥርጥር የለውም::

በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት አገሪቷን በእጅ አዙር ቅኝነት የያዛት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣አሁንም በቦታው እንዳለ ነው::ከጥንቱም ቢሆን የሠራዊቱ አሰልጣኝና መሳሪያ አቅራቢ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እንደሆነ ይታወቃል:: አሁንም ቢሆን፣በሰኔ 26 ቀን ወታደሩ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ፣ ስኤታ ማዦር ሹምነት፣ በራሱ ላይ በዚሁ ቀን የአሜሪካኖች ታማኝ የሆነውን አማን አንዶምን ሾሞታል:: አማን እንደተሾመ ከሰራቸው የመጀመሪያ ነገሮች አንዱ በኢትዮጵያ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ወታደራዊ 'አማካሪ' የሆነውን ደናልድ ደው የተባለውን ጄኔራል ተቀብሎ ማነጋገር ነበር::

ከዚህ ግንኙነት በኋላ ያሜሪካን የጦር እርዳታ እንደሚቀጥልና በሁለቱ መካከል የነበረውም ወታደራዊ ትብብር የማያቋርጥ መሆኑ ተነገሯል። በዚያው ሰሞን በዓለም ጋዜጦች እንደተነገረው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ለኢትዮጵያ አዲስ ገዥዎች የመቶ ሚሊዮን አሜሪካን ብር መሳሪያ ለመስጠት ተስማምቷል። ይህ አድራጎት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በደርጉ ላይ ያለውን እምነት ያሳያል።

አንዳንድ የምእራብ ጋዜጦች እንደሚያወሩት ከሆነ፣ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይህን ያህል "እርዳታ" ለመስጠት "የተገደደው" ሶቬየት ህብረት ለሶማሊያ ሪፐብሊክ ብዙ ዘመናዊ አውሮፕላኖችን፣ በተለይም ሚግ 21 የተባሉትን የጦር አውሮፕላኖች በርከት አድርጉ ስለሰጠ ነው ይላሉ። የሶማሊያ መንግስት በርግጥ የተባለውን መሳሪያ ሁሉ ተቀብሉ እንደሆነና በርግጥም ለጦርነት ባመዘጋጀት ላይ እንደሆነ አናውቅም። እኛ የምንለው፣ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ህዝቦች ወንድማማች ህዝቦች ስለሆኑ በሰላምና በመልካም ጉርብትና አብሮ የማይኖሩበት ምክንያት የለም ነው። ስለዚህም፣ ሁለቱም ህዝቦች በየመንግስቶቻቸው በኩል የሚያደርጉትን መሰናዶዎች መቃወም አለባቸው እንላለን። የኦጋዴን ህዝብ የራሱን የወደፊት እድል ለመወሰን መብት አለው። ይህ መብቱ እንዲታወቅለትና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የወሰን ክርክር በሰላም መንገድ እንዲፈታ መጠየቅ አለብን።

ለማንኛውም ግን፣ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሆነ ሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለኢትዮጵያ የመሳሪያ "እርዳታ" ቢያደርጉ፣ ወይንም ወታደራዊ "ትብብርን" ቢያሳዩ፣ የኢትዮጵያን ህዝቦች ብሄራዊ ነፃነት እንደለማዷቸው ለመገፈፍ ብለው ነው እንጂ፣ ለኢትዮጵያ ደህንነት አስበው እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት። የአገሪቷን ብሄራዊ ነጻነት ሊያስጠብቅ የሚችል የኢምፔሪያሊስቶች መሳሪያ ሳይሆን የህዝቦቿ የራሳቸው የፖለቲካ ንቃትና ድርጅቶቻቸው ናቸው። ባሁኑ ጊዜ ግን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚሰጠው መሳሪያ አንዳች የውጭ ጠላትን ለመከላከል ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝቦች ራሳቸውን "ጠንካራ አስተዳደር" በሚል ለመጨፍጨፍ እንዲቻል ነው። ደርጉ ሥልጣኑን የያዘው "ለቀ ለቀ የፀጥታ ችግሮች" ስለተፈጠረ ነው ብሉ የለም ወይ? የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሁለት መቶ ሃምሳ ሚልዮን የኢት. ብር "እርዳታ" በመሳሪያ መልክ የሰጠው ለዚህ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝቦች ማወቅ አለባቸው። ትናንት የኃይለ ስላሴ መንግስት "በአንድነት" ስም የኤርትራን ህዝብ ሲጨፈጭፍ ቆይቷል። የጎጃምን፣ የትግራይን፣ የባሌን፣ የኦጋዴንንና የሌሎችንም ግዛቶች ህዝቦች በልዩ ልዩ ጊዜያት



እንደዚሁ በፋሺስታዊ አቋሙ ጨፍጭፏል። ዛሬ፣ ያ ትናንት በንጉሡ ትእዛዝ ሲጨፈጭፍ የነበረው ሠራዊት፣ በገዛ ስልጣኑ ህዝቦቹን መጨፍጨፍ ይዟል። በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እርዳታና የበላይ ጠባቂነት።

በሰኔ 22 የተጀመረው የሠራዊቱ እንቅስቃሴ ኃይለ ስላሴን አስከገለበጠበት ቀንና እርሱንም በመገልበጡ በርከት ያሉ እርምጃዎችን ወስደ ነበር። እንዲያውም አለፍ አለፍ በጻፋቸውም አንዳንድ ነገሮች ከዚህ በላይ በአንድ ቦታ እንደጠቀስነው ሁሉ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት አስከመምሰል ደርሶ ነበር። በመስከረም ሁለት የወጣው የውጭ ፖሊሲ መግለጫውም የመጀመሪያ ነጥብ "የውጭ ፖሊሲያችን በገለልተኝነት እምነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ይኸው የገለልተኝነት እምነት በስም ብቻ ሳይሆን በግብርም ይገለጣል" ስለሚል፣ ያንኬያችን ሳያስደነግጥ አልቀረም። ይሁንናም ከመስከረም ሁለት ወዲህ ሲአይኤና የደርጉ የውስጥ አድሃሪ ኃይሎች የወታደር አስተዳደሩን ፈላጭ ቆራጭነት ሳይመሰርቱ አልቀረም።

ሲአይኤ በህጋዊ መንገድ ተመርጦ የነበረውን የቺሌን ፕሬዚዳንት አሌንዴን ገለበጧል። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1967 የግሪክን ህጋዊ መንግስት በጉልበት ገልብጦ ፋሺስቶች ስልጣኑን እንዲይዙ አድርጓል። ዛሬ የፖርቱጋል መንግስት ውስጥ ሲአይኤ ገብቶ ወታደሩን እንዳይከፋፍል ያሰጋል። እንግዲህ ይኸው ሲአይኤ በአገራችን የደርጉን አመራር ይዞ ፋሺስታዊ አገዛዝን በኢትዮጵያ ላይ በማስፈር ላይ ነው ማለት ነው። ለመሆኑ ይህ ፀረረቮሉሽናዊ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የስለላ መሳሪያ እንዴት ነው የሚሰራው?

እንደእውነቱ ከሆነ፣ ሲአይኤ የሚሰራው "የስለላ" ሥራ ብቻ አይደለም። "ስለላ" ማለት የአንዱን አገር ምስጢሮች አውቆ ለገዛ ራስ መንግስት ማስተላለፍ ከሆነ ሲአይኤ በቀጥታ በአንድ አገር የውስጥ ጉዳዮች ገብቶ፣ ፖርቲዎችን፣ ግለሰቦችን፣ የህዝብ ክፍሎችን በዶላር እየገዛ ወይ ለመከፋፈል ወይ አንዱን ገልብጦ የሚስማማውን ከስልጣን ላይ ለማውጣት፣ ወዘተ. ሊሰራ ይችላል። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ህዝቦች ዋና ጠላት እንደመሆኑ መጠን፣ ይህ ፀረረቮሉሽናዊ መሳሪያው በሁሉም አገር እጁን ያገባል፣ ወይንም ለማግባት ይሞክራል። እርስ በርስ ያጋጫል፣ ይበታትናል፣ አንዳንዴም የፖለቲካ ሰዎችን ያስገድላል፣ የማይሰራው ተንኮል የለም። በቺሌና በግሪክ የፈጸማቸው ወንጀሎች አሁን በይፋ ወጥተዋል። በተረፈም፣ የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ፎርድ እኤአ በመስከረም 17 1974 ባደረገው የጋዜጦች ጉባኤ ላይ "ሲአይኤ በቺሌ

እንዲገባ የተፈቀደው እሉንዲ ተቃዋሚዎቹን ፓርቲዎች ለማጥፋት ስለተነሳ ነው'በማለት፣
እሉንዲን የገለበጡት ያንኪዎች መሆናቸውን አምኗል፡፡ይሁንናም፣እሉንዲን ለመገልበጥ
ሶስት ዓመትና ወደ24 ሚሊዮን የአሜሪካን ብር እንደፈጀባቸው ይነገራል፡፡

እንድርያስ ፓፓንድሬው የተባለው፣አባቱ የግሪክ ጠ/
ሚኒስቴር የነበረው የግሪክ የፖለቲካ ሰው በጻፈው መጽሀፍ ውስጥ ሲአይኤ እንዴት የግ
ሪክን መንግስት እኤአ 1967 እንደገለበጠ በዝርዝር ይናገራል፡፡መጀመሪያ ነገር
'የቀኝ/ፋሺስታዊ/ የሆኑትን የፖለቲካ ሰዎች ገዝቶ የመንግስትን ስልጣን ከፓፓንድሬው
እንዲቀሙ አደረገ፡፡ከዚያ በኋላ በቀጥታ የግሪክ የፀጥታ ክፍል አባላት የሆኑት እነ
ፓፓዶቡሎስ ይኸናውንም መንግስት ገለበጠው ፋሺስታዊ ፈላጭ ቆራጭነትን በግሪክ ህዝብ
ላይ እንዲያሰፍር አደረገ፡፡'

በኢትዮጵያም ሲአይኤ በጥቂት መቶ ሺህ የአሜሪካን
ዶላር ከደርጉ ውስጥና ውጭ ብዙ ሰዎች ሊገዛ እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡
ባሁኑ ወቅት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ዓላማ የየኪቲት እንቅስቃሴ እነሱ ከሚፈልጉት
ርቆ እንዳይሄድ፣በተለይም በወታደሩ ውስጥም ሆነ በጠቅላላው ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት
አገር ወዳዶች 'ኮሙኒስት'እየተባሉ እንዲደመሰሱ ማድረግ፣ባገሪቱ ሊደረግ የሚችለው
ማንኛውም ለውጥ የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም እንዳይነካ ማድረግ ነው፡፡ለዚሁም ወታደሩን
እርስ በርስ ለማጋጨት፣ለአገር አሳቢ የሆኑትን ሁሉ ሰብስቦ ለማሰርና በኋላም ለመፍጀት
ሲቪሉንም እንዲሁ እርስ በርስ ለማጣላት፣ሬቮሉሽናዊ ግሩፖች ውስጥ ሁሉ በመግባት ለመ
ከፋፈል፣ሬቮሉሽናዊ እየመሰሉ ፀረሬቮሉሽን ማሰራት፣ ይህ ሥራቸው ይሆናል፡፡

የሲአይኤን ስራ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ፣በተለይም
ከሁሉ የነቃው የህብረተሰባችን ክፍል፣ነቅቶ ማክሸፍ አለበት፡፡መቸውንም ቢሆን በገንዘ
ብና በገል ጥቅም አገራቸውን ለባእድ ሸጠው የማያውቁት በብዙ ደምና መስዋእት ያገሪ
ቷን ነፃነት ያስጠበቁ የኢትዮጵያ ህዝቦች የያንኪዎችን ከአገራችን ተጠርጎ መውጣት
ካሁኑ መጠየቅ አለባቸው፡፡በተለይም ከህዝቡ ክፍሎች የተደራጁት ወገኖች፣ተማሪዎች፣
አስተማሪዎች፣የሠራተኛው ማህበራት፣ወዘተ. የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ከአገራችን መወ
ገዱ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ደግሞም ይህ የህዝቦች ሁሉ ጠር በአገሪቱ ላይ የሚያደርሰውን
ጉዳት ለሰፊው ህዝብመግለጽ ግዴታቸው ነው፡፡ኢምፔሪያሊስቶች ከአገራችን እንዲወጡ እን
ጠይቅ፡፡ይህንን ጥያቄ ተራማጅ የሆነው የዓለም ህዝብ በሙሉ ይደግፈናል፡፡



ቀደም ብለን ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩና ያን
ኪዎች ከአገራችን እንዲወጡ መጠየቅ እንዳለብን ገልጸናል፡፡በነዚህ ነጥቦች ዙርያ ላይ
እንመለስበታለን፡፡አሁን ግን የመንግስትን ስልጣን በሚመለከተው በኩል እስካሁን የቀረ
ቡትን ሃሳቦች ከዚህ በታች እንተነትን፡፡

__________ xxxx __________

አገሪቱ ከንጉሡ ወዲት መራመድ አለባት?የሚከተለው
እርምጃ ምን መሆን አለበት?ለነዚህ ጥያቄዎች ከነቀትና አሳባቸውን ለመግለጽ እድል ካላ
ቸው የህዝብ ክፍሎች —ማለትም አስተማሪዎች፣ተማሪዎች፣የኢስላም መሪዎች — ዛሬ ተደጋ
ግሞ የሚቀርበው ሀሳብ'ህዝባዊ ጊዜያዊ መንግስት' ወይንም 'ጊዜያዊ የሞግዚት መንግስት'
የሚባለው በፍጥነት ይቋቋም በተቻለ ፍጥነት እንዲቋም የሚል ነው፡፡ከዚህ በታች በዝርዝር
እንደምንመለከተው ሁሉ፣ ስህተተኛነቱን ወደጐን ብንተው እንኳ፣ይህ ሃሳብ በማያሻማ አኳ
ኋን ተጣርቶ አልቀረበም፡፡ይሁንናም ባሁኑ ጊዜ፣ ከጠቅላላው ተራማጅ የኢትዮጵያ የህዝብ
ክፍል/እና እስካሁን እስከምናቀውድረስ/ ካውሮፓው የኢትዮጵያ ተማሪዎች በስተቀር
ሁሉም በነገሩ'አስፈላጊነት' ተስማምቶበታል፡፡

እዚህ አውሮፓ የዚህ የ'ሞግዚት መንግስት'/ኬር ቴከር
መንግስት/ ሃሳብ ለመጀመሪያ የቀረበው — እና እስከምናውቀው ድረስ — በሚያዝያ1966
በአውሮፓ ተማሪዎች ማህበር ቅርንጫፍ ማህበራት መሪዎች ስብሰባ ላይ ነበር፡፡በዚሁ ስብ
ሰባ ላይ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ለውይይት በቀረበበት ጊዜ፣አንዱ የስብሰባው ተሳታፊ
'ሞግዚት መንግስት'መጠየቅ አለብን የሚል አሳብ አቀረበ፡፡እንደእውነቱ ከሆነ፣አሳቡን
ጠዋት አቅርቦት ከሰዓት በኋላ ሻረው /'ሳበው'ይባላል በአውሮፓ/፡፡ጉዱ ይህን ሃሳብ
ከየት እንዳፈለቀው ማወቅ አስቸጋሪ ነው፣ደግሞም ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም፡፡
ጉዱ ምናልባትበሚያዝያ 8 ቀን 1966 በአዲስ አበባ የተጻፈ 'መፍትሄው ጊዜያዊ መን
ግስ ነው' የሚል በራሪ ወረቀት ባዲስ አበባ ተሠራጭቶ ስለነበር አሳቡን ያቀረበው በዚያ
ላይ ተመስርቶ ሊሆን ይችላል፡፡/በነገራችን ላይ ይህ በራሪ ወረቀትም ቢሆን የጊዜያዊ
መንግስቱን አቋቋም አጣርቶ አላቀረበም፡፡ትግላችን ጥር 4.1966 መመልከት/

ይህ'የሞግዚት መንግስት'አሳብ እንደቀረበ፣ከዚህ በላይ
በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ ከነበሩት በርከት ያሉ የአውሮፓ ማህበር አባሎች የአሳቡን መሰ
ረተ ቢስነት ወዲያው ለማሳየት ሞክረዋል፡፡በዚያን ጊዜ የነበረው ዋና የክርክር ነጥብ፣
ሰፊው ሕዝብ የራሱን የፖለቲካ ድርጅቶች ባላቋቋመበት ቦታ፣'ሞግዚት መንግስት'ምረጥ

ማለት በባዶ ቦታ ሰፊውን ህዝብ ከያዘው ሬቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ወደማይረባ "ምርጫ"፣ ከህገወጥ ሬቮሉሽናዊ ድርጊቶች ወደህጋዊ ጥገናዊ ድርጊቶች ማዞር ነው የሚል ነበር:: የዚህን ሃሳብ መሰረተ ቢስነት ለማሳየት የተነገሩ ብዙ ነጥቦች ነበሩ::ግን አንዱ ቀላል ጥያቄ፣ የዚያን ጊዜ ሆነ ዛሬ፣ህዝቡ ከመደራጀቱ በፊት ምረጥ ቢሉት ማንን ይመርጣል? በዚህ ጥያቄ ላይ ከታች እንመለስበታለን::በበኩላችን በጠቅላላው በውጭ አገር ስለነበረው ክርክር ያውሮፓን ማህበር ሪፖርቶችና መጽሄቶች አንባቢው እንዲያነብ እየጋበዝን ስለጥያቄው ባጭሩ እዚህ ላይ እናወሳለን::

"የሞግዚት መንግስት"ወይንም "ጊዜያዊ መንግስት" ወይንም "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" ሃሳብ ከሚያዝያ ወር ወዲህ ብዙ ደጋፊያችን አገኝቷል::እዚህ ውጭ አገር፣በአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር ረዘም ላለ ጊዜ ካመነታ በኋላ ሃሳቡን ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ ተቀብሎታል::አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪያችና የአስተማሪያች "የውይይት ማህበር" ሃሳቡን ተቀብለውታል::ኢሰአማም አሁን በመስከረም መጀመሪያ ላይ ባደረገው ጉባዔው ይህንኑ አሳብ በመደገፍ የተባለው መንግስት እንዲፈጠር ጠይቋል::ሃሳቡ ብዙ ድርጅቶችን ማርኳል ማለት ነው::የቀረው የአውሮፓ ማህበር ብቻ ነው::ይህንን ማህበር በሚመለከተው በኩል ከላይ ያለውን ለአንባቢ እያስታወስን፣ አሁን ግን እስካሁን ካገር ቤቱ የቀረቡትን ይህንን ጥያቄ የሚመለከቱትን አሳቦች ወደ መተንተን እንሸጋገራለን::

ከላይ ከተጠቀሰው በራሪ ወረቀት በኋላ፣ስለጊዜያዊ መንግስት ተቀናብሮ የቀረበ አስተያየት/እና እስከምናውቀው ድረስ/ የኢትዮጵያ የዩኒቨርስቲ መምህራን "የውይይት ማህበር" የሚባለው ድርጅት በሀምሌ 18 ቀን 1966፣እንዳልካቸው እንደወደቀ ሚካኤል እንደተካው ለጦር ኃይሎች ደርግ ያቀረበው ጽሁፍ ነው::

ይህ ጽሁፍ በመጀመሪያ ክፍሉ የየካቲት እንቅስቃሴ እንዲመጣ ያደረጉትን ምክንያቶች ተንትኖ ከዚያም በደርጉ አጻጻፎች ላይ አንዳንዱ ተገቢ ሂሳቦችን ካቀረበ በኋላ ስለጊዜያዊ መንግስት የሚከተለውን በሰፊው የምንጠቅሰውን ያቀርባል::

> "አሁን ሳለንበት ሁኔታም የሚበጀው የህዝብ ተሳትፎና ሙሉ ድጋፍ ያለው ጊዜያዊ መንግስት ሲቋቋም ነው ብለን እናምናለን::ስለዚህ በአስቸኳይ ጊዜያዊ መንግስት እንዲቋቋም አጥብቀን እንጠይቃለን::...ጊዜያዊውም መንግስት በሚከተለው ሁኔታ እንዲቋቋም አሳብ እናቀርባለን::
>
> ሀ. ከልዩ ልዩ ክፍሎች— ማለትም ከጦር ኃይሎች፣ከሠራተኛው ማህበሮች፣ከመምህራን ማህበሮች፣ከመንግስት ድርጅቶችና ከህግ መምሪያ ምክር ቤት



> በተመረጡ ህዝቡን በሚወክሉ አዋቂያች "ልዩ ደርግ"ይቋቋማል:: የዚህ "ልዩ ደርግ" ተግባሮች የሚከተሉት ይሆናሉ:— ..."

ይልና የተባለው ደርግ ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲመርጥ፣ይህም ጠቅላይ ሚኒስትር ጊዜያዊ መንግስት እንዲያቋቁም፣ይህም መንግስት በልዩ ደርጉ ቁጥጥር ስር እንዲሆን ይገልጻል::በበኩሉ "ጊዜያዊው መንግስት" የሚኖሩት ስራያች መሰረታዊ የፖለቲካ መብቶችን፣ ከስራ ላይ ማዋል፣የፀጥታ ድርጅትን ማጥፋት/በነገራችን ላይ ይህ ደርግ አሁን የሚሰራው ለደርጉ ነው::/፣የህገመንግስቱን ንድፍ ለህዝቡ ለውይይት ማቅረብ፣የተያዙትን ወደፊትም የሚያዙትን የቀድሞ ባለሥልጣኖችን ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግና "ወደፊት በህዝብ ተሳታፊነት በህዝብ ድምጽ ተመርጦ ሥልጣን ለሚይዘው ሕዝባዊ መንግስት አስፈላጊውን ዝግጅት ማከናወን"ና ቸው::

እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው፣የመጀመሪያው ነገር፣የልዩ ደርጉ አባሎች ይሆናሉ የተባሉትን ሰዎች "በህዝብ ተሳትፎና ሙሉ ድጋፍ" የተመረጡ "ህዝቡን የሚወክሉ አዋቂያች" ናቸው ብለው ቢቀርቡም እነርሱ ግን በርግጥ ሊወክሉ የሚችሉት ትንሽ ከበርቴውንና ምናልባትም የቢሮ ከበርቴውን መሆኑን ነው::ከጦር ኃይሎች የሚመረጡት የትንሽ ከበርቴው መደብ አባሎች ይሆናሉ::ደግሞም እነዚህ በሰኔ 26 ስልጣኑን የያዙት "የጦር ኃይሎች" ይህን ስልጣን ከሌላ የመደብ ጓደኛ ጋር ሊካፈሉት ፈቃደኛ ይሆናሉ ብሎ ሊያስገምት የሚችል ምን ምክንያት አለ? የሠራተኛ ማህበሮች የተባለው ኢሰአማ ሲሆን፣ሁሉም እንደሚያውቀው የኢሰአማ መሪያች ፈጽሞ ወዝአደሩን የሚወክሉ፣ ሌላው ቢቀር በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንኳ ያልተመረጡ፣የተሾሙ ሰዎች ናቸው::የመምህራን ማህበሮች፣የመንግስት ድርጅቶች/ሚኒስቴሮች?/፣የፓርላማ አባሎች የተባሉት ለልዩ ደርጉ ሊያበረክቱ የሚችሉት ትንሽ ከበርቴያቸውን፣ምናልባትም የቢሮ ከበርቴን ነው::በተጨማሪም ምናልባትም ዝቅተኛ ካሳባትን ነው::እንግዲህ ለዚህ ለዚህ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለገበሬውና ለወዝአደሩ ልዩነቱ ምንድን ነው? በተረፈም፣"በህዝብ ተሳትፎና ሙሉ ድጋፍ" የቆመ መንግስት ነው ብሎ እራሱን የኃይለ ሥላሴን ፈላጭ ቆራጭ ጉዳና፣አሁን ሠራዊቱ የያዘውን ጉዳና የማይከተልበት ምን ዋስትና አለ?

ሁለተኛውና ከዩኒቨርሲቲ አስተማሪያች የማይጠበቅ የዚህ ሃሳብ ጉድለት፣አስተሳሰቡ ራሱ በዝርዝርና በተጣራ አኳኋን አለመቅረቡ ነው::ሠራዊቱ፣መምህራን፣ኢሰአማ፣ፓርላማውና ሚኒስቴሮች/"የመንግስት ድርጅቶች"እነሱን ማለት ከሆነ/ በተባለው ደርግ ውስጥ እኩል ድምጽ ይኖራቸዋል ወይ ደግሞስ የመወከል ነገር ከተነሳ አይቀር በየካቲት እንቅስቃሴ የተሳተፉት የህብረተሰብ ክፍሎች — ለምሳሌ የእስላም

ሃይማኖቶች ተከታዮችን፣ዘቀተኛ ነጋዴዎችን፣የመሬት ገበሬዎችን፣የጅማ ነዋሪዎችን፣ወዘተ...— ለምን አልተጠቀሱም? በደርጉ ውስጥ ስንት አባል ሊኖር ይችላል?ወይንም ሊኖር ይገባል? ሃሳብ ማቅረብ ብቻ አይበቃም፣ሃሳቡ በቀጥታ ከሥራ ላይ የሚውልበትንም ዘዴ ዘርዝሮ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።በተረፈም፣ልዩ ደርጉና በርሱ የሚመረጠው መንግስት ይፈጽሙታል ለተባለው ሥራ ከሠራዊቱ ቁጥጥር በምን ዓይነት ነፃ ይሆናል? ነፃካልሆነ ደግሞ፣ሠራዊቱ ከላይ አሁን እንዳለ አዟዥ ሆኖ በሀምሌ ፪ ገለጻት እንደነበረው ሁሉ "የማያስፈጽምበት"ምክንያት አልታየንም።እነዚህን ለማስፈጸም ሠራዊቱ ራሱና ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም እንደመሰናከል ካልታዩ ማለታችን ነው።

ያዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርና ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴም ባቀረበው ውስጥ ይህ በዩኒቨርሲቲው መምህራን "የውይይት ማህበር" የቀረበው "የልዩ ደርግ"አሳብ ተመልሶ ይመጣል።አስተማሪዎች "ልዩ ደርግ" ያሉትን፣ተማሪዎች ደግሞ በሀምሌ 23 ለጦር ኃይሎች ደርግ በጻፉት ወረቀት ውስጥ "ከፍተኛ ደርግ"ይሉታል። እንደሚከተለው ይጸፋሉ።

> "በአሁኑ ጊዜ ወታደራዊው ደርግ ከሁሉም በማስቀደም፣ከኢንዱስትሪና ከመንግስት አገልግሎት ድርጅቶች ሠራተኞች፣ከገበሬው፣ከምሁራንና ከሌሎች የሲቪል መደቦችና ከፍሎች የተውጣጣ ከፍተኛ ደርግ/ምክር ቤት/ስርዝ የነሱ/ አስመርጦ መመስረትና ሙሉ የወታደር ድጋፍ እንዲያገኝ አሁን ካለው የወታደራዊ ደርግ ጋር መቀላቀል ያስፈልገዋል።..."

ይህ ከፍተኛ ደርግ ጊዜያዊ መንግስትን እንዴት እንደሚያቋቁም ከጓዶቹ ጽሁፍ ፈጽሞ ግልጽ አይደለም። ዝቅ ብለው "...ጊዜያዊ መንግስት የሚመሰረተው እንደተባለው በልጅ ሚካኤል እምሩ የሚመራው ካቢኔ መሆኑ ቀርቶ፣የገለጸነው ከፍተኛው ደርግ /ምክር ቤት/ና አዲስ የተመረጠው ካቢኔ ጥምር መሆን ይኖርበታል።" ከፍተኛ ደርጉ ጠቅላይ ሚኒስትር ይመርጣል ብለዋልና እንግዲህ ምናልባት እዚህ ላይ"አዲስ የሚመረጠው ካቢኔ" የሚባለው ይህ ከፍተኛ ደርግ እራሱ የሚያቋቁመውን ይሆናል።ለማንኛውም፣ጊዜያዊ መንግስት የሚባለው "ከፍተኛ ደርጉ"ካቢኔው አንድነት ተደምሮ መሆኑ ነው። ግልጽ አይደለም። ግን ይመስላል።

እዚህ ላይ የከፍተኛው ደርግ አመራረጥ ካስተማሪዎች "ልዩ ደርግ"አመራረጥ የባሰ የተምታታ መሆኑን እናስተውል።"ከኢንዱስትሪና ከመንግስት አገልግሎት ድርጅት ሰራተኞች"ምርጫ ለማድረግ ይቻላል እንበል።ግን ከየትኛው ገበሬ



ከየትኛው ምሁር፣ከየትኛው "የሲቪል መደብ" ተብሎ ሊመረጥ ነው? /በነገራችን ላይ፣ "ሲቪል መደብ"ምን ማለት ነው።/

ለማንኛውም፣እነዚህም ጓዶች፣የጊዜያዊው መንግስት ሥራ ነው ብለው የሚያቀርቡት ነገር የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መፈቀድና ከሥራ ላይ መዋል ነው። የዚህን ጊዜያዊ መንግስት "ጠቃሚነት" በዚሁ ወረቀታቸው ውስጥ ሲገልጹ፥—"አሁን ባለው ሁኔታ ህዝቡና ወታደሩ በመራራቃቸው፣በመሃከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን ጥርጣሬ አስወግዶ በእምነት ላይ የተመሰረተ ህብረትና ድጋፍ በመፍጠር ንቅናቄውን ከታሰበበት ግብ ለማድረስ ስለሚረዳ ..."ነው ይላሉ።/ሥርዝ የነሱ/ከአስተማሪዎች ሆነ ከተማሪዎች የ"ጊዜያዊ መንግስት"አሳብ የቀረበው፣ወታደሩ ሥልጣኑን ወስዶ ለራሱ ያስቀራል በሚል "ጥርጣሬ" ነበር ብለን እንገምታለን።ግን ከመጀመሪያውስ ቢሆን ሰፊው ህዝብ ባልተደራጀበት ቦታ፣ እንዳቸም ህዝቡን ለማሰለፍ የሚችል ፓርቲ በሌለበት ቦታ ወታደሩ ስልጣኑን እንዳይዝ ምን ይከለክለዋል? ደግሞስ የዚያን ጊዜስ ቢሆን ከሰኔ 26 ጀምሮ ሥልጣን ይዞ አልነበረም ወይ? እዚህ ላይ ተጠረጠረ አልተጠረጠረ ምን ልዩነት ያመጣል?የተባለው ጊዜያዊ መንግስት ቢቋቋምስ ሠራዊቱ ባስፈለገው ጊዜ እንዳይፈነቅለው ምን ዋስትና አለ? የጊዜያዊ መንግስት ፈላጊዎች የረሱትና ደጋግመን መግለጽ የአለብን ነገር፣ሰፊው ህዝብ ያለድርጅት ምንም ሊያገኝ እንደማይችል ነው።ይህን ሀቅ በደንብ ቢገነዘቡት ኖሮ"ገና ከየካቲት፣ ከመጋቢት ጀምሮ ያወርጋ ማህበር እንዳደረገው ሁሉ፣ከኃይለ ስላሴ ሆነ ከእንዳልካቸው፣ከሚካኤል ሆነ ከደርጉ በቀድሚያና በፍጥነት የዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከስራ ላይ መዋል በጠየቁ ለዚህ ዲሞክራቲክ መብቶች የሚደረገውንትግል ህዝቡ እንዲያፋፍም በቀሰቀሱ፣እንዲሁም በዚህ ትግል ውስጥ በተደራጁና ህዝቡንም ባደራጁ ነበር።አሁንም የግድ ወደዚያው መመለስ ያስፈልጋል።

መቼስ ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው የመደቦች ትግል በተለይ ቦግ ብሎ የሚታየው በትንሽ ከበርቴው ውስጥ ሆኖ ሳለ፣አንዳንዱ ጊዜ የሚያስደንቁ ውጤቶችን ይሰጣል።አሁን ለምሳሌ፣በመስከረም ሁለት ኃይለ ስላሴን ገልብጦ "ጊዜያዊ የወታደር አስተዳደርን"በተጠየቀው "ጊዜያዊ መንግስት"ቦታ ያቋቋመው ደርግ፣ ዘር ዘር የሲቪል ደርግን ወይንም ከፍተኛ ደርግን አሳብ በመሰረቱ ብዙ በማይለይ ሁኔታ ሊቀበለው ነው።ከነዚህ ከተባሉት ብዙም የማይለይ አካል ሊፈጥር ነው።ምናልባት ኢሰአመ በምሁራንና በተማሪዎች ላይ ተደርቦ በመስከረም 6 ጉባዔው "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን" መቋቋም ስለጠየቀ ሊሆን ይችላል፣በመስከረም 13 ደርጉ ባወጣው አዋጅ መሰረት"አማካሪ ጉባዔ"ይመረጣል። የዚህ "ጉባዔ"ሥራ ግን "ጠቅላይ ሚኒስትር"መርጦ ጊዜያዊ መንግስትን

ሚሿቸው ሳይሆን ደርጉን መምከርና ምናልባትም ሌላ ህገመንግስት ማዘጋጀት ይሆናል:: ምርጫው ቢፈጸም ለማየት እንደሚቻለው ሁሉ፣ የዚህ ጉባዔ አባሎች የወዝአደሩና የገበሬው እውነተኛ ወኪሎች ሳይሆኑ የትንሽ ከበርቴው፣ የቢሮ ከበርቴውና የነፍጠኞች የዘቀተኛ ባላባቶች ወኪሎች ይሆናሉ:: ለሰርቶ አደሩ ህዝብ ምንም ያህል ጥቅም ሊያመጡ አይችሉም::

እንግዲህ ብዙዎቻችን ያውርጋ ማህበር አባሎች ከመጀመሪያውም ይህንን የጊዜያዊ መንግስት፣ ወይንም ሞግዚት መንግስት ሃሳብ ያልተቀበሉት ከዚህ በላይ በመጠኑ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች በመገንዘብና የጊዜው ዋና ጥያቄ ሌላ መሆኑን በማስተዋል ነበር:: አሁንም ቢሆን፣ እንዲያውም ከድሮው በበለጠ አኳኋን የጊዜው ዋና ጥያቄ የጊዜያዊ መንግስት ጉዳይ አይደለም:: ይህ የተባለው መንግስት ቢፈጠርም እውነተኛ ገዥ ሠራዊቱ ሆኖ እንደሚቆይ ፈጽሞ ለመጠራጠር አይቻልም:: ደግሞም የኢትዮጵያን ወዝአደርና አርሶአደር ጥቅም ሊያስጠብቅ እንደማይችል ግልጽ ነው:: የጊዜው ዋና ጥያቄ የሰፊው ህዝብ ለመደራጀት መቻል ነው:: ስለዚህም ባሁኑ ጊዜ ልንጠይቃቸውና ልንሰራቸው የሚገቡን ነገሮችአሉ:: እነዚህን መዘርዘር ያስፈልገናል::

15/. ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ መጠየቅ ያለብን፣ ካሁኑ በቅድሚያ መጠየቅ ያለበት፣ ከኃይለ ስላሴ መንግስት ስንጠይቀው የኖርነውን ዲሞክራሲያዊ መብት ነው:: ኢትዮጵያ አሁን "በመሸጋገሪያ ዘመን" ላይ ስለሆነች አሳቦች በነፃና በሰፊው ለመቅረብ መቻል አለባቸው:: የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ ማህበራትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማቋቋም መብቶች፣ ወዘተ. ካሁኑ መከበር አለባቸው:: የመስከረም 2 አዋጅ ቁጥር 8 አሁኑኑ እንዲሰረዝና እነዚህ መብቶች በፍጥነት ከሥራ ላይ እንዲውሉ መጠየቅ አለብን:: የጊዜያዊ መንግስትን ወሬ ትተን በዚህ ትግል ላይ መረባረብ አለብን:: እነዚህን መብቶች ሠራዊቱ ራሱ ከጥቂት ወራት በፊት ካኃይለ ስላሴ መንግስት ሲጠይቅ እንደነበረ ከዚህ በላይ ባንድ ቦታ ላይ ጠቅሰናል:: አሁን ሠራዊቱ ስልጣንን ከያዘ በኋላ ለነዚህ መብቶች መነፈግ የሚሰጠው ምክንያት መጀመሪያ ህዝቡን ማስተማር አለብን፣ ፊደል ማስቆጠር አለብን፣ ያለበለዚያ ጥቂቶች በነሱ ቦታ ይወስናሉ የሚል ስንኩል ሰበብ ነው:: ይህ መቸስ የዲሞክራሲን ትርጉም አለማወቅ ወይንም እያወቁ ለማጭበርበር መሞከር ነው:: ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚያስፈልጉት ለምኑ ሆነና? ሃሳቦችን ለህዝቡ አቅርቦ አብዛኛው ህዝብ እንዲደግፋቸውና በዚህም ድጋፍ ላይ ተመስርቶ ከሥራ ላይ ለማዋል አይደለምን? ሃሳቦችን ለህዝብ ማቅረብና ልዩ ልዩ ሀሳቦች ለህዝቡ ድጋፍ እንዲወዳደሩ ማድረግ ህዝቡ በቀጥታ በተግባር እንዲማር ማድረግ አይደለምን? ፊደልን ማስቆጠር ስለተባለው፣ ከዚያ የሚቀድመው የፖለቲካው ጉዳይ እንደሆነ ለማንም ግልጽ መሆን አለበት:: ትክክለኛ የፖለቲካ ነፃነት ካለ፣ መሃይሙን



የኢትዮጵያ ህዝብ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለማስተማር ይቻላል:: ይህ ከሌለ ግን ሰላሳ አርባ ዓመታትም መሃይምነትን ከአገራችን ሊያጠፉ አይችሉም:: "ከሁሉ አስቀድሞ የፖለቲካ ነፃነትን እሹ፣ የቀረው ሁሉ ይጨመርላችኋል" ነው::

ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መነፈግ ከየካቲት ጀምሮ ሲሰጥ የቆየው በኃይለ ስላሴም ዘመን የነበረው ሌላ ስንኩል ምክንያት፣ ሁሉም "በየጓሮው" ፓርቲዎችን ያቋቁማል፣ ኢትዮጵያ ትገነጣጠላለች፣ ወዘተ. የሚል ነው:: በኢትዮጵያ ብሄረሰብ መካከል ጨቋኝና ተጨቋኞች እንዳሉና ይህም መፍትሄ የሚያገኘው የብሄረሰቦች እኩልነት ታውቆ ሲከበር መሆኑን፣ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው፣ በስብከት ብቻ ይህንን ቅራኔ ሊፈታ እንደማይችል ደጋግመን ገልጸናል:: የዲሞክራሲያዊ መብቶች መከልከልና የኃይለ ስላሴን ጎዳና በመከተል በመሳሪያ ኃይል "አንድነትን" ለመፍጠር መሞከር ውድቀትን ያመጣል እንጂ የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች አንዳቸውም ያህል አያቀራርብም:: በተረፈም፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከታወጁ ሰው "በየጓሮው" ፓርቲ ያቋቁማል የሚለው ስህተተኛ አስተሳሰብ መሆኑን ትግላችን በግንቦት ወር 1966 በዝርዝር አስረድቷል::

የነሀሴ ወር "የሠራተኛ ድምጽ" በርእሰአንቀፁ፣ በተለይም በእንግሊዝኛ በተጻፈው ውስጥ፣ የፓርቲዎች መቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል:: ኢሰአማ በ"ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" በመማረክ ፈንታ መጽሄቱ በጠየቀው በኩል ቢቀጥል ኖሮ፣ ማለት የዲሞክራሲያዊ መብቶችን በፍጥነት ከሥራ ላይ መዋል መጠየቁን ቢቀጥል ኖሮ የሚጠቅሙ ውጤቶችን ባገኝ ነበር::

ባሁኑ ጊዜ ባገራችን ያሉትን የመደብ ኃይሎች ስንመለከት፣ አሁኑኑ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ቢፈቀዱ፣ እመጀመሪያው ላይ ሊቋቋሙ የሚችሉት ሁለት ሶስት የንዑስ ከበርቴው ፓርቲዎችና ምናልባትም አንድ የመሳፍንትን ርዝራዥና የቢሮ ከበርቴውን የሚያጠቃልል ምናልባትም ወደወዝአደሩ የሚጠጋ አንድ ሌላ ፓርቲ፣ በጠቅላላው ከግማሽ ደርዘን በላይ ፓርቲዎች ሊቋቋሙ የሚችሉአይመስለንም:: /ምናልባትም ቢበዛ ቢበዛ አንድ የዘቀተኛ ባላባቶችና የነፍጠኞች ፓርቲ ሊቋቋም ይችል ይሆናል::/ በኋላ ግን ቀስ በቀስ የመደብ አሰላለፉ እየተጣራ ሲሄድ የመደብ አሰላለፉ እየተጣራ ሲሄድ የፓርቲዎች ቁጥር ይቀነሳል:: እውነት ነው፣ ይህ ሁሉ ግምት ብቻ ነው:: በርግጥና በቁርጥ ስንት ፓርቲዎች እንደሚቋቋሙ ለመናገር አይቻልም:: እዚህ ላይ ለማለት የምንፈልገው ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ሁሉ፣ የፓርቲዎች ቁጥር ይበዛል ተብሎ ይህ የህዝቦች መሰረታዊ መብት መከልከል እንደማይገባው ነው:: ደግሞስ ፓርቲዎች ቢበዙ ምን አለበት ዙር ዙር ከላይ እንደተባለው ሁሉ የመደብ ትግሉ እየተጣራ ሲሄድ ዋነኞቹን መደቦች የሚወከ

ሎት ብቻ ይቀራ የለም ወይ?

ወጣም ወረደ፣ የመጀመሪያው ባሁኑ ሰዓት መጠየቅ ያለበት ጉዳይ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ነው፡፡ በነገራችን ላይ፣ በተባለው መሰረት ተማሪው ተገዶ "እድገት በህብረት፣ የዕውቀት ዘመቻ" የተባለውን እቅድ ከስራ ላይ እንዲያውለው ከተደረገ፣ የመጀመሪያው ለህዝቡ ሊያስተምር የሚገባው ህዝቡ ተደራጅቶ ይህንን መሰረታዊ መብት እንዲጠይቅ ነው፡፡ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው የአዲሱ ገዥዎች "ፍልስፍና" ለሰፊው ህዝብ ምንም ጥቅም የማይሰጥ፣ ያለተጧራ ነው፡፡ ለሰፊው ህዝብ የሚጠቅመው ጥሪ "ተደራጅ፣ ለመብትህ ታገል፣ ካልተደራጀህ ምንም አታገኝም" የሚለው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች በተባለው መሰረት ወደየገጠሩ እንዲሄዱ ከተገደዱ፣ ይህንን ጥሪ ከዳር እስከዳር ለማስተጋባት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡

25/. የፖለቲካ እስረኞች ያላንዳች ልዩነት ሁሉም እንዲፈቱ መጠየቅ አለብን፡፡ የጦር ኃይሎች ደርግ የኃይለ ስላሴን ጉዳና በመከተል "ሠራዊቱን ለመከፋፈል ሞከሩ"፣ "አገሪቷን ለመከፋፈል ተነሱ"፣ "የቀድሞውን አገዛዝ ለመመለስ ተነሱ"፣ እያለ ይዞ ያሰራቸው አገር ወዳዶች በቁጥር እየበረከቱ ሄደዋል፡፡ እነዚህን ደርጉ በቶሎ እንዲፈታቸው መጠየቅ አለብን፡፡

ባሁኑ ጊዜ በእስር ላይ የሚገኙት ወታደሮችና ዝቅተኛ መኰንኖች፣ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር ተዋጊዎች፣ ተማሪዎችና አስተማሪዎች፣ ወይ የቡድን ጥቅናን በመቃወም፣ ወይ ሲቪል መንግስት በፍጥነት ይቋቋም በማለታቸው፣ ወይንም በደርጉ ላይ ተገቢ ሂስ በማቅረባቸው ተይዘው ወደእስር ቤት የተወረወሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀቀኛ ግለሰቦችና የነፃነት ተዋጊዎች በፍጥነት መፈታት አለባቸው፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ፣ የወታደር አስተዳደሩ የመስከረም 2 አዋጅ ቁጥር ዘጠኝ እንዲሰረዝ መጠየቅ አለብን፡፡ የኢትዮጵያን ህዝቦች በመበዝበዛቸውና በመጨቆናቸው፣ አገሪቷን ለኢምፔሪያሊዝም አሳልፈው በመሸጣቸው የታወቁት፣ በወሎ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን እንዲያልቁ ያደረጉት የቀድሞ ባለሥልጣኖችና የተራማጅ ኢትዮጵያውያን እኩል መታየትና እንደነሱ "ለፍርድ መቅረብ" አጥብቀን መቃወም አለብን፡፡ የፖለቲካ እስረኞች ስንል እነዚህን ተራማጆች ማለታችን እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል፣ የኤርትራ ግንባር መሪዎች በውጭ አገር ጋዜጦች አማካይነት ለሰላም ውይይት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህ አቋማቸው ትክክለኛና ተቀባይነት ማግኘት የሚገባው ነው፡፡ የጦር ኃይሎች ደርግ ይህንን አሳብ እንዲቀበለውና በኤርትራ ላይ የሚፈጸመውን እልቂት እንዲያቆም መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡



ኃይለስላሴ የሄደበትን ጉዳና መከተል ፈጽሞ አያዋጣም፡፡ በተጨማሪም፣ ጊዜያዊው የኢትዮጵያ መንግስት በኤርትራ ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ፋሺስታዊ ወንጀል በጥብቅ ማውገዝ አለብን፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦችም እንዲያወግዙት ለማድረግ መጣር አለብን፡፡

35/. የዘውዱ አገዛዝ ከኢትዮጵያ እንዲጠፋና 'ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ' እንዲታወጅ መጠየቅ አለብን፡፡ በዚህ በኩል፣ ባለፈው ሰኔ ወር ወጥቶ የነበረው ህገመንግስት እንደገና መቀየር አለበት ማለት ነው፡፡ መጀመሪያ ነገር በምዕራፍ 1 ውስጥ ዘውዱን የሚመለከተው ሁሉ መሰረዝና ኢትዮጵያ ሪፖብሊክ መሆንዋን የሚያስታውቅ አንቀጽ በዚያ ሁሉ ፍሬከርስኪ ቦታ መተካት አለበት፡፡ ሁለተኛ በየአንቀጹ ውስጥ ለህዝቡ መብቶች ገደብ የሚያበጁት ፀረ ዲሞክራቲክ ህጎች መወገድ አለባቸው፡፡ ህገመንግስቱ የብሄረሰቦችን፣ የሃይማኖቶችን፣ የጾታዎችን እኩልነት በማያሻማ ሁኔታ ማጽደቅ አለበት፡፡

ከዚህ በላይ በቁጥር 1 ላይ የተጠየቀው የዲሞክራቲክ መብቶች ጉዳይ አስቀድሞ መፍትሄ ካላገኘ፣ "ምርጫ ይደረጋል፣ በህገመንግስቱ ላይ ውይይት ይደረጋል" ቢባል ምንም ትርጉም አይኖረውም፡፡ ስለዚህ የዲሞክራቲክ መብቶች መከበርና የዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ መታወጅ የማይነጣጠሉ ጥያቄዎቻችን መሆን አለባቸው፡፡

45/. ኢምፔሪያሊዝም ከኢትዮጵያ እንዲወገድ መጠየቅ አለብን፡፡ በተለይም፣ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በወታደር አማካሪዎቹ፣ በአስተማሪዎቹ፣ በኤክስፐርቶቹ፣ ወዘተ. እያመካኘ ያስገባቸው የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎቻችን እሁኑኑ ከአገራችን እንዲወጡ መጠየቅ አለብን፡፡ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሆነ ሌሎች በአገራችን ላይ ያሰፈራቸው የጦር ሰፈሮች እንዲነሱ መጠየቅ አለብን፡፡ የኃይለስላሴ መንግስት ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር የተፈራረማቸው የወታደር ሆነ የአገሪቷን ነፃነት የሚፃረሩ ውሎች በቶሎ እንዲሰረዙ መጠየቅ አለብን፡፡ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የየካቲት እንቅስቃሴ ወደፊት ገስግሶ ፀረ ኢምፔሪያሊስት እንዳይሆን ያልገለበጠውና የማይገለብጠው ድንጋይ የለም፡፡ ኢምፔሪያሊዝም የራሱን ኢኮኖሚያዊና የስትራተጂ ጥቅሞች ለመጠበቅ ሲል ወይ አገር ወዳዶችን በመከፋፈል፣ ወይንም በገንዘብ እየገዛ ፋሺስታዊ አስተዳደርን ከማቋቋም ፈጽሞ አይመለስም፡፡ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ካገራችን መባረር ባሁኑ ጊዜ አጣዳፊ ጥያቄ ነው፡፡

እንግዲህ ባሁኑ ሁኔታ በጥድፊያ መጠየቅ አለባቸው፣ ሁሉም ተራማጅ ግለሰብና ድርጅት ይዞአቸው መነሳት አለበት ብለን የምንገምታቸው ጥያቄዎች እነዚህ አራቱ ናቸው፦ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ፣ የፖለቲካ እስረኞች መፈታትና የኤርትራ የሰላም ውይይት መጀመር፣ የዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ መታወጅና የኢምፔሪያሊዝም ካገራችን መውጣት

ለንጠይቃቸው የሚገቡን እነዚህ አራት ነጥቦች ሲሆኑ/ ዋና ዋናዎቹ ማለታችን ነው እንጂ ሌላ የሚጠየቁ የለም ለማለት አይደለም/ ልንሠራው የሚገባን ዋናው ነገር መደራጀትና ማደራጀት ነው::

ይህ ጥያቄ ከሁሉም በላይ የሚመለከተው በትግሉ ሜዳ ላይ ያሉትን ተራማጆች ነው::ዛሬ በኢትዮጵያ ተራማጆች መካከል ከተማሪው ማህበራት በተለይ ከውጭ አገሩ እንቅስቃሴ የመነጨ ያስተሳሰብ ልዩነቶች እንዳሉ ያደባባይ ምስጢር ነው::እነዚህ ሁለት ያስተሳሰብ አቅጣጫዎች ባገር ቤትም እንዳሉና ዘር ዘር ደግሞ የልዩነቶችም መሰረት የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ራሱ እንደሆነ የታወቀ ነገር ነው::ይሁንናም በኛ አስተያየት ለነዚህ ከላይ ለደረደርናቸው ጥያቄዎች በሚደረገው ትግል ሁለቱም ወገኖች አብረው የማይሰለፉበት ምክንያት የለም::ለዚህም መሰረታዊ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ የአሰራር ዘዴ በተግባር ላይ ማዋል ብቻ ነው::አነስተኛው ለብዙሃኑ መታዘዝ አለበት፤ልዩነት ባለባቸው ነጥቦች ላይ ከስምምነት መድረስን እንደዓላማ ወስደ በጥሞና መከራከር ይገባል፤እነዚህንና የመሳሰሉትን መመሪያዎች ከሥራ ላይ በማዋል ለትግል አንድነት መጣር ጊዜያዊው የተራማጆች ግዴታ ነው::

በዚህ በኩል የማህበራችን ታሪክ ይህን ያህል የሚያበረታታ ባይሆንም አንድ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ብለን እንገምታለን::እንደሚታወቀው ባውሮፓ ሁለት የፖለቲካ መስመሮች አሉ::ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ባለፉት ሶስት አራት አመታት ያነስተኛው/የማይናገሪቱው/መስመር ሆኖ ቆይቷል::ይሁንናም ይህኛው ወገን ብዙውን ጊዜ ያብዛኛዉን ውሳኔ አክብሮ ከስራ ላይ አላዋለም::እንዲያውም ባንዳንድ ድርጊቶቹ ፀረዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ የብዙሃኑን ውሳኔ በተጨበጠ አኳኋን ሲያፋልሳቸው ተገኝቷል::ለዚህም አድራጎቱ ቢያንስ በሁለት ዓመታዊ ጉባዔዎች ላይ ተወግዟል::የሆነ ሆኖ የማህበራችን ድርጅታዊ አንድነት እስካሁን አልፈረሰም::ዲሞክራሲ ከስራ ላይ እንዲውል ከተፈለገ አነስተኛው የብዙሃኑን ውሳኔ ተቀብሎ ከሥራ ላይ ማዋል አለበት::ያገራችን ተራማጆች ይህንን መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊ ሥነስርዓት እስካልተቀበሉና በግለሰብነት እስከተዋጡ ድረስ የኢትዮጵያን ረቮሉሽን ወደኋላ ይጎትታሉ እንጂ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማቅረብ አይችሉም::

ለማንኛውም፤ተራማጁ ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ያለበት ግዴታ መደራጀትና ማደራጀት ነው::የድርጅቱን ዓይነትና ያሉበትን ኃላፊነቶች እንዴት አድርጎ ከስራ ላይ ለማዋል እንደሚቻል ዘርዝር በተጣራ አኳኋን ማቅረብ የተደራጆቹ ፈንታ ነው:: ከዚያ በኋላ ግን ሰፊውን ህዝብ ለማደራጀት ሰፊ ጥረት መደረግ ይኖርበታል::



የመደራጀት ጥያቄ ባሁኑ ጊዜ አጣዳፊ የሚሆንበት ዋናዎቹ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል አሁን ከደረሰበት ደረጃ ወደፊት ሊራመድ ከንግዲህ የሚችለው ህዝቡ ከተደራጀ ብቻ በመሆኑና በተለይም፤ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ አጼ ገዢያቸ ፍጹም ፋሺስታዊ ጉዳና ሊወስዱ ስለሚችሉ ነው::ይህንን ጉዳና እንዳይወስዱ ለማድረግ የሚቻለው ሻንዳች አይነት ጊዜያዊ መንግስት፤ቀግዚት፤ ሳይሆን፤የሰፊው ህዝብ የተደራጀ ኃይልና ትግል ብቻ ነው::ኢምፔሪያሊዝም በአጼው ገዥያቻችን አማካይነት ሊፈጽም የሚችለው ፀረህዝብ ወንጀል ለማክሸፍ የሚችለው የሰፊው ህዝብ የተደራጀ ኃይል ብቻ ነው::ኢትዮጵያ ሌላ ግሪክ፤ሌላ ቺሊ እንዳትሆን በፍጥነት መደራጀትና ህዝቡን ማደራጀት ያስፈልጋል::

__________xxxxx__________

እንግዲህ ከዚህ በላይ ያቀረብናቸውን አሳቦች በማጠቃለያ መልክ ከዚህ በታች ከማቅረባችን በፊት፤የዛሬውን የዓለም ሁኔታ ዓይነተኛ የሚያደርጉትን አንዳንድ ነጥቦች እዚህ ላይ ማስታወስ ተገቢ ይመስለናል::የኢትዮጵያ ህዝቦች ረቮሉሽናዊ ትግል በሚካሄድበት ባሁኑ ወቅት፤የዓለም ሁኔታ በጣም እየተለወጠ በመሄድ ላይ ነው::አንዳንድ ምሳሌያችን ለመጥቀስ ያህል ቀድሞ በፋሺስታዊ አገዛዝ ሥር የነበረት ፖርቱጋልና ግሪክ አሁን ወደከበርቴ ዲሞክራሲ እንዲመለሱ የህዝቡ ትግል አስገድዷቸዋል::የመጀመሪያውን አገር በሚመለከተው በኩል፤ይህንን ለውጥ ያስገኘው የጊኒ ቢሳዎ፤የአንጎላና የሞዛምቢክና የፖርቱጋልም የራሷ ህዝቦች ፀረቅኝ አገዛዝና ፀረፋሺስት ትግል ነው::የኢንዶቻይና ህዝቦች በየእለቱ አዳዲስ ድሎችን እንዳገኙ ነው::የቅርብ ምስራቅ ህዝቦች ኢምፔሪያሊዝምን እንዳሸበረት ናቸው::በበኩሉ የኢምፔሪያሊስት ዓለም ታይቶ በማይታወቅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ውስጥ እየወደቀ ሄዷል::በጠቅላላው በዛሬው ዓለም ላይ የምናየው ለውጥ ለህዝቦች ነፃነት፤ለህዝቦች ረቮሉሽን እያመቸ የሚሄድ ነው::ለኢትዮጵያም ህዝቦች ሁኔታው እያመቸ ይሄዳል::ህዝባችን ከተደራጀና ካሁን በበለጠ ነቅቶ ከታገለ ከየካቲት እንቅስቃሴ አስር እጅ የሚያሸበርቁ ተአምሮችን ሊሰራ ይችላል::የዚህም ተአምር ጊዜ ተቃርቧል::

ይህንኑ በማመን፤ከዚህ በላይ ያሰፈርነው ጽሁፍ የያዛቸውን ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው እናጠቃል:—

1, የየካቲት የኢትዮጵያ ህዝቦች ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ አሁን ወደኋላ ላይ ወደ "ተጉታች ኩዔታ" የተለወጠ ቢመስልም፤እንቅስቃሴው ገና አላከተመም::ህዝቡ በየካቲት ያነሳቸው ጥያቄዎች ስላልተፈጸሙ አሁንም የነሱን መፈጸም ይጠብቃል::እንቅስቃሴው የተጉታች

ኩዴታ'መለክ የያዘበት ዋናው ምክንያት ገዥ መደቦች ፀረረቮሉሺንን ለማዘጋጀት ባለመ ቻላቸውና እንቅስቃሴውን ያነሳሱት ሆነ በእንቅስቃሴው የተካፈሉት መደቦች የመንግስት ሥልጣንን ለመያዝ የተዘጋጁ ስላልነበሩ ነው።

2. የኃይለ ስላሴ መገለበጥ በኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታን ይይዛል። ይሁን እንጂ የንጉሡ መገለበጥ የባላባታዊ ስርዐቱን ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰባዊ መሰረት አልነካም። የጦር ኃይሉም የተነሳሳው በስርዐቱ ላይ ሳይሆን በስርዐቱ ወሪያች ላይ ነበር።

3. ሠራዊቱ በሰኔ 26 ስልጣኑን ሲይዝ ሆነ አሁን የተጣራ ፕሮግራም አልነበረውም፣ የለውም የወሰዳቸው እርምጃዎች የመጡት የ"ህዝብ ድምጽ"በመከተል ነው። "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን መመሪያውን አጥርቶ ባያቀርብም፣ ደርጉ የወሰዳቸው ተራማጅ እርምጃዎች አገር ወዳድ ያስመስሉታል። ነገር ግን ያለተራማጅ ፖለቲካ አገር ወዳድነት ፋሺዝምን ሊወልድ ይችላል፣ ይህ አደጋ ዛሬ በኢትዮጵያ አለ።

4. በኢትዮጵያ የሚደረገው ረቮሉሽን ባሁኑ ወቅት አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ረቮሉሽን ብቻ ነው። ይህንን ረቮሉሽን ለመራና ከፍጻሜ ሊያደርሰው የሚችለው የወዝአደሩ መደብ ነው። ይህ መደብ የራሱን ፓርቲ ካቋቋመ በኋላ ሌሎችን አጋዥ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ባንድነት ግንባር በማሰለፍ ባላባታዊ ስርዐትንና ኢምፔሪያሊዝምን በመገልበጥ ይደመስሳል። ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን አቋቁሞ የሶሺያሊዝምን መሰረት ይጥላል።

5. የወታደሩ "ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርን"ማወጁና በተለይም የመስከረም ሁለት አዋጅ አንቀጽ 8ና9 ፍጹም ፀረዴሞክራቲክና ፈላጭ ቆራጭ ናቸው። ስልጣኑን ከነሰሙ ከወሰደ ወዲህ ደርጉ በሚወስዳቸው እርምጃዎች በያንኪዎች የሰለላ ድርጅት፣ በሲአይኤ፣ ሥር የወደቀ ይመስላል። ያንኪዎች ከአገራችን እንዲወጡ መጠየቅ አለብን።

6. ከንገዲህ ወዲት እንራመድ ለሚለው ጥያቄ ካዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች፣ በኋላም ከኢሠአማ የቀረበው የጊዜያዊ መንግስት ጥያቄ ለሰፊው ህዝብ— ማለትም ለገበሬውና ለወዝአደሩ በተለይ — ምንም ጥቅም የማያመጣ፣ ትግላቸውን ወደፊት የማያራምድ ከመሆኑ በላይ ይሁን እንኳ ቢባል በተጣራ አኳኋን አልቀረበም።

7. በአሁኑ ሰዓት ሆነ ወደፊት ለህዝቡ ጥቅም የሚያመጣው፣ ትግላቸውን ወደፊት የሚያራምደው የህዝቡ የራሱ መደራጀትና ለዴሞክራቲክ መብቶች መታገል ነው። ስለዚህም፣ ከሁሉ አስቀድሞ የዴሞክራቲክ መብቶችን መታወቅና ከሥራ ላይ መዋል መጠየቅ አለብን። ከዚህ ጋር አያይዘን የታሰሩትን ተራማጆችና የመብት ተሟጋቾች ቢቶሉ መፈታትና ከኤርትራ ግንባር የሰላም ውይይት እንዲጀምር መጠየቅ አለብን። የዘውዱ አገዛዝ ከአገራችን እንዲጠፋና



ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እንዲቋቋም፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከአገራችን እንዲወጣ መጠየቅ አለብን።

8. በዛሬው እለት የተራማጆች ዋና ተግባር መደራጀትና ማደራጀት ነው። ይህም ጥያቄ አጣዳፊ ነው። በተራማጆች መካከል ያለው ልዩነት በዴሞክራሲያዊ ሥነስርዐት ለነዚህ ጥያቄዎች አብሮ መታገልን ሊያግድ አይገባውም።

_______________xxxxxxx_______________

## ቀኖችና ድርጊቶች

ሰኔ18: የመንግስት ባለስልጣኖች ያለመርማሪው ኮሚሽን ፈቃድ ወደውጭ አገር እንዳይጓዙ የሚከለልከል አዋጅ ወጣ፡፡ከሁለት ቀናት በኋላ፣ባለሥልጣኖች መጓዛቸው አስፈላጊ መሆኑን ካረጋገጡ ለመሄድ ይችላሉ የሚል ትዕዛዝ የሚኒስትሮች ምክርቤት አወጣ፡፡ጉዳዩ በአንዳልካቸውና በመርማሪው ኮሚሽን መሃል የነበረውን ትግል ያሳያል፡፡

ሰኔ 19: "በጃንሆይ ሊቀመንበርነት በአገሪቱ ከፍተኛ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ንግግር ተደረገ" በሚል አርእስት ስር፣የሰኔ 20ው አዲስ ዘመን እንዲህ ይጽፋል፡- "በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀ.ኃ.ሥ. ሊቀመንበርነት፣የዘውድ ምክርቤትና የሚኒስቴሮች ምክር ቤት አባሎች በትናንቱ እለት ሁለት ሰዓት የፈጀ ስብሰባ አድርገዋል፡፡በአንዳንድ አገሪቱን በሚመለከቱ ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ሚኒስትሮች ባቀረቧቸው ሪፖርት ሰፊ ንግግር ተደርጓል፡፡" /የተባሉት "ከፍተኛ ያገር ጉዳዮች" የትኞቹ እንደሆኑና ምን እንደተወሰነ ጋዜጣው አይናገርም፡፡

ሰኔ20: በሻለቃ አድማሴ መሪነት ስምንት መማክርት ወደ4ኛ ክፍለጦር ሄደው የታሰሩት ሚኒስትሮች እንዲፈቱ ይጠይቃሉ፡፡

ሰኔ 21: ያዲስ አበባ ከተማ፣ያውሮፕላን ማረፊያውና ራዲዮ ጣቢያዎቹ በጦር ኃይሎች ተያዙ፡፡ይህም ከየካቲት ጀምሮ አራተኛ ጊዜ መሆኑ ነው፡፡

ሰኔ 22: ጧት የአንዳልካቸው መንግስት ከወታደሮቹ ጋር የሚነጋገር ኮሚሲዮን ፈጠረ፡፡ የኮሚሲዮኑ አባሎች ዘውዴ ገ/ሥላሴ፣ ተካልኝ ገዳሙ፣አብዱርህማን መሀመድና ደምሴ ተፈራ ናቸው፡፡

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ጀምሮ መዘዋወር ተከተለ፡፡ማታ አነአሥራተ ካሳ፣ዘውዴ ገ/ህይወትና ይልማ ዴሬሳ መያዛቸው በራዲዮ ተነገረ፡፡

ሰኔ 23: ሠራዊቱ ለንጉሠ ነገሥቱና ላገሪቱ ታማኝነቱን ከገለጠ በኋላ የሚፈልጋቸው ሰዎች "ለአዲሱ ካቢኔ ሥራ መሰናከል የሆኑትን ነው" የሚል መግለጫ ሰጠ፡፡ማታ እንደገና የተያዙት ሰዎች ዝርዝር ተነገረ፡፡በዚያውም፣በመንግስቱ የአራት ሰዎች ኮሚቴና በጦር ኃይሎች ወኪሎች መካከል "ሙሉ ስምምነት" እንዳለ ተነገረ፡፡

ሰኔ 25: <u>አዲስ ዘመን</u>፡፡ "የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ጠቃሚ ውሳኔዎችን አሳለፈ፡፡ለግርማዊ ጃንሆይና ለአዲሱ ካቢኔ ታማኝነቱን ገለጠ፡፡" በሚል አርእስት ስር፡- "የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ሰሞኑን ለተደረገው ንቅናቄ ህገንና ስርዐትን በመከተል ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ለአዲሱ ካቢኔ ታማኝነቱን በመግለጥ፣አቅዱ ፕላኑን በማ



ዘጋጀት፣ለሚኒስቶሮች ምክር ቤት እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱትን ነገሮች /ይለዋል/ ለማስወገድ ኮሚቴው... "ይላል፡፡

በዚሁ እለት ኮሚቴው በሰጠው መግለጫ መሠረት የወህኒ ቤት የፖሊስ ሠራዊት ካዲሱ ኮሚቴ ጋር የሚተባበር መሆኑን ማስታወቁን ይገልጻል፡፡ለዚህም የመቶ አለቃ ካሳዬ አራጋውና ወታደር አምባቸው አለሙ ከኮሚቴው ጋር ተባብረው እንዲሰሩ የተወከሉ መሆናቸው ተገለጠ፡፡

ሰኔ 26: የደርጉ አባሎች ከንጉሡ ፊት ቀርበው እንዲህ ይላሉ፡-

"የኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ጃንሆይ፣ግርማዊነትዎ እድሜ ዘመንዎን ሙሉ መስዋእት ያደረጉበት የኢትዮጵያ ፀጥታና አንድነት እንዲጠበቅ አሳፊነቱ በይበልጥ የጦር ኃይሎችዎ በመሆኑና የጊዜው ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ ልዩ ልዩ ችግሮችን ስለፈጠረ፣ የግርማዊነትዎ ዙፋንና የኢትዮጵያም ፀጥታ የፀና እንዲሆን ከዚህ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች የጦር ኃይሉ ስለጠየቀን፣ግርማዊነትዎ እንዲፈቅዱልን የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች፣የክብር ዘበኛ፣የፖሊስ ሠራዊትና የወህኒ ፖሊስ፣እንዲሁም የበሄራዊ ጦር ሠራዊት ወኪሎች ከግርማዊነትዎ ዙፋን ፊት ቀርበናል፡፡"ካሉ በኋላ የሚከተሉትን ይጠይቃሉ፡፡

1ኛ. የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ

2ኛ. ስደተኞች ምህረት ተደርጎላቸው እንዲመለሱ

3ኛ. ህገመንግስት በቶሎ ተጠናቆ" ለህዝቡ እንዲገለጥና በሥራ ላይ እንዲውል"

4ኛ. ለዚህም ፓርላማው መዘጋቱ ቀርቶ ሥራውን እንዲቀጥል

5ኛ. "ይህ የተቋቋመው ደርጋችን ለአገሪቱ አንድነትና እድገት፣ሰላምና ፀጥታ፣ እንዲሁም ለአገሪቱ የመከላከያና የፖሊስ ኃይሎች መደርጀትና መሻሻል ከመንግስቱ ባለሥልጣኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲያደርግ እንዲፈቀድልን ከዙፋንዎ ፊት ዝቅ ብለን በትህትና እንለምናለን፡፡ለግርማዊነትዎ ረዥም እድሜ እየለመንን፣ኢትዮጵያ ትቅደም ብለን ለተነሳሳንበት ዓላማችን የኃያሉ እግዚአብሄር ድጋፍ እንዳይለየን እንጸልያለን፡፡"/እነዚህ ጥያቄዎች የመነጩት በሰኔ 25 ሙሉ ሠራዊቱ ተሰብስቦ ሲመካከር ከዋለ በኋላ ሲሆን፣ አሁን የገነነው "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሠራዊቱ በኩል ሰረወር የመጀመሪያው ጊዜ ይመስላል፡፡/

በዚሁ ዕለት አማን አንዶም ሌተና ጄኔራል ተብሉ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹምነት ተሾመ፡፡

ሰኔ 27፡አዲስ ዘመን፡፡"ከጦር ኃይሎች የተሰጠ መግለጫ በሚል አርእስት ስር፡—"የጦር
ኃይሎች፣ይኸውም የምድር ጦር፣የአየር ኃይል፣የባህር ኃይል፣የክብር ዘበኛ፣የወ
ፀኒ ቤት ፖሊስ ሠራዊትና የብሄራዊ ጦር አባሎች፣በጠቅላላው የአሁኑን ወታደራዊ
እንቅስቃሴ የፈጠረት ሁሉ፣ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጡ እንደመሆናቸው መጠን
በኢትዮጵያዊነት ስሜት የተቃጠሉ፣ለኢትዮጵያ ህዝብና ለንጉሠ ነገሥታቸው ደህን
ነት እጅግ በጣም የሚያስቡና የሚጨነቁ፣የሚሰሩትም ሥራ ሁሉ በእውነተኛ ኢትዮ
ጵያዊነት መንፈስ ላይ የተመሰረተ፣መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲረዳልንና
የእለት ሥራውን በረጋ መንፈስ እንዲያከናውን አጥብቀን አደራ እንላለን፡፡...

ኰሚቴው ሥራውን የሚያከናውነው በጣም አርቆ በማሰብና በመጠንቀቅ ነው፡፡
...ማንኛውም ሰው የተያዘውና የሚያዘውም ህገወጥ እርምጃ ይወሰድብናል ብሎ
እንዳይሰጋ፡፡፡..."

—በዚሁ እለት፣"የጦር ኃይሎች ኰሚቴ ለአዛዦች ገለጣ አደረገ፡" አዛዦቹም፣
አማን አንዶም፣ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም፣ጃገማ ኬሎ ብሄራዊ ጦር፣ገዛው በላይ ነህ
የምድር ጦር ዋና አዛዥ፣ታደሰ ገብሬ፣የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ፣ታደሰ መለኬ፣የ4ኛ
ክፍለጦር ዋና አዛዥ፣ታፈሰ ለማ የአንደኛ ክፍለጦር የክብር ዘበኛ አዛዥ ነበሩ
"የጦር ኃይሎች ኰሚቴ ያደረገው ገለጣ እንደተፈጸመም፣የአያንዳንዱ ~~ሠራዊት~~ አዛዦችበሰጡት
አስተያየት የአገሪቱን ሙሉ ደህንነት ለማመለከተው ኰሚቴ፣ይኸውም የግርማዊ ንጉ
ሠነገስት ዘውድ እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ ትቅደም ለሚለው አላማ ሙሉ በሙሉ ደጋፊ
ያች መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ ኰሚቴው ለሚያደርገው ጥረት በሚቻላቸው ሁሉ ድጋ
ፋቸው ለማይለየው መሆኑን አረጋገጠዋል፡፡"

—"...በሁለተኛው የጦር ኃይሎች ጊዜ በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተቋቁሞ የነበ
ረው ብሄራዊ ፀጥታ ኰሚሽን"ፈረሰ፡፡

—"ከፖሊስ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተውጣጥተው የሚሰሩት የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ መስሪያ
ቤት አባሎች፣እንዲሁም የጦር ኃይሎች፣የክብር ዘበኛ፣የፖሊስ ሠራዊትና የልዩ
ልዩ ወታደራዊ ክፍሎች አባሪ የነበሩና አሁንም በጡረታ ላይ የሚገኙ...ኰሚቴው
የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በመደገፍ ተባባሪነታቸውን.፡."ገለጡ፡፡

ሀምሌ 2፡"ሥራ ለማቆም ስላሰቡት መስሪያ ቤቶች የጦር ኃይሎች ደርግ ማስጠንቀቂያ ሰጠ"
ይህ "ማስጠንቀቂያ"ስር ቶአደረገን ህዝብ በኃይል ያስፈራራል፡፡"አለቆቻቸውን የሚ
ገላምጡትን"ይወቅሳል፡፡"በተጨማሪም ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ህገወጥ ድርጊትና አንዳ
ንድ የዘረፋ ሙከራዎች እንዳሉ ሰምተናል"ካለ በኋላ፣"...ከዛሬ ጀምሮ ለሚደረ



ገው አሳፋሪ ተግባር የጠነከረ እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን እየገለጥን..."
ይላል፡፡ከሰኔ 22 ጀምር ያዲስ አበባ ህዝብ በልዩ ልዩ መንገዶች ወታደሩ ፕሮ
ግራሙን እንዲያሲያውቅ ጠይቆ ስለስቸገረው በዚህ ቀን ደርጉ የታወቀትን የ13
ነጥቦች"ፕሮግራሙን"ገለጠ፡—

1ኛ.ኰሚቴው ለግርማዊ ጃንሆይ፣የኢት.ጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ ያለውን ታማኝነት
  ደግሞ ይገልጻል"

2ኛ. የደርጉ ዓላማ "አንቀፋቶችን"በማስወገድ ካቢኔው በተሻለ መንገድ እንዲሰራ
  ማድረግ ነው፡፡

3ኛ.ደርጉ የሚፈልጋቸው በደል የሰሩትን ባለሥልጣኖች መሆኑን፣የሚይዛቸውም በህግ
  መሰረት መሆኑን አስታውቆ ሁሉም ሰው በሥራው እንዲረጋ ይጠይቃል፡፡

4ኛ."ደርጉ በመዘጋጀት ላይ ያለው ህገመንግስት በአስቸኳይ ሥራ ላይ እንዲውል
  ያደርጋል፡፡"

5ኛ. የኢትዮጵያውያን እኩልነት እንዲጠበቅና የሠራተኛ ህግ እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

6ኛ."ስሉጉሳና" ሃይማኖት ልዩነትና "ስለብሄራዊ ስሜት"አንስቶ "ህዝቡ ለሥራ
  ታጥቆ እንዲነሣ"እንደሚያደርግ ይገልጻል፡፡/ቁጥር5ና ይህኛውም ግልጽ አይደሉም/

7ኛ.ደርጉ ከካቢኔው ጋር "ጥብቅ ግንኙነት"በማድረግ ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚሰራ
  ይናገራል፡፡

8ኛ."ደርጉ የኢትዮጵያን እድገትና አንድነት የሚያደናቅፉተን አንዳንድ ባህላዊ
  እምነቶቸና የገዛት አስተዳደር ዘይቤያችን ዘመናዊ መልክ እንዲይዙ ያደርጋል"

9ኛ.ለረሃብ የውጭ እርዳታ እንዳይቋረጥ ይጠይቃል፡፡

10ኛ. ቱሪስቶች ወደአገር መምጣታቸውን እንዳያቋርጡ ይጠይቃል፡፡

11ኛ.እርዳታ እናደርጋለን ያሉት የወዳጅ አገሮች እንዲቀጥሉ ይጠይቃል፡፡

12ኛ. የተጀመረው እንቅስቃሴ ያለደም መፋሰስ ለውጥ የሚያስገኝ መሆኑን ይገልጣል፡፡

13ኛ.ደርጉ ወደፊት "ዓላማዎችን"ያስታውቃል፡፡

እነዚህን ነጥቦች ይዞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ "ኢትዮጵያውያን
የፖለቲካ ስደተኞች ወደአገራቸው እንዲመለሱ ተጠየቀ"በሚል አርእስት ስር በዋናው
ጽሁፋችን በገጽ 20 በሰፊው የጠቀስነው ጽሁፍ ይወጣል፡፡

ሀምሌ3፡"ለሁከት ፈጣሪዎች"ሥራ ማቆምና ሰላማዊ ሰልፍን ለሚያዘጋጁ ሲያቸ ሁለተኛ ማስጠን
ቀቂያ ተሰጠ፡፡ኰሚቴው ከግለሰቦች ሁሉ መሳሪያ ሊሰበሰብ ነው ተብሎ የሚወራውን
አስተባበለ፡፡በማስተባበልና በማስጠንቀቅ፣ኰሚቴው ከዚያን ቀን ወዲያ"ለወራ ሙሰኞች

መግለጫ ያወጣል::በፖ.ሣ. ቁጥር 5707 ህዝቡ ሃሳብ ለመስጠት እንደሚችል ተገለጠ::

ሀምሌ4:በጄኔራል ደናልድ ደውፔ የአሜሪካኖች የጦር አማካሪና በጄኔራል አማን አንዶም መካከል በተደረገው ውይይት መሰረት አሜሪካ ለኢትዮጵያ የመሳሪያ እርዳታዋን እንደምትቀጥልና የነበረው የጦር ትብብርም እንደሚቀጥል ተነገረ::በተረፈ፣ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተነገረው ሁሉ፣አሜሪካ የመቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ብር መሳሪያ ለኢትዮጵያእንደምትሰጥ ተነግሯል::

ሀምሌ5: የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር ለደርጉ ሙሉ ድጋፍ በመስጠት መግለጫ አወጣ::ኢሰአማ ደርጉን የደገፈው በተለይ በደርጉ ፕሮግራም ቁጥር 5ና6 ላይ በመመስረትና በመከላከያ ሚኒስቴር ተቋቁሞ የነበረውን "ከፍተኛ የፀጥታ ኰሚሽን" እንዲፈርስ በማድረጉ መሆኑን ገለጠ::

—ደርጉ አስተያየት ሊሰጡባቸው የሚችሉበትን ቦታዎች ለህዝብ አስታወቀ::"ህዝቡ እራሱ የዚህ ንቅናቄ ተካፋይ መሆኑን እንዳለበት"በማስገንዘብ::/የህዝቡ ተካፋይነት ሃሳብ በመስጠት ይወሰን ይመስል /

ሀምሌ9:አዲስ ዘመን::"የጦር ኃይሎች ኰሚቴና የምርመራ ኰሚሽን አባሎች ውይይት አደረጉ" በሚል አርእስት ስር "...ለአገሩና ለህዝቡ የገባውን ቃል ከማስፈጸም የሚገታው ነገር እንደሌለና በአሁኑም ጊዜ በአለኝታ የሚጠብቀውን ህዝብ ተቶ ወደሰፈሩ እንደማይመለስ ደርጉ አረጋግጧል::"

ሀምሌ11:አዲስ ዘመን::"የጦርከኃይሎች ኰሚቴና የምርመራ ኰሚሽን አባሎች ውይይት አደረጉ" በሚል አርእስት ስር፣ወታደሩ ለኰሚሽኑ አባሎች ባነበበው ወረቀት ውስጥ እንዲህ ይላል::—

"ይህ ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ የተነሳሳው የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሄራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ አጠገባቸሁ ተገኝቶ ማናቸውንም ድጋፍና እርዳታ የሚያደርግላቸሁ መሆኑንእያረጋገጠላቸሁ፣ደርጉ በወከላቸው ሠራዊትና በኢትዮጵያ ህዝብ ስም የሚጥልባቸሁ ታላቅ አደራ፣እነዚህ ኢትዮጵያን ዛሬ ባለቸበት አሳፋሪ ሁኔታ ላይ የጣሉ፣እነዚህ ከመቶ ሺህ ለሆኑት ኢትዮጵያውያን እልቂት ምክንያት የሆኑባለሥልጣኖች በነፃ ተለቀው እስከዛሬ የነበረውን ባላባታዊ አገዛዝ በሃሰት እንደገና መስርተው ኢትዮጵያን ወደታላቅ አዘቅት ውጥ መልሰው እንዳይጨምሯት ታላቅ ጥንቃቄ እንድታደርጉ ነው::"



ሀምሌ 14 :አዲስ ዘመን::"የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርወታደራዊውን እንቅስቃሴ ይደግፋል"በሚል አርእስት ስር፣"ደርጉ የሚወስደው እርምጃ የህዝቡን አስተሳሰብ በመከተል መሆኑ ተገልጧል::"

—ሃሰት ለሚያወሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጠ"በሚል አርእስት ስር፣"ማናቸውም ሰው ያልተጨበጡና ከእውነት የራቀ የሀሰት ወሬ ሲያወራ ቢገኝ ጥብቅ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን በቅድሚያ እናስታውቃለን::"

ሀምሌ 15:እንዳልካቸው ተገልብጦ በርሱ ቦታ ሚካኤል ተሾመ::በዚህ ቀን ከንጉሡ ፊት የቀረቡት "የደርግ አባሎች" ያደረጉት ንግግር በሚቀጥለው ቀን በአዲስ ዘመን ወጣ:: የሚከተሉት ነጥቦች ነበሩበት::

"የአገራችንንና የህዝቡን ችግር ለመካፈልና መፍትሄዎችንም ተባብሮ ለመፈለግ "ኢትዮጵያ ትቅደም"በሚል በአገርና በወገን ፍቅር መሰረታዊ ዓላማ በተነሣሣንበት ጊዜ፣የጦር ኃይሎች ደርግ ለአገርና ለወገን የሚጠቅመውን እንዲሰራ ግርማዊነትዎ በመፍቀዱ፣ለአገርና ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች እየተቀበሉ አዝዞ ማስፈጸም የዘወትር ጥረትዎ የሆነው ንጉሠ ነገስታችንን በህዝቡና በጦር ኃይሉ አባሎች ስም እንድናመሰግን ይፈቀድልን::...

"የደርጉ ፍላጎት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሆኑት ንጉሠ ነገስት የመሰረቷቸውና የደከሙባቸው የተቀደሱ ዓላማዎችን በመከተልእጊቡ ለማድረስ ስለሆነ በማናቸውም ረገድ ግርማዊ ንጉሠ ነገስቱን የሚቃወመውን ሁሉ ተቃዋሚ ነው::ለሥራውም መሰረት ያደረገው የግርማዊ ንጉሠ ነገስት ዙፋን ፍጹም እንዳለ ሆኖእንደተጠበቀና እንደተከበረ እንዲኖር ነው::...

"...እንዳልካቸው ...ቀድሞ በአገሪቱና በህዝቡ ላይ በደረሰው በደሊ ምክንያት የወደቀው ካቢኔ አባልና የኃላፊነቱ ተካፋይ ስለሆኑ በስልጣኑም ላይ ከወጡ በኋላ በጥፋታቸው ምክንያት በጦር ኃይሉ ለተያዙት ዘመዶቻቸው በማዘንበል፣ኢትዮጵያ ትቅደም በማለት ንጉሠ ነገስቱንና ዘውዱን አክብሮ የተነሳው ሰራዊት ተግል እንዲሰናከልከመለያየትና ከማከፋፈል ተንኰል ስላልተቆጠቡ ለአገሪቱና ለህዝቡ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለውጥና ሽግግር በርጋታ እንዳይፈጸም ችግር ስለፈጠሩ፣በአብዛኛውም ህዝብና የጦር ኃይል ስላልተደገፉ ከሥልጣኑ ላይ እንዲወርዱ የግርማዊነትዎን ፈቃድ እንለምናለን::"

ሀምሌ 16 ፡አዲስ ዘመን፡፡"ለምን ደም ይፋሰስ"በሚል አርእስት ስር ከጦር ኃይሎች ኰሚቴ የተሰጠ ማብራሪያ

"የጦር ኃይሉ የሚፈልገው ኢትዮጵያ ሌላው ዓለም ከደረሰበት ደረጃ እንድትደርስ፤ህዝቡ ታጥቆና በርትቶ እንዲሰራ እንቅፋቶች እንዲወገዱ ማድረግ እንጂ የማንንም ሀብትና ንብረት ለመውረስ ወይም ከሌላው ዓለም ህብረተሰብ ተገንጥሎ ብቸኛ ለመሆን አይደለም፡፡

ካለፈው የካቲት ወር አንስቶ እስከዛሬ ድረስ በተካታታይ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሊገኝ የቻለው በአምላክ ትእዛዝና ፈቃድ እንጂ በሰው ኃይል ብቻ የተደረገ አይደለም፡፡... የህዝቡን ስቃይና እሮሮ ረሃብና በሽታ የተመለከተው አምላክ በድንገት ከመሃከላችን ገብቶ ድርብ ስቃይ እንዳይደርስ ኃይሉን ሰጥቶን እስከዚህ ለመድረስ አስቻለን፡፡፡.."

ሀምሌ 20፡ አዲስ ዘመን፡፡"ከጦር ኃይሎች ደርግ የተሰጠ ማብራሪያ"፤ኢትዮጵያ ትቅደም" በብዙ አቅጣጫዎች በሰፊው ሊተረጐም የሚችልና ሊተነተን የሚችል ከፍተኛ ብሄራዊ ጥሪ እንደመሆኑ መጠን፤ሰፋ ባለ ሁኔታ እስከምናቀርብ ድረስ ለዛሬው ከዓላማዎቹ ግንባር ቀደምቹን ባጭር ለመግለጽ እንሞክራለን፡፡"ካለ በኋላ፤ጽሁፉ በጠቅላላው የሚከተሉትን ነጥቦች ይደረድራል፡—

"ኢትዮጵያ ትቅደም"ማለት ከሁሉም በላይ ለአገራችን እናስብ፤ታጥቀን እንነሳና እንስራ፤ጥል፤መለያየት ቀርቶ ለጋራ እድገትና መሻሻል እንስራ፤አንዱ ሌላውን እንደይጨቁን፤ወዘተ...ማለት ነው ብሉ አጠቃለይና የማይጨበጡ ነገሮችን ይዘረዝራል፡፡ምናልባት ቀላል ትርጉምና ተጨባጭነት ያለው ዓረፍተ ነገር ቢኖር የሚከተለው ነው፡—ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት፤"ከፖለቲካ ተጽእኖ የባእድ የምጣኔ ሀብት ጥገኝነት ከሚያስከትለው ስውር ቀኝ ተገዥነት፤ወይም ዘዴያዊ ብዝበዛ ወጥታ ራሷን እንድትችል ቢመስኩ ያልተቆጠበ ትግልና መስዋእትነት እንዲደረግ አጥብቆ የሚጠይቅ ነው፡፡"ከዚህ መለከም አነጋገር በኋላ ትርጉሙ እንደገና ወደ አጠቃላይ ነገሮች ተዛውሮ፤የኑሮ ልዩነት ይስተካከል፤ አለኩል፤ዝሙት፤ስንፍና ይጥፋ ወዘተ... ይላል

ሀምሌ 23 ፡ ስብሰባ ለማድረግ ከደርጉ ፈቃድ ማግኘት እንደሚያስፈልግ ተነገረ፡፡

ሀምሌ 25 ፡"ለወራ ሰራተኞች ማስጠንቀቂያ ተሰጠ፡፡

—"ስብሰባ ለሚያደርጉ የተሰጠ ተጨማሪ ማብራሪያ" ብለው፤ለመሰብሰብ የሚፈልግ የስብሰባውን መሪ ስምና ቦታ በመለየት አስቀድሞ ለደርጉ መጻፍ እንዳለበት ተገለጠ



ነሀሴ 2፡ከጦር ኃይሎች ደርግና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተውጣጣ የጋራ ኰሚቴ ተቋቋመ ከሚኒስትሮች 5 ከደርጉ 6 ሰዎች፡፡—

— በዚሁ እለት በአዲስ ዘመን፤"ከማን ሽሽቶ፤ማንን ዋሽቶ፤ወደማን "በሚል ርእስ የሚከተለውን አለ፡—

"ህዝቡ ከችግሮቹ ሊያመልጥ የሚችልበትን ዘዴ እንዲያቀድ፤መሃይምነትን እንደመቀጣጠሪያ አድርገው የጋረዱት በመሆኑ፤ሀብትና ትምህርት አጣምረው ይዘው በመደለል ከተቆራኙት መዥገሮች ለማላቀቅ፤ከወጥመዱቸው ለማምለጥ ብዙ መሰናክሎች እንዳሉበት ስለምናውቅ ያለማመንታት የቆምነው ለአብዛኛው ደሃ ህዝብ ነው.."

"ደጋግመን እንደገለጥነው ይህ በህዝብ አስተያየትና ድምጽ በመመራት ላይ ያለው ወታደራዊ ደርግ ...በጥፋታቸው እንደሚፈለጉት ባለስልጣኖች በነፃነት ስም ባርነትን፤በስርኢት ሽፋን ኃጢአትን የሚያሰፍኑ ጠማማ ፈራጆችን፤ሀቀኝነት እንደረት የሚመራቸው አስተዳዳሪዎችን ተክቶ ህዝቡ የተለማመደውን ገፍና በደል እንዲሽከም የሚያደርግና ወይንም የጠገበውን አባሮ ገና አዲስ የሚቃምጠውን አገናኝቶ መመለስን ከቶ አይሞክረውም፡፡"

ነሀሴ 4፡ ህገመንግስቱ ታትሞ ስጋዜጦች ወጣ፡፡

ነሀሴ 7፡ አዲስ ዘመን፡፡"ደሞዝ የሚያገኙበትን ሥራ መበደል ለውጥን መቃወም መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡"የሚል ከደርጉ በተሰነዘረ ማስጠንቀቂያ ውስጥ፤ደርጉ እንዲህ ይላል፡፡—

"ኢትዮጵያ ትቅደም ብለን በተነሣሣንበት ባሁኑ ሰዓት...ባዲስ ስሜት ራሳችንን አድሰን ለአዲስ ስራ እንጂ ለምንወዘፍበት አዲስ ሥልጣን መሽቀዳደም አይኖርብንም፡፡ የምንመኘ ብንኖርም አይገኝም፡፡ የህልም እንጀራ ነው፡፡ሥልጣኑ ላይ የሚወጣው ባጭሩ ታጥቆ ሸሚዙን እስኪክንዲ ሲቀስቆ የሚሰራው እንጂ፤በስልጣን ሰበብ ሊሞሸር የሚሻው አለመሆኑ ቁርጡ ካሁኑ መታወቅ አለበት፡፡"

ነሀሴ 9፡ ጽህፈት ሚኒስቴር በጦር ኃይሎች ደርግ ቁጥጥር ስር እንዲሆን ተወሰነ፡፡

ነሀሴ 10፡አንድነታቸውን ለህዝብ ለማሳየት የጦር ኃይሎች ሰልፍ አደረጉ፡፡

ነሀሴ 11፡"የጦር ኃይሎች ደርግ ግንባር ቀደም አርምጃዎች"በሚል ርእስ ስር፤አደስ ዘመን፤ የዘውዱ ምክር ቤት፤የዙፋን ችሎትና ፍርድ አጣሪ መዘጋታቸውን አበሰረ፡፡የተዘጉት በነሀሴ 10 ነበር፡፡

ነሀሴ 14፡23 የኤርትራ መማክርት ሥራቸውን ይለቃሉ፡፡የአምሀጀርን አልቂት በመቃወም፤በጠቅላላው በኤርትራ ህዝብ ላይ የደረሰውን በደል በመግለጥና አሁንም እንዲ

ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ሲፈቱ፣በኤርትራውያን ላይ ግን ልዩነት ተደርጉ በእስር ላይ መገኘታቸውን በመግለጥ ተቃውሞዋል፡፡

—የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ኃላፊዎች የወጣውን ህገመንግሲት እንደሚቃወሙ ተገለጠ፡፡

ነሀሴ 19፡ የንጉሡ ቤተ መንግስቶች "የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት" ተባሉ፡፡

ነሀሴ 22፡ የአንበሳ አውቶቡስ ኩባንያ በመንግስት/በገንዘብ ሚኒስቴር/ስር እንዲሆን ተወሰነ፡፡ አብዛኛዎቹ ባለአክስዮኖች ንጉሳዊ ቤተሰብና መሳፍንት ነበሩ፡፡

ነሀሴ 24፡ አዲስ ዘመን፡፡"ከደርጉ "ለአወናባጆች ማስጠንቀቂያ" በሚል አርእስት ስር "ከጠቅላላው ህዝብ ጋር በመተባበር ለጋራ ጥቅም የመሰረተውን ዓላማ ግብ ለመምታት በሚታገለበት ወቅት፣ከማንኛውም አቅጣጫ የሚሰነዘርበትን ወቀሳና ነቀፋ በደስታ እየተቀበለ በወገን ንፁህ ምክር ወዲያው ለመታረም ዝግጁ ነው፡፡ነቀፌታው ግን፣የአገሪቱን የጠቅላላውን ህዝብ ጉዳይ ወደገል ጥቅም እንዲያዘነበል የሚጪነን ከአገሪቱና ከህዝቡ በፊት ራስን ለማስቀደም የሚደረግ ከሆነ በጥብቅ እናወግዛለን፡፡አለ ደርጉ

ነሀሴ 26፡ በአዲስ አበባ ከተማ ንጉሡን በኃይል የሚቃወሙ የግድግዳ ሥዕሎች በየቦታው ተለጠፉ እነዚህ ስዕሎች ባንዱ በኩል ኃይለ ስላሴ ውሾቹን ሲቀልብ፣በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ ሲያለቅ የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

ነሀሴ 30፡ ሠራዊቱ የንጉሡን የአከባበር ዘዴ እንደ "ብሄራዊ ሀፍረት"ካወገዘ በኋላ፣አርምጃ መውሰዱ እንዳለበት አስታወቀ፡፡ሙሉ ጳጉሜን ያዲስ አበባ ህዝብ ንጉሱ እንዲወገዱ በመጠየቅ ካሳለፈ በኋላ፣የንጉሡ ልጅ የታወቀቸው ዘራፊ ተናኘወርቅ፣መስከረም አንዱ 1967 ተያዘች፡፡በማግስቱም ኃይለ ስላሴ ከሥልጣን ተወገደ፡፡ በዚሁ ቀን "ጊዜያዊ የወታደር አስተዳደር"በደርጉ ተመሰረተ፣ፀረ ዴሞክራቲክ አዋጅ ወጣ፡፡



What are classes?

"Classes are large groups of people differing from each other by theplace they occupy in a historically determined system of social production,by their relation (in most cases fixed and formulated in law)to themeans of production,by their in the social organisation of labour,and,consequently,by the dimensions of the share of social wealth of which they dispose and the mode of acquiring it.Classes are groups of people oneof which can appropriate the labour of another owing to the different places they occupy in a definite system of social economy."

(Lenin,Coll.Works,Moskow 1964;Vol.29,p.421)

What is a revolutionary situation?

"To the Marxist it is indisputable that a revolution is impossible without a revolutionary situation;furthermore,it is not every revolutionary situation that leads to a revolution.What, Generally speaking,are the symptoms of a revolutionary situation? We shall certainly not be mistaken if we indicate the following three major symptoms:(1)when it is impossible for the ruling classes to maintain their rule without any change;when there is a crisis,in oneform or another,among"theupper classes", a crisis in the policy of the ruling class,leading to a fissure through which the discontent and indignation of the oppressed classes burst forth.For a revolution to take place,it is usually insufficient for the "lower classes not to want"to live in the old way;it is also necessary that "they should be unable" to live in the old way;(2) when the suffering and want of the oppressed classes have grown more acute than usual;(3) when, as the consequence of the above causes,there

is a considerable increase in the activity of the masses, who uncomplainingly allow themselves to be robbed in "peacef time", but, in turbulent times, are drawn both by all the circumstances of the crisis and by the "upper classes" themselves into independent historical action.

Without these objective changes, which are independent ofthe will, not only of individual groups and parties, but even of individual classes, a revolution, as a general rule, is impossible. The totality of all these objective changes is called a revolutionary situation....it is not every revolutionary situation that gives rise to a revolution; revolution arises only out of a situation in which the above mentioned objective changes are accompanied by a subjective change, namely, the ability of the revolutionary class to take revolutionary mass action strong enough to break (or dislocate) the old government, which, never, not even a period of crisis, "falls", if it is not toppled over."

(Lenin.Coll.Works.Moscow 1964.Vol.21,pp.213-14, emphasis in original)

## ከታጠቀ አዘጋጅ

ይህ ጽሁፍ የደረሰን በጥቅምት ወር ነበር፡፡በገንዘብ እጥረት ምክንያት
እስካሁን ሳይወጣ ቆይቷል፡፡ጽሁፉ ከተጻፈ ወዲህ የጽሁፉን መልእክቶች አርጌ የሚያስደ
ርግ ለውጥ በኢትዮጵያ አልነበረም፡፡የነበሩትን ዋና ዋና ድርጊቶች/ከጥቅምት ወዲህ/
እንደሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክራለን፡፡

ባለፈት ሁለት ወራት ከተደረጉት አንዱ፣በአሥር ላይ ከነበሩት የቀድሞ ባለ
ስልጣኖች ስልሳ ያህሉ መገደል ነው፡፡/ወታደሩ በሰጠው የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር በመጨረ
ሻው ላይ የተጠቀሱት ሰባቱ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ውስጥ ያልሆኑ፣ ከሻምበል እስከ ተራ
ወታደር ድረስ ማእረግ ያላቸው ነው፡፡እነዚህኞቹ ለምን እንደተገደሉ ስለማናዉቅ እያጣራን
ነው፡፡/ለነዚህ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ለመገደል እርምጃ የተወሰደበት ቀጥተኛው የቅርብ
ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ለማንኛውም የድሮ ኃይላቸውን ለመመለስ ከሚያደርጉት ሙከራ
ነጥሎ ለማየት አይቻልም፡፡እነዚህ ሰዎች የድሮው አገዛዝ ቀንደኞች ቢሆንም የጉልተኛው
መደብ ሆነ ሥርአት ከነሱ ጋር ወድሟል ማለት አይደለም፡፡ መደቡ ተራራ ጫፉ ተመታ
እንጂ አካሉ አሁንም አለ፡፡ይህን እውነት መሳት ወደከፍተኛ የፖለቲካ ስህተት ይወስዳል፡፡

ለጥቆ ለማየት የሚቻለው በደርጉ ውስጥ ሥር ሰዶ የነበረው ቅራኔ ተጻራሪ
ሆኖ መፈንዳቱ ነው፡፡በመሳሪያ ኃይል ብቻ ሊፈታ ቻለ፡፡ የአማን አንዶም ከስልጣን መው
ገዱና በኋላም መገደል የቅርብ ምክንያቱ እንዲሁ ግልጽ አይደለም፡፡ከሁኔታዎች አዝማሚያ
አማን የቀኝ ሰራ ያዘጋጅ እንደነበረ ለመገመት ይቻላል፡፡ የደርጉ በውስጣዊ ቅራኔዎች
መወጠር ስለሚያዳክመው ለህዝቡ ትግል ይጠቅማል፡፡

ከደርጉ የመገደል እርምጃ ወዲህ በደርጉና በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ቅራኔ
ተፈጥሯል፡፡አሜሪካ "እርዳታዋን እንደምታቆም /"ሁኔታው እስኪጣራ ድረስ"ይላል መግለጫ
ው/አስታውቃለች፣የጀርመን መንግስትም እንደዚሁ ፡፡ ነገር ግን ይህ በወዳጆች መሃል ጊዜ
ያዊ መኮራረፍ እንጂ ዘላቂ ጠብ እንዳልሆነ፣ደርጉ እስከመጨረሻው ፀረኢምፔሪያሊስት እን
ደማይሆንና በቅርቡ ኰለሰው እንደሚታረቁ ግልጽ ነው፡፡

ደርጉ ህዝቡን ከትግሉ ለማገለል፣ዲሞክራቲክ መብቶችን ለመገፈፍ የሚወስዳቸው
እርምጃዎች በተባባሰ ሁኔታ ቀጥለዋል፡፡ብዙ ፈላጭ ቆራጭ አዋጆች ተጨምረዋል፣እነሱንም
ከሥራ ላይ የሚያውሉ የጦር ፍ/ቤቶች ተቋቁመዋል፡፡ የኤርትራን ጥያቄ በማመለከተም በ
ኩል፣ደርጉ ትክክለኛ የሆነውን የሰላም ውይይት ከመጀመር በፊት በኤርትራ ህዝብ ላይ
የሚያደርገውን ፋሽስታዊ እልቂት ለመቀጠል መርጧል፣5000 እዲስ ወታደሮች ወደዚሁ
ተልከዋል፡፡

ህዳር 1967